## ምዕራፍ ሀያዐራት

ትዕግሥት የፈተና ውጤት ሊሰጥ አንድ ቀን ሲቀረው ከደብረ ዘይት አዲስ አበባ ገባች ። ወደ ዩኒቨርስቲዉ መኝታ ክፍሏ ስታመራ ፣ አንዳች ነገር የጓሊት ይጎትታት ነበር ። ከዘመዶቿ ጋር ከርማ መለያየቷ ተጫጭኖዋታል ። በዚያ ላይ ማርታና ቤተልሔም ገና ስላልመጡ ብቻዋን ነበረች ።

አቤልን ለማየት ቆርጣ ነበር የመጣችው ። ተለይታው በከረመችበት የዕረፍት ጊዜ ውስጥ ሲናፍቃት ነበር ። ግን ለምን ? መናፈቁን ነው እሷ ያልወደደችው ። ትዕግሥትም እንዶ አቤል ለፍቅር እንግዳ ናት ። በልጅነቷ ጭቃ እያቦካች ጎጆ ሠርታ ፣ "ባልና ሚስት" የተጫወተችበትን ጊዜ ወይም ከትምህርት ቤት ጓደኞቿ ጋር የተቃለደችባቸውን ጊዜያት ታስታውስ እንደሆን ነው እንጂ ፣ ሌላ የፍቅር ትዝታ የላትም ። አሁን ዕድሜዋ ይገፋፋታል ። የወንድ ልጅ ከንድ ተደግፋ በነፋሻማ ስፍራዎች መወዝወዝ ያምራታል ። አፍ ለአፍ ገጥማ ምስጢር የምታወራው አቻ ወንድ ያምራታል ። የወንድ ልጅ ከንፈር ጣዕም መቅመስ የሚያሰኛት ዕድሜ ላይ ነች ። ነገር ግን በዚህ ፋንታ የመጀመሪያ ፍቅሯ ከዐይን የማያልፍ ሆነ ። አቤል ቀርቦ ምስጢሯን አይካፈላትም ። የፍቅር ትኩሳቷን አይጋራትም ፣ የደረቀ ከንፈሯን አያረጥብላትም ፣ ወንዶች ላይ ለሚቅበዘበዝ ዐይኗ ገደብ አይገዛላትም ። እሷነቷን ቀርቦ አያውቅላትም ። በሩቅ እየተያዩ መነፋፈቅ ብቻ !

ትዕግሥት ይህን ሁሉ አመዛዝና ነበር - አቤልን ቀና ብላ ለማየት የወሰነችው ። ትርጉም የሌለው ፍቅር ሆነባት ። ከመጉዳቱና ከማንገብገቡ በቀር ጥቅሙ አልታይ አላት ። እንዳሰበችው የመጣች ዕለት ጨክና ሳታየው ዋለች ። ከደብረ ዘይት ያመጣችው የአገልግል ምግብ ስለ ነበር ፣ ወደ ምግብ አዳራሽም ብቅ ሳትል ዋለች ። ሐሳቧ ሴሚስተሩን በሙሉ ከእርሱ ርቃ ለመቀጠል ነበር ። ግን ያን ዕለቱኑ ወደ ምሽት ላይ ከቁጥጥሯ በላይ የሆነ ውስጣዊ ኃይል እንድትወጣ ገፋፋት ። ዐይኗ ውጭውን ማየት ፈለገ ። ጋቢ ደርባ ወጣች

አቤል ራቱን በልቶ የሚገባጠሙበትን መንገድ እስራታ ነበር የሔደችው። ሆኖም አቤል ወደ መመገቢያው አዳራሽ የገባው መጨረሻ ላይ ስለ ነበር፣ እንዳሰበችው ቶሎ አላገኘችውም ። ዐይኗ ተርቦ ለግማሽ ሰዓት ያህል በምግብ አዳራሹና በወንዶች መኝታ ክፍሎችና መሐል ከተንጎራደደች በኋላ ጨረፍታውን አየች ። አቤል አፉን እየጠራረገ ከምግብ አዳራሹ ወጣ ። እሱን ስታይ የልቧ ትርታ መጨመሩ ራሷን በራሷ ትዝብት ላይ ጣላት ። ካየችው በኋላ ለመሔድ ብታስብም እግሯ አልተንቃነቀም ። ማየት ብቻ ሳይሆን መታየትንም ፈልጋ ነበር ።

ድፍን ባይልም መጨላለም ጀምሮ ስለ ነበር፣ አቤል ትዕግሥትን ከሩቅ አልለያትም ። ቀረብ ሲል ነው በጋቢ ውስጥ የተደበቀ ውበቷ የታየው ። እሷ መሆኗን ዐይኑ እንዳረጋገጠ፣ እየተራመደ ብርክ ሲይዘው ታወቀው ። ሊቀርባት የፈራ ይመስል እርምጃውን ቀነሰ ። እሷም ቆማ አልጠበቀችውም ። እንዳየች ካረጋገጠች በኋላ፣ ዞራ ወደ መኝታ ክፍሏ ተራመደች ። እግሯ እንጂ ልቧ አቤልን መሸሽ አልፈለገም ነበር ። አድራጎቷ እሷኑ መልሶ አሣቃት ። ልታየው ፈልጋ ወጥታ ሲያያት መሸሿ ምን ይባላል ?! ፍቅረኞች ተለያይተው ከርመው ሲተያዩ አንገት ለአንገት ተቃቅፈው እየተሳሳሙ ፍቅራቸውን ይወጣሉ እንጂ ይደባበቃሉ ? ከዚች ደቂቃ ጀምሮ ልቧ አቤልን ብቻ መወንጀሉን አቆመ ። የአቤል ሕመም እንደ ተጋባባት ተሰማት ። " ታዘብኩህ ! " አለችው ልቧን በልቧ ።

አቤል በእይታው ቅጽበት ውስጥ ፊቷ ዐይኑ ውስጥ ተቀረጸበት ። የወፈረች መሰለው ። ዕረፍቱ ተስማምቷት ነበር ማለት ነው ? ደግሞም ስታየው ፈገግ ብላለት በፈገግታዋ የሚንደጉድ ጉንጯን ያየ መሰለው ። ሁሌም ስሜቱ የፈጠረው ምስል ይሆናል እንጂ፣ ባያት ቅጽበት ውስጥ ይህን ያህል ለማጤን የተረጋጋ መንፈስ አልነበረውም ። በደንብ ያየው ጀርባዋን ነው ። ጋቢዋ ከዐይኑ እስኪጠፋ ድረስ ተከተላት ።

ካያት ደቂቃ ጀምሮ ልቡ መሥቃየቱ አልቀረም ። ነገር ግን የዚህ ምሽቱ ሥቃይ ከወትሮው የተለየ ሆኖ ተሰማው ።



ሥቃዩ ውስጥ ደስታም ነበረበት ። 'በዚህ ጽዓት ብቻዋን ምን እንጎራደዳት ? ያውም በወንዶች መኝታ ቤት አካባቢ ! ' ሲል ራሱን ጠየቀ ። ሆን ብላ ልታየው ፈልጋ መምጣቷን ለአፍታም አልተጠራጠረም ። የስንበት ናፍቆቷን በዐይኗ ተወጥታ መሔዷን ልቡ ነገረው ። እናም ለዐይን ፍቅሩ የመሸነፏ ወይም የመድከሟ አዝማሚያ ሆኖ ታየው ። ይህ ነበር በሥቃዩ ውስጥ ደስታን የፈጠረለት ።

ያጋጠመውን ሁኔታ ለሌላ ሰው ለማጫወት ወይም በደስታና ሥቃይ መሐል የሚዋልል ስሜቱን ለማዋየት ፈለገ ። ማታ ለእስክንድር ሊያጫውተው ከጀል አደረገና እስካሁን ያልነበረውን ግልጽነት መጀመሩ አስቸጋሪ ሆነበት ። ስለዚህ ስሜቱን አፍኖ አልጋው ላይ ወጣ ።

በማግሥቱ ጠዋት አንድም ከግቢ የወጣ ተማሪ አልነበረም ። ሁሉም የፈተናውን ውጤት በመጠባበቅ በማስታወቂያ ሰሌዳው አካባቢ ያንዣብባል ። እንደ ተለመደው የብዙ ተማሪ ልብ በድንጋጤ መንጠሩ አልቀረም ። ለፈተና ሲቀርቡ ድንጋጤ ! ለውጤት ሲቀርቡ ድንጋጤ !

የእያንዳንዱ ተማሪ ምኞትና ጭንቀት ሲታይ ተአምር እንጂ፣ የሥራውን ውጤት የሚጠብቅ አይመስልም ።

አቤልና እስክንድርም ወደ ትርምሱ ሊቀላቀሉ ሲሔዱ ከሳምሶን ጉልቤው ጋር መንገድ ላይ ተገናኙ ። ከውጭ እንደ መጣ ማስታወቂያ ሰሌዳው አካባቢ ስላጣቸው፣ እነሱኑ ፍለጋ ወደ መኝታ ክፍላቸው እየገሰገሰ ነበር ።

" እንዴት ነው ? በጠዋት ከተፍ ! " አለው እስክንድር፣ ሰላምታ ሲለዋወጠው ።

" እንዴዬ ! ቶሎ መርዶአችንን እንስማ እንጂ ! " አላቸው፣ እጃቸውን አጥብቆ ጨብጦ እየወዘወዘ ። እስክንድርም ሆነ አቤል በዘዴ እጃቸውን ከሳምሶን ለማላቀቅ እየሞከሩ ነበር ። እሱ በፍቅር ስለሚይዛቸው አይታወቀውም እንጂ እጁ ያማል ። ሲጨብጥ የዱላ ያህል ነው የሚሰነዝረው። አጥብቆ ከያዘም በኋላ አይለቅም ። እሱን ላለመጨበጥ ከሩቅ ሰላም እያሉ የሚሸሹት ተማሪዎች ብዙ ናቸው ።

ገና በጠዋቱ አልቦታል ። መላጣው ራሱ ቅቤ የቀለጠበት መስሏል ። የደረቱ ቅርጽና የክንዱ ጡንቻ እንዲታይለት ጥብቅ ያለ ጉርድ ሸሚዝ ነበር የለበሰው ። ውጤቱን ለማወቅ ከመጠን በላይ ቸኩሎ ነበር ።

“ ዕረፍቱ ተስማምቶሃል ጃል ” አለው እስክንድር ፣ ወደ ትርምሱ ሲያመሩ ።

“ መጠርጠሩስ ! ከቤቴ ሌላ አንዴ አክስቴ ቤት ፣ አንዴ አጎቴ ቤት እያልኩ ስገነባ ነው የከረምኩት ። አቤል ፣ በአንተስ በኩል ዕረፍቱ እንዴት ነበር ? ”

አቤል አልሰማውም ። ወደ ትርምሱ እየቀረቡ በሔዱ ቁጥር ከትርምሱ ውስጥ ትዕግሥትን ለይቶ ለማውጣት ልጃገረዶቹ ላይ ዐይኑ እየተንቀዋለለ ነበር ።

“ ምን አልክ ? ” አለው ሳምሶንን ፣ ጥያቄው ወደሱ መሆኑን በደመ-ነፍስ ተረድቶ ።

“ ዕረፍቱ እንዴት ነበር ? ”

“ ደኅና ነበር ፣ ” አለው ፣ ከጥያቄው ለመገላገል ብሎ ።

“ ብርቅነሽ ጋ ከዚያ ወዲህ ሔደህ ታውቃለህ ? ”

ጥያቄው አስደነገጠው ። እሱ ለተጠየቀው ከሌላ ሰው መልስ ይፈልግ ይመስል ፣ የእስክንድርን ዐይን ዐይን ተመለከተ ። ሳምሶንም እሱን ተከትሎ እስክንድርን ተመለከተ ።

እስክንድር ዐይናቸውን ለመሸሽ ማዶ ማዶ ይመለከት ጀመር ። የብርቅነሽ ስም ሲጠራ ንቅሳቷ ታየው ። ጨዋታዋ ታወሰው ። የዋህ ንጹሕ ሴት ! ‘ ኬሬዳሽን ! ’ አለ በልቡ ።

የሦስቱም ዐይን በየሔደበት ሲያርፍ ያደናገጣቸው ጥያቄ ሳይመለስ ቀረ ።

“ ምን ታያለህ ? ” አለው ሳምሶን እስክንድርን ።

“ አንተስ ምን ታያለህ ? ”

ሁለቱም እርስ በርስ ተንቃቁና ተሣሣቁ ። የአቤልም ዐይን እነሱ ያዩትን ቢያይም ምንም አልተናገሩትም ።



“ እንዴት ደምቃለች ጃል ! ” አለ እስክንድር ፣ ነገሩን ግላጭ አውጥቶ ።

“ ህም ! ” ሲል ሳምሶንም አድናቆቱን ገለጸ ።

የሦስቱም ዐይን ያረፈው ማርታ ላይ ነበር ። ቦግ ብሎ የቀላው የከንፈር ቀለሟና በጸጉር ሥራ ጥበብ ቡናማ የሆነው ጸጉሯ አድምቀዋታል ። ልብሷ ሰው ሳይሆን አሻንጉሊት አስመስሏታል ። ሁለመናዋ ከሩቅ ዐይን ይስባል ። እሷን ካዩ በኋላ ነው ትዕግሥትና ቤተልሔም አጠገቧ መኖራቸውን የለዩት ። የአቤል ዐይን ወደ ትዕግሥት ሲሻገር ፣ የሁለቱ ግን ማርታ ላይ እንደ ተተከለ ነበር ።

ቤተልሔምና ማርታ በጠዋት ነው የመጡት ። እንደመጡ ወደ መኝታ ቤቷ ሔደው ከትዕግሥት ጋር ከተገናኙ በኋላ ፣ ቁርሷን እንኳ በደንብ ሳትበላ እያዋከቡ ነው ወደ ማስታወቂያ ሰሌዳው አካባቢ ያመጧት ። ሦስቱም ውጤታቸውን ለመስማት በጣም ጓጉተዋል ።

የቆሙበት ቦታ ሞቅ ያለ የግል ጨዋታ ይዘው ስለ ነበር እነ አቤልን አላዩዋቸውም ። ማርታ በእጅዋም በአፏም ታወራለች ። በዕረፍቱ ጊዜ ስንት ወንድ እንዳወጣች ፣ ስንት ሆቴል እንዳዳረሰች ትዘረዝራለች ። የሷ ወሬ እንዲደነቅላት ብቻ ስለምትፈልግ ፣ ሌሎች እንዲያወሩ ፋታ አትሰጥም ። ትዕግሥት አድማጭ ነች ። ቤተልሔምም ምንም አትተነፍስም ፣ — ውጭው ባይበርድም ውስጡን እያንቀጠቀጣት ነበር ። ውጤት የማወቅ ሰዓት በመሆኑ ፣ እንደልማዷ በፍርሀት እየተርበደበደች ማርታ የምታወራላትን አንዱንም አልሰማች ።

“ እግዚአብሔርዬ ፣ አንተ ታውቃለህ ! ” አለች ፣ አንድ ሰውዬ ወረቀቶች ከመለጠፊያ ጋር ይዞ ወደ ማስታወቂያው ሰሌዳ ሲጠጋ አይታ ።

ሰውዬውን ተከትለው ሁሉም ወደ ሰሌዳው ግር ብለው ተጠጉ ። የፈተናው ውጤት በየትምህርት ዓመታቸው በተ

ሊያዩ ስሌዳዎች ላይ ተለጠፈ ። ተማሪ አንዱ በአንዱ ላይ እየተንጠራራ ከስሌዳው ላይ የመለያ ቁጥሩን መፈለግ ጀመረ ።

እነ እስክንድር ግርግሩ መሐል ሲደርሱ፡እነ ማርታ ውጤታቸውን ለማየት ስለ ተበታተኑ ተሠወሩባቸው ። የአንደኛና የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ውጤት ብቻ ነበር የወጣው ።

“ የአራተኛ ዓመቶች ውጤት አልደረሰም እንዴ ? ” አለው እስክንድር ፣ ውጤቱን የለጠፈውን ሰውዬ ሲመለስ አግኝቶት ።

“ ከሰዓት በኋላ ” ብሎት ሰውዬው እየተጣደፈ ሔደ ።

“ እስቲ እኔም ጉዴን ልመልከት ” አለ ሳምሶን ፣ አስደንጋጭ ድምፁ ስልት አጥቶ እየተንቀጠቀጠ ።

“ ቆይ ምን አስቸኮለህ ? ግርግሩ ተግ ይበልልህ ” አለው እስክንድር ።

ሳምሶን “ ኧረ ባክህ ! ” ብሎት ፣ ተማሪውን እየገፈታተረ ወደ ሁለተኛ ዓመቶች የውጤት ሰሌዳ አመራ ።

አቤልና እስክንድር ፣ ከግርግሩ መሐል ወጥተው ብቻቸውን ቆመው ቀሩ ። አንዳች ነገር ተጫጭኗቸዋል ፤ አይነጋገሩም ።

ግርግሩን አትኩረው ይመለከቱ ጀመር ። ማንኛውም ነገር ውስጡ ሲሆኑበትና ከውጭ ሲታዘቡት የተለያየ ገጽታ አለው ። የፈተና ውጤት ጊዜ እንዲህ ከሩቅ ሆነው ሲያዩት አሳዛኝ ትርኢት ይታይበታል ። ውጤቱ የድካም ዋጋ ሳይሆን የብሔራዊ ሎተሪ ዕጣ ይመስላል ። አንዳንዱ እየጣቀ ሔዶ ውጤቱን አይቶ ሲመለስ ፊቱ ከሶ ይመስላል ። በፍርሀት እየተንቀጠቀጠ ሔዶ ፣ እየቦረቀ የሚመለስም አለ ። ውጤቱ አስደንግጦት የቆመበት ዘፍ የሚልም አይታጣም ። አብዛኛው ተማሪ ስለ ራሱ የነበረው ግምትና አሁን ያገኘው ውጤት እየተራራቀበት ፊቱን አጨማድዶ ሲመለስ ነው የሚታየው ።



‘ እኔስ ከየትኛው ዐይነት እሆን ? ’ ሲል እስክንድር ራሱን ጠየቀ ። የውጤት ጊዜን ሁኔታ እንዲህ በሩቅ ታዝቦ አያውቅም ነበር ።

አንዲት ልጃገረድ በጓደኞቿ ተደግፋ እያለቀሰች በአጠገባቸው ስታልፍ አይተው ፣ የአቤልም የእስክንድርም ልብ አብሮ አለቀሰ ።

“ አይዞሽ ፤ ዩኒቨርስቲ የሕይወት መጨረሻ አይደለም ” አላት እስክንድር ቀስ ብሎ ።

ቀና ብላ አላየችውም ፤ ጓደኞቿ ግን ያሾፉባት መስሏቸው ዞረው ገላመጡት ። ግልምጫ ከዐፈር የሚደባልቅ ቢሆን ፣ የማይተዋወቁት ሰው ግልምጫ — አሆሆ ! ቶሎ ብሎ ዐይኑን ከዐይናቸው አሸሸ ።

ዘወር ሲል ሚስተር ሆርስ ከሦስት ልጆች ጋር ሆኖ ቅልጥሙን እጥፍ እያረገ ፊቱ ፈክቶ ሲያልፍ አየው ።

“ እንዴት ነው ውጤት ? ፊትህ ሁሉ ጥርስ ሆኖአል ” አለው በሩቁ ፣ ከአኳኋኑ ማለፉን ተረድቶ ።

“ አልሞትንም ፤ ተርፈናል ። የዩኒቨርስቲ ሕይወታችንን አራዝመናል ። ”

“ እንኳን ደስ ያለህ ! ” አለውና ፣ ‘ በቀላሉ የሚደሰት ተፈጥሮ ጥሩ ነው ’ አለ በልቡ ። በድንገት የአቤል ድምፅ አስደነገጠው ።

“ ያቻት ትዕግሥት ! ”

አቤል ከርቀት ትዕግሥትንና ማርታን ሲያይ ሳያስበው ነው ፣ ስሟ ያመለጠው ። በድንጋጤ ስሟን ከመጥራቱ ሌላ የሚጨምርበት ነገር አልነበረም ።

“ እህ ? ” አለው እስክንድርም ደንግጦ ።

አቤል ምንም አልመለሰም ። ፊቱ በቅጽበት ተለዋውጦ ከሰል መሰለ ። ከንፈሩ ተጣብቆ አልላቀቅ አለው ። ዐይኑ ፈዝዞ ቀረ ።

እስክንድርም መልስ አልጠበቀም ። የአቤልን ዐይን ተከትሎ ትዕግሥትንና ማርታን ተመለከታቸው ። ውጤታቸውን አይተው በመመለስ ላይ ነበሩ ። ፊታቸው ዳምኗል ። በኀዘን ተውጠው አንዳችም ቃል ሳይለዋወጡ መሬት መሬት እያዩ ነው የሚሔዱት ። ለእነ አቤል ደግሞ የባሰ ዳምነውና ተክዘው ታዩአቸው ።

ትዕግሥትና ማርታ እነ አቤልን ሲያዩዋቸው፣ መንገዳቸውን አሳብረው በሌላ በኩል ሔዱ። በማርታ ግፊት ነበር ይህ የተደረገው ። ማንም ሳያያት ወደ መኝታ ክፍሏ መሔድ ነው የፈለገችው ።

አቤል መቆም አልቻለም ። ወገቡ የተቀነጠሰ መሰለው። ትዕግሥት ወድቃለች ማለት ነው ? ከዩኒቨርስቲው ልትባረርና ሊያጣት ? ስለ ራሱ ውጤት አንዴም አላሰበ ። መለየት የሞት ያህል ሆኖ ታየው ።

ቃላት መተንፈስ ፈለገ ። ግን ከንፈሮቹ አልላቀቅ አሉት ። እርዳታ በሚጠይቅ አመለካከት እስክንድርን አየው ። ከተረታ ወይም ከደከመ ልብ ብቻ ነው የዚያን ዐይነት እይታ የሚመነጨው ።

“ ምን ልርዳህ ? ” አለው እስክንድር ፣ ሁኔታው ስለገባው ።

አቤል ምንም ሳይመልስለት ፣ በሚስለመለሙ ዐይኖቹ እያየው ፣ ቀስ ብሎ አጠገቡ ያገኘው ነገር ላይ ቁጭ አለ ።

እስክንድር በሐሳቡ ፣ ‘ አሁን ምን ዐወቅንና ነው ? ’ አለ ። ‘ ምናልባት እነዚህ ልጆች ሳይወድቁ በዝቅተኛ ማርክ ብቻ እንደሆነስ የተከዙት ? ለምን ተከትዬአቸው ሔጄ አልጠይቃቸውም ? እነሱ ቢሸሹኝ ተጎድተው ይሆናል ። እኔ ግን ሔጄ ጠይቄአቸው፣ወድቀውም ከሆን ማጽናናት አለብኝ። ካለዚያ የመተዋወቅ ትርጉሙ ምንድን ነው ? ’ አለና አቤልን የተቀመጠበት ትቶት ሔደ ።

ለሁለቱም ከማዘኑም ሌላ ፣ የአንድ ቀንም የጨዋታ ትዝታ ቢሆን መጥፎ ነውና ፣ ከማርታ ጋር የመለያየቱ ነገር እሱንም ቅር ብሎት ነበር ።



ፈጥኖ ሔደ ። ሲደርስባቸው ቀድማ ያየችው ትዕግሥት ነበረች ። በደካማ ፈገግታ ሰላምታ ሰጠችው ። ማርታም እሷን ተከትላ ዘወር ስትል አየችው ። ሰላምታ ልትሰጠው ብትፈልግም ፈገግ ማለት አልቻለችም ።

እስክንድር አጠገባቸው ከደረሰ በኋላ፣ ስለ ውጤታቸው መጠየቅ ፈርቶ ከንፈሩ ይንቀጠቀጥ ጀመር ።

“ እንዴት ነው ? ” አላቸው ፣ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ፣ አንዴ ወደ ማርታ ፣ አንዴ ወደ ትዕግሥት እየተመለከተ ።

“ ዩኒቨርስቲያችሁን ለቀቅኩላችሁ ፤ እናንተው ኑሩበት ! ” አለችው ማርታ ቀድማ ። መንፈሷ ቢደክምም ምላሿ አልሞተም ነበር ።

“ ምነው ? ውጤቱ መጥፎ ነው እንዴ ? ”
“ ኤጭ ! ”

ከንፈሩን መጠጠና ወደ ትዕግሥት ዞሮ ፣ “ የአንቺስ ውጤት እንዴት ነው ? ” ሲል ጠየቃት ።

“ ጥሩ ነው ። በመካከለኛ ውጤት አልፌአለሁ ” አለችው በፈገግታ ።

“ እንኳን ደስ ያለሽ ! ዋናው ማለፍሽ ነው ! ! ” አለና እሱም ፈገግ ብሎ እንደገና ጨበጣት ።

ማርታ ሁለቱንም በቅናት አስተያየት ሳጠቻቸው ። ዐይን የሚገድል ቢሆን ሁለቱም የቆሙበት ክው ብለው ቀርተው ነበር ።

እስክንድር ደስታና ኀዘን መሐል ገብቶ ወደ የትኛዋ እንደሚሆን ግራ ገባው ። “ ግማሽ ፊትን አጥቁሮ፣ ግማሽ ፊትን ማሣቅ ቢቻል እንዴት ጥሩ ነበር ! ’ አለ በልቡ ።

ማርታን ፊት ለፊት ሊያያት አልደፈረም ። ቀስ ብሎ በስርቆሽ ተመለከታት ። የጠወለገች አበባ መስላለች ። ‘ ለካ ውበት የስሜት ነጸብራቅ ነው ? ’ አለ በሐሳቡ ። ስሜቷ

ከውስጥ ሲነድ ፥ ሲቃጠል ፥ ሲብከነከን ታየው ። ድርብ የከንፈር ቀለሟ በመጠውለጉ ፊቷ ላይ ጎልቶ ምናምን የላሰች አይጥ አስመስሏታል ። ቅንድቧ ብቻ እንደ ወትሮው ይርገበገባል ።

እስክንድር የቅንድቧን መርገብገብ አይቶ ወሬ እንደ ምትፈልግ ዐወቀ ። ግን ምን ዐይነት ወሬ ? በእሷ መውደቅ ምክንያት ተማሪውንና አስተማሪውን ማማት መበጨቅ ?

“ አይዞሽ ማርታ ፥ ዩኒቨርስቲ የሕይወት መጨረሻ አይደለም ” አላትና ፥ አንድ ቀን ያጫወተችውን አስታውሶ ፥ “ ደሞም ከዚህ ወጥተሽ ስኮላርሽፕ መጠበቅ ትችያለሽ ” አላት ።

“ እኔ ማርታ ጉዳዬም አይደል ! ብቻ እንኳን ዩኒቨርስቲ የምትሉትን አየሁላችሁ !

እስክንድር በልቡ ፥ ‘ እኛ ደሞ ምን አደረግንሽ ? ’ ብሎ ጭጭ !

“ የማትስ አስተማሪ’ኮ ነው ጉድ ያረገኝ ” አለች ትንሽ ቆየችና ፥

“ እሱ ‘ F ’ ባይሰጠኝ ኖሮ ሌላው ትምህርት አል ጎዳኝም ነበር ። ”

“ ማነው እሱ ? ” አላት ፥ ያስተዛዘናት መስሎት ።

“ አቶ ኃይሉ የሚሉት አንድ ሽማግሌ አለ ። ላውጣሽ ብሎኝ ስሉ ዘጋሁት ቂጭቱን ተወጣብኝ ። ”

“ ያሳዝናል ! ” አለ እስክንድር ፥ ውሸቷ ኮርኩሮት በሆዱ እየሣቀ ።

“ ደሞ ከእሱ ጋር ልውጣ እንዴ ? ቅሌታም ሽማግሌ ! ”

እስክንድር እንደገና ከንፈሩን መጥጦ ዝም አለ ። ማርታ በሽቀች ። ዝምታውን አልወደደችም ። ወሬዋን እያዳነቀ ከእሷ ጋር አብሮ መምህሩን ያለ መወንጀሉ ነው ያናደዳት። እስክንድር ደግሞ ይህን ለማድረግ ኅሊናው አልፈቀደለ



ትም ። የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ በነበረበት ጊዜ፥አቶ ኃይሉ 101 ሒሳብ አስተምረውታል ። እናም እንዲህ በቀላሉ የሚ ልከሰከሱ ሰው እንዳልሆኑ ያውቃል ። እንዲያውም ለእምነ ታቸውና ለሥራቸው የቆሙ ስለሆኑ፥አንዳንድ ሰዎች “ግትር” የሚል ስም ሰጥተዋቸዋል ።

“ ቶሎ ቶሎ እንሒድ እባክሽ ! ” አለችና ማርታ ትዕግ ሥትን አመናጨቀቻት ።

“ እሺ ” አለችና ትዕግሥት እየተከተለቻት ፥ “ የእና ንተስ ውጤት እንዴት ነው ? ” አለችው - እስክንድርን ። የአ ቤልን ውጤት ለማወቅ ጓጉታ ስለ ነበር ነው ደፍራ የጠየ ቀችው ።

“ የእኛ ገና ከሰዓት በኋላ ነው ” አላት ።

“ እሺ በል ፥ ቤተልሔምን ካገኘሃት ወደ መኝታ ክፍል መሔዳችንን ንገራት ” አለችው ።

በእሺታ ራሱን ነቀነቀ ። እነሱ ከአጠገቡ ሲሔዱ እሱ ወደ ኋላው መመለስ አልቻለም ። ቆሞ ተመለከታቸው ። ለማርታ ከልቡ አዘነላት ። ተዋውቆ መለያየት እንዴት አሳዛኝ ነገር ነው ! ያቺ አብረው ያሳለፏት አንዲት ቀን ትዝ አለችው ። ባይሳካም ከእሷ ጋር ተባብረው ለመርዳት ሞክ ረው ነበር ። ሐሜት መውደዷና ቀናተኛነቷ ፊቱ ላይ መጡ በት ። አንድ ቦታ የማያርፉት ዐይኖቿ ሲቁለጨለጩ በሐሳቡ ታየው ። አንድ ቀን ፥ “ ያ ነገር አለህ እንዴ ! ” ያለችው ታወሰው ። እሷን ለማውጣት ብር አጥቶ ድህነቱን የረገመ ባቸው ቀናት ታወሱት ።

“ ወይኔ እስክንድር ! ” አለና ከኪሱ የማስታወሻ ደብ ተሩን አወጣ ። የማርታ ስልክ ቁጥር እውስጡ መኖሩን ካረ ጋገጠ በኋላ ፥ መልሶ ኪሱ ከተተው ።

ወደ አቤል ሲመለስ ከቤተልሔም ጋር መንገድ ላይ ተገናኙ ።

ብቻዋን ትፍነከነካለች ። ዐይኗም ጥርሷም ጉንጯም ሁለመናዋም ይሥቃል። ዐይኗ መልካም ዜና ለማብሠር የሚ

ያውቀውን ሰው ፍሊጋ ይንቀለቀላል ። ውጤቷን መጠየቅ አስፈላጊ አልነበረም ።

" እንኳዋን ደስ ያለሽ ! " አሳት እየሣቀ ።

" በአምላክህ ! የናንተስ ገና ነው ? "

" ገና ፣ ከሰዓት ። "

ጨበጣት ። እጅዋ ፣ ብብቷ ፣ ጡቷ ፣ ሁለመናዋ ላብ ያመነጫል ። ከመቼውም የበለጠ ወፍራ ታየችው ።

" ማርታና ትዕግሥት ወደ መኝታ ቤት ሔደናል ብለውሻል " አላት ፣ ሲጨብጣት የራሰውን እጁን ለማድረቅ ቀስ ብሎ ሱሪው ላይ እየጠረገ ።

" እነሱን ፍሊጋ ' ኮ ነው የምሔደው ። እንዴት ሆነው ይሆን ? '

" እኔ እንጃ ፣ በደንብ አልጠየቅኳቸውም " አላት ፣ ነገሩን ለማሳጠር ብሎ ። አቤልጋ ደርሶ የትዕግሥትን መልካም ዜና ለማብሠር ቸኩሎ ነበር ።

ከነበረበት ቦታ እንደ ተቀመጠ አገኘው ።

" ስማ አቤል ፣ ትዕግሥት ዐልፋለች " አለው ።

አቤል ጆሮውን ማመን አቃተው ፤ ከተቀመጠበት እንደ አክሮባት ዘሎ ተነሣ ።

" እ ? ምን አልክ ? "

" ትዕግሥት ዐልፋለች ። ማርታ ነች የወደቀችው ። "

የአቤል ገጽታ ላይ የነበረው የትካዜ ደመና ተበታትኖ ጠፋ ። ከደመናው ውስጥ ፀሐይ ብቅ አለች ።

የትዕግሥት ማለፍ ብቻ ሳይሆን የማርታም መውደቅ የአቤልን ደስታ ድርብ እንዳደረገለት እስክንድር ገመተ ። ' ግን ለምንድን ነው የምንጠላውን ሰው ክፉ እንዲደርስበት



የምንመኘው ? ' አለ በሐሳቡ ። ሆኖም ለማሰብ ፋታ አላገኘም ። ሳምሶን ' ጉልቤው ' ውጤቱን አይቶ ሲመለስ አየው ።

አረማመዱ አላማረውም ። ፊቱ ከበደው ። አኩርፎ ከቤቱ የወጣ ሕፃን ልጅ መስሏል ። የሚለውን ለመስማት እስክንድርና አቤል ቸኩሉ ።

" ወደቅኩኮ ! " አላቸው ፣ አጠገባቸው ከመድረሱ ።

" እ ? ! " አሉት ሁለቱም ተደናግጠው ።

እስክንድርና አቤል እንዴት እንደሚያጽናኑት ግራ ገብቷቸው ተፋጠው ቀሩ ። እሁንም ግማሽ ደስታ ግማሽ ኀዘን ! ይህች የተዘበራረቀች ዓለም !

" አየህ ፣ አንድ ዓመት ነው የምታቃጥለው " አለው እስክንድር ፣ ከንዱን ይዞት መንገድ ከጀመሩ በኋላ ፤ " በሚቀጥለው ዓመት እንደገና ገብተህ መቀጠል ትችላለህ ። "

" ነገሩ ነው እንጂ የሚያበሽቀው ! " አለ ሳምሶን ፣ ጥርሱን ነክሶ ።

' ደሞ አንተ ማንን ልትወነጅል ይሆን ? ' አለ እስክንድር በልቡ ። ' በራሴ ድክመት ነው የወደቅኩት የሚል ተማሪ ማን ይሆን ? '

ትንሽ እንደ ሔዱ ሳምሶን ድንገት ቀጥ ብሎ ቆመ ። ቤተልሔም ወደ መምህራን ቢሮ ስታልፍ በርቀት አይቷት ነበር ። እሱ ውጤቱን ሊያይ ሲሔድ እሷ በውጤቷ ተደስታ ስትቦርቅ አይቷታል ። ያኔ ምንም አላላት ። አሁን መውደቁን ካወቀ በኋላ ግን በእሷ ማለፍ ተናደደ ። እና ከሩቅ ሲያያት ከንፈሩን ነከሰባት ።

ቤተልሔም ወደ መኝታ ክፍል ከመሔዷ በፊት ለለማ ደስታዋን ልታበሥረው እየሔደች ነበር ። እንዷኩታ እንደ ገባች ከቢሮው ተቀምጦ አገኘችው ።

" እህ ፥ ውጤት[እንዴት]ነው ? " አለ ገና ሲያያት ።

" ኮንግራጁሌሽን ! አልፌአለሁ " አለችው ፥ በተቀመጠበት ልታቅፈው እየተንደረደረች ።

" ወዳጅ ዘመድ ይኑር በይ " አላት እርዳታውን ለመጠቀም ።

" ይኑር ! " ብላ አንገቱ ላይ ተጠመጠመችና ጉንጩን ሳመችው ።

" ምን ምን ደኀና አገኘሽ ? " ሲል ጠየቃት ።

" ሒሳብ ' 203 ' ጎጆ ሠርቻለሁ ። "

በዩኒቨርስቲ ውስጥ 'F' ያገኙበትን ትምህርት " ባንዲራ ሰቅያለሁ ' ሲባል ' A ' ያገኙበትን ትምህርት ደግሞ ፥ ' ጎጆ ሠርቻለሁ ' ማለት የተለመደ ቋንቋ ሆኖአል ።

" እሱማ የኔው ነው " አላት እንደገና ባለውለታነቱን ለመጠቆም ።

" እኮ ! " አለችው እየቦረቀች ።

" ታዲያ ጎጆውን የሠራው ማነው ? እኔ ነኝ ወይስ አንቺ ? "

" አንተ ! " ብላው እንደገና ልትስመው ከንፈሯን ስታስጠጋ፥ በሩ በድንገት ብርግድ አለ ። ሁለቱም እንደ ተቃቀፉ ክው ብለው ቀሩ ።

የገባው ሳምሶን " ጉልቤው " ነበር ። አውሬ መስሎ ታያቸው ።

ሁኔታቸው የፊልም ትርኢት መሰለ ። እነሱ ዱብ ዕዳ እንደ ወረደባቸው ፍቅረኞቹ በጭንቀት ተቃቅፈው ፥ ሳምሶን ቆሞ በፍቅረኞቹ ላይ ሽጉጡን የደገነ ፥ " ቴክስ " ይመስል ነበር ።



" ምን ፈለግክ ? " አለው ለማ ፥ ድንጋጤው ከበረደለት በኋላ በትዕቢት ድምፅ ። ሳምሶን ለእሱ አልመለሰላትም ።

" አንቺ ሸርሙጣ ! " አላት ቤተልሔም ላይ አፍጦ ። " እናንተ አስተማሪ እያወረዳችሁ ትኖራላችሁ ፤ እኛ ግን እንባረራለን ! "

" ወይኔ ! " ብላ ቤተልሔም ለማ ሥር ሽጉጥ አለች ። ሊውጣት የመጣ ነው የመሰላት ። ዐይኖቹ ውስጥ የሚንቀለቀለው የንዴት እሳት አስፈራት ። ሽንቷ አምልጧት ጭርር ሲል ተሰማትና ጭንና ጭኗን አጋጠመች ።

ለማና ሳምሶን ተፋጠጡ ። የአንበሳና የነብር ፍጥጫ መሰለ ። በጉልበቱ የሚተማመነው ሳምሶን ፥ ለማ ፊት እንደ ቆመ ጡንቻውን ለመሰንዘር ምን እንዳገደው ለማሰብ ሞከረ። ሕግ ! የሰዎችን የስሜት ፈረስ ለጉሞ ሲይዝ ታየው ።

" እንዴዬ ! አሁን ምንድነው የፈለግከው ? " አለው ከተቀመጠበት ለመነሣት እያሰላ ።

" ምን አገባህ ! " ብሎ ሳምሶን፥ ሌላ መናገር ፈርቶ እንዳፈጠጠ፥ ያላየው ሰው ከኋላ መጥቶ በድንገት ትከሻውን ጨመደደው ።

" ምን ማድረግህ ነው ሳምሶን ? " አለው እስክንድር ፥ ትከሻውን እንደ ጨመደደ ከቢሮው ሊያስወጣው እየታገለ ። ከእሱና ከአቤል ተለይቶአቸው መምጣቱ ከንክኖት ነበር ፥ እስክንድር እየሮጠ የደረሰበት ።

" ልቀቀኝ ! " አለው ሳምሶን ፥ መጋበዙ እልሁን አግሎበት ።

እስክንድር በግድ እየጎተተ ከቢሮው ካወጣው በኋላ ፥ " ዕረፍ ሳምሶን " አለው ፥ " ነገሮችን ለማመዛዘን ሞክር ። ለማ ቤተልሔምን ይጠቅማት ይሆናል እንጂ፥ አንተን አይጎዳህም ። ምክንያቱም ቀድሞ የምትዋደዱበት ወይም የምትጣሉበት ምንም ግንኙነት አልነበራችሁም ። "

" እንጃልህ ! " አለና እሉም ላይ አፈጠጠበት ። ' ወቾጉድ ! ዛሬስ ለእኔም አይመለስ ' አለና ቀስ ብሎ እያባበለው ይዞት ሔደ ።

እስክንድርና አቤል ፣ ሳምሶንን እያባበሉ ወደ መኝታ ክፍሉ ከወሰዱት በኋላ ፣ ስለ ራሳቸው ለማሰብ ተገደዱ። የሌላውን የፈተና ውጤት የሰማው ጆሮአቸው የራሳቸውን ለመስማት ተጣደፈ ። መውደቅና ማለፍ ሁለቱ ተቃራኒ ነገሮች እስካሉ ድረስ ፣ መከሠታቸው የግድ ቢሆንም ፣ የማንም አእምሮ በቀላሉ አይቀበላቸውም ። ከሰዓት በኋላው ለእነአቤል በጣም ራቀባቸው ። በተለይ አቤል የትዕግሥትን ማለፍ ከሰማ በኋላ፣የራሱን ውጤት ለማወቅ ለምን እንደሚጓጓ ሊገባው አልቻለም ። ምናልባት ተአምር ይወርድ ይሆን ?

ሁለቱም፣ ውጤት ከሰማው ተማሪ ጋር መቀላቀል አልፈለጉም ። ግን ጆሮአቸውን በጥጥ አይደፍኑት ነገር ! ባለፉ ባገደሙበት ቦታ ተማሪው በቡድን ቆሞ አንዱን ሲያነሣ አንዱን ሲጥል መስማት አስለቻቸው ። አንዱ በአንዱ ሲቀና ወይም ደግሞ መምህሩን ሲወነጅል ነው የሚሰማው ።

በዚህ ዓለም ላይ ማን ይሆን ለኀሊናው ሐቀኛ የሆነ ፍጡር! ሁሌም የራሱን ማንነት ደብቆ ሌላውን ሲወነጅል ነው የሚገኘው ሁሉም ። ተማሪው አስተማሪውን በማርከስ ይወነጅላል።ሠራተኛ አለቃውን ይወነጅላል።አለቃም ድክመቱን በበታች ሠራተኛ ላይ ይለጥፋል ። ለዚህ ምንጩ ምን ይሆን ? የአስተዳደጋችንና የአኗኗራችን ኋላቀርነት የፈጠረብን ችግር ይሆን እንዴ ? ምናለበት አንዱ ሌላውን ከመወንጀሉ በፊት ፣ " ለመሆኑ እኔ ማን ነኝ ? " ብሎ ራሱን መጠየቅ ቢችል ? አንዱ ከሌላዉ ጋር የሚኖረው የግንኙነት መሠረት ሥራና የሀገር ዕድገት ሆኖ ሳለ ፣ እርስ በርስ መበጫጨቅ ቢቀር ምናለበት ? ማንም ከምድር በላይ ወይም ከምድር በታች ላይኖር ፣ ለመበላለጥ በምናደርገው ቅናት የበዛበት ፉክቻና ግላዊ ርኩቻ የጋራችን የሆነችውን ምድር ባንጎዳት ምናለበት ? እስክንድር በሸቀ ።

ከቀትር በኋላ፣ ከእስክንድርና ከአቤል ቀድሞ ውጤቱን የቀመለከተው ' ድብርት ' ነበር ።



" ውጤት ወጥቷል " አላቸው ፣ የራሱን አይቶ ወደ መኝታ ክፍሉ ከተመለሰ በኋላ ፣ ደስታ አፍኖት ሲያልጎመጉም ጥርሱን አሳይቶ አልሣቀም ።

" ያንተ እንዴት ነው ? " አሉት ።

" ግሩም ነው ! "

" ስንት ጎጆ ሠራህ ? " አለው እስክንድር ።

ሦስቱን ጣቶቹን አሳያቸው ።

' የጉልበት ዋጋ ነው ! ' አለ እስክንድር በልቡ ። የ'ድብርት ' አጠናን ምንጊዜም የጉልበት ሥራ ያህል በመታገልና ብዙ ሰዓት በማጥናት ስለሆነ፣በጉልበቱ ዩኒቨርስቲ መቆየቱን ሁሉም ያውቅለታል ።

ወዲያው እስክንድርና አቤል ተያይዘው ወደ ሰሌዳው ሔዱ። የሦስተኛና የአራተኛ ዓመት ተማሪዎች ቁጥር ያን ያህል ብዛት ስለ ሌለው፣በቀላሉ ወደ ሰሌዳው ተጠግተው ተመለከቱ ። እስክንድር በጥሩ ውጤት ዐልፏል ። የአቤል ውጤት ግን አልወጣም ።

አቤል ራሱን ማመን አቅቶት የመታወቂያ ወረቀቱን ከኪሱ አውጥቶ የመለያ ቁጥሩን ተመለከተ ። ያ ቁጥር ሰሌዳው ላይ የለም ። ማለፍም ሆነ መውደቅ የግድ ሰሌዳ ላይ መውጣት አለበት ። እና የአቤል ከዚህ ከሁለቱ ውጭ ምን ሊሆን ይችላል ?

የእስክንድር ማለፍ ሲያስደስታቸው ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአቤል ጉዳይ ሁለቱንም ግራ አጋባቸው ። እስክንድር ልቡ ፈራ ። ስሜቱ መጥፎ ነገር ጠረጠረ ። ለማንኛውም ተያይዘው ውጤቱ ወደ ተዘጋጀበት ቢሮ ሔዱ ።

" አቤት ! ምን ነበር ? " አለቻቸው ጸሐፊዋ ፣ የምታንቀጫቅጨውን ታይፕ አቋርጣ ። " የእሱ ውጤት አልወጣም ። እና . . . " ብሎ እስክንድር ወደ አቤል እያመለከተ ንግግሩን ሳይጨርስ አቋረጠችው ።

" ስሙ ማን ነው ? "

" አቤል ። የፍልስፍና ትምህርት ክፍል ። "

“ እሃ ! አቤል ሙሉዬ ፣ ያንተ ውጤት አልደረሰንም ። እስኪ ዮናታንን ሒደህ አነጋግራቸው ” አለችና ሥራዋን ቀጠለች ።

‘ ውጤቴ ዮናታንጋ ምን ያደርጋል ? ’ አለ አቤል በልቡ። ዮናታንን ማየት አልፈለገም ነበር ። በዝጉ ውስጥ ሲሸሻቸው ነው የከረመው። ምክራቸውን አለ መስማቱና ሕክምናውን ያለ መቀጠሉ እያሳፈሩት ከእሳቸው ለመራቅ ሞክሮ ነበር።

የግዱን ከእስክንድር ጋር ሆኖ ወደ ዮናታን ቢሮ ሔደ። ዮናታን የሉም ። ቢሮአቸው ተቆልፎአል ።

“ ምን ይሻላል ? ” አለ የእስክንድርን ዐይን ዐይን እያየ ።

“ ምን ይሻላል ? ” ብሎ እስክንድርም ቃሉን በትካዜ ድምፅ ከደገመ በኋላ ፣ “ እንግዲህ ነገ መጥተን እንጠይቃቸዋለን ። መቼም ከአሁን በኋላ አይገቡም ” አለው እያስተዛዘነ ።

ነገ እንዴት ይነጋ ይሆን ? የጭንቅ ምሽት ፤ የመከራ ሕልም ሌሊት ።



# ምዕራፍ ሀያአምስት

በማግሥቱ ጠዋት፣ አቤልና እስክንድር ዮናታንን ቀድመው ነበር ፣ ከቢሮአቸው የደረሱት ። አቤል ዐይናቸውን ማየት ቢያስፈራውም አልቀረለትም ። ለሰላምታ እጁን ሲዘረጋላቸው፣አንገቱን ደፍቶ መሬት መሬት እያየ ነበር ።

“ እሀሳ ፣ ምነው እንዲህ ጠፋችሁ ? በዕረፍታችሁ ጊዜ ጭራሹን ሸፍታችሁ ከረማችሁ ! ” አሉ ዮናታን ።

“ምን . . . እንዲያው ፣ ባናስብበት ነው ” አለ እስክንድር ፣ መልሱ ጠፍቶት እየተንገዳገደ ። ከአቤል ለመስማት ዐይን ዐይኑን ተመለከቱት ። አቤል የመጣበትን ጉዳይ አዘግይቶ ለመልካም ማኅበራዊ ግንኙነት ሲል፣ ላይ ላዩን ማውራት የማይችል ፍጡር ነው ። የመጣው ስለ ፈተናው ውጤት ለማወቅ ነው ፤የሚፈልገውም አንዲት የዮናታንን ቃል ነው ።

ዮስቱም ከልባቸው ጋር ድብብቆሽ ሲጫወቱ ቆዩ ። ዋናውን አርዕስት የሚጀምረው ጠፉ ።

“ ውጤትህ እንዴት ነው ? ” አሉት ዮናታን ፣ እስክንድርን ። ለመንደርደሪያ ያህል እንጂ የእስክንድርን ውጤት ካወቁት ቆይተዋል ።

“ ጥሩ ነው ” አላቸው ።

“እ . . . የአቤል ውጤት እንኳ አልደረሰውም መሰለኝ ” ሲሉ በዝግታ ፣ ወደ ዋናው ጉዳይ ገቡ ።

አቤልና እስክንድር በአዎንታ ራሳቸውን ነቀነቁ ።

“ አዎ . . . እ . . . ውጤቱ እንኳ ደኅና ነበር ። ነገር ግን እኛ አቤልን በደኅና ውጤት ሳይሆን በማዕረግ ማስመረቅ ስለምንፈልግ ፣ ውጤቱ ከመሰጠቱ በፊት የፍልስፍናው ትምህርት ክፍል በእሱ ጉዳይ ላይ መነጋገር ይፈልጋል ። ለዚህ ነው፣ ውጤቱ የዘገየው” አሉ ፣ ወደ እስክንድር እየተመለከቱ ፤ እግረ መንገዳቸውንም በስርቆሽ እይታ የአቤልን ስሜት እያጠኑ ። የአቤልን ስሜት ላለመጉዳት የፈጠሩት ውሸት ነው እንጂ ውጤቱስ ደኅና አልነበረም ።

ዮናታን የተማሪዎቻቸውን የፈተና ወረቀቶች በሚያርሙበት ጊዜ፣በመጀመሪያ የተመለከቱት የአቤልን ነበር ። አንድም የጠለቀ መልስ የሰጠበት ጥያቄ የለም ። የእያንዳንዱን መልስ ጨረፍ ጨረፍ አድርጎታል ። መልሱን የማያውቀውንም ጥያቄ ባዶውን ትቶታል ። ዮናታንም ለማየት ያህል ተመለከቱት እንጂ፣ ለአቤል ወረቀት ደረጃ ለመስጠት አል ነበረም ። በዮናታን የአሠራር ዘዴ ውስጥ የመጨረሻ ፈተና የወሳኝነት ቦታ የለውም ። ለተማሪዎቻቸው የውጤት ደረጃ የሚሰጡት በመጨረሻው ፈተና ሳይሆን ሴሚስተሩን ሙሉ ተማሪው ባሳየው የትምህርት እንቅስቃሴ ነው ። እናም “ ምን መደረግ አለበት ? ” ሲሉ አሰቡ ። በዚያውም ሌሎቹ መምህራን ለአቤል ምን ዓይነት ውጤት እንደ ሰጡት ስለንጉሔደው ጠየቁ ።

አቤል ከሚወስዳቸው አምስት ኮርሶች ውስጥ ከዮናታን በስተቀር የአራቱ መምህራን ውጤት ተሰጥቶባቸው ነበር ። በሁለቱ የትምህርት ዓይነት ‘ D ’ በሁለቱ ደግሞ ‘F’ ሰጥተውታል ። ‘ D ’ የሰጡት መምህራንም ምናልባት በመመረቂያው ዓመት እናጨናግፈውም ከሚል ርኅራኄ የመነጨ ሳይሆን አልቀረም ። ዮናታን ይህን ውጤት ባዩበት ጊዜ የቆሙበት እንቅጠቅጣቸው ። ‘ በሰው ሕይወት መፍረድ እንዴት ቀላል ነው ? ’ ሲሉ አሰቡ ። እናም ወዲያው ከቢልልኝ ጋር ለመነጋገር ወደ ቢሮአቸው ሔዱ ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአቤልን ጉዳይ በመከታተል የሥነ - ልቡናው መምህር ቢልልኝ በጥብቅ እየረዷቸው ነበር ።

የዮናታን ተረብሾ መሔድ ቢልልኝንም ቢረብሻቸውም የዚያኑ ያህል የሚጽናኑበት ነገር በልባቸው ይዘው ነበር ። በአቤል ጉዳይ ላይ ከሥራ ረዳቶቻቸው ጋር ባካሔዱት ጥናት ብዙ መረጃዎች ማግኘታቸው ልባዊ ደስታ ሰጥቶአቸዋል ። ሆኖም ጥናታቸው ውጤት ላይ ከመድረሱ በፊት፣አቤል ከዩኒቨርሲቲው መባረሩ ሌላው አሳሳቢ ነገር ነበር ። ዮናታንና ቢልልኝ በጉዳዩ ላይ ከተወያዩ በኋላ፣አንድ መደምደሚያ ላይ ደረሱ ። የነበረው ምርጫ ዮናታን ለአቤል ወረቀት ውጤት ሳይሰጡ መተው ነበር ። የአምስቱም ኮርሶች ውጤት ካል ተሟላ፣ጠቅላላ ውጤቱ ተጠናቅሮ ለተማሪው ሊቀርብ አይ ችልም ። ዮናታን ይህን ሲያደርጉ በፍልስፍናው ትምህርት



ክፍል ለሚነሣው ክርክርም ሆነ በግል ለሚጠየቁት ማንኛውንም ኃላፊነት ወስደው ነበር ። ምናልባትም እንዲህ ዐይነቱን ኃላፊነት እንዳይፈሩ ያደረጋቸው ንጹሕ እምነታቸው ሊሆን ይችላል ።

“ ታዲያ እንዴት ይሻላል ? ” አላቸው እስክንድር ተጨንቆ ።

“ ምንም ችግር የለውም ። ጉዳዩ በጥቂት ቀናት ውስጥ ውጤት ያገኛል ” አሉ ዮናታን ፣ ቢልልኝ የሰጣቸውን መተማመኛ ተመርኩዘው ።

አቤል መተንፈስ ፈለገ ። የዮናታንን ስሜት ሳይጎዳ መናገር የፈለጋቸው ቃላት፣ ከልቡ ሳይሆን ከመሬት ውስጥ የሚፈልቁ ይመስል ፣ መሬት መሬቱን ተመለከተ ።

“ እርስዎ ሊረዱኝ ደክመዋል ። እና አሁን ባልፍም ብወድቅም ምንም አይደለም ” አላቸው ፣ በዐይኑ እያስተዛዘነ ።

“ ግን አንተ የምትወድቅ ተማሪ አይደለህም ” አሉት ። እሳቸውም ፣ የልባቸው ኀዘን ፊታቸው ላይ እየተነበበ ፣ “ ለማንኛውም አትጨነቅ ። ቅድም እንዳልኩህ በጥቂት ቀናት ውስጥ ውጤትህን ታገኛለህ ። ”

‘ ጥቂት ቀናት ? እስከ መቼ ? ምነው የእኔ ብቻ እንዲህ አከራካሪ ሆነ ? መውደቅ ወይም ማለፍ — ከሁለቱ አንዱ ነው ድርሻዬ ። ካላጠኑ ማለፍ እንደማይቻል ዐውቃለሁ ። ምነው አሁን ከመውደቁ አፋፍ ላይ ስደርስ ልቤ ተንቀጠቀጠ ? ለምንስ ሰው አስቸግራለሁ ? ’ እያለ በሐሳብ እየዋዠቀ ፣ ዮናታንን በጥያቄ ዐይን ተመለከታቸው ።

“ መውደቅ ” ከሚለው ቃል ጋር ትዕግሥት በሐሳቡ መጣችበት ። ምን ይሰማት ይሆን ?

“ እንግድያው እንሒድና ውጤቱ እስኪደርስ እንጠብቃ ? ” አለ እስክንድር ፣ ዝምታው አላምር ብሎት ወደ አቤል እየተመለከተ ።

ዮናታን እስክንድርን በግል ለማነጋገር ፈልገው ፥ እንዴት ምልክት እንደሚሰጡት ተቸግረው ነበር ። በመጨረሻ አቤልና እስክንድር ሲሔዱ ሲሉ ነገሩት ።

" እስክንድር ፥ ስለ ውጤትህ ለብቻህ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ ።"

እስክንድር ግራ ገባው ። ውጤቱ በእጁ ገብቷል ። እና ምን የሚያስፈልግ ነገር አለ ? ወይስ በእጁ ከገባው ውጤት ውስጥ የሚለወጥ ነገር አለ ?

" ታዲያ መቼ ልምጣ ? " አላቸው በሩን ይዞ ቆሞ ።

" በተመቸህ ጊዜ ። እኔ አሁንም ቢሆን እስከ ስድስት ሰዓት ቢሮዬ ነኝ ። "

ነገሩን ለማወቅ ስለ ተቻኮለ ፥ አቤልን ወደ መኝታ ቤቱ ሸኝቶ ወዲያውኑ ተመለሰ ።

" የፈለግኩህ ስለ አቤል ጉዳይ ላነጋግርህ ነው " ሲሉ ጀመሩ ዮናታን ። " ትምህርቱን ሊቀጥል አይችልም ። ማቋረጥ አለበት ። ውጤቱም ጥሩ አይደለም ። ግን ውጤቱን ሰጥቶ ዩኒቨርስቲዉን እንዲለቅ ማድረግ ለእንደሱ ዐይነት ጎበዝ ተማሪ ሞራሉን ክፉኛ መጉዳት ይሆናል ። በዚያ ሁኔታ ከወጣ፥ ሁለተኛ ፊቱን ወደ ትምህርት ዓለም አይመልስም ።

" አዎ ። እና ትምህርቱን በዘዴ እንዲያቋርጥ ማድረግ ነው። ስለ ደረሰበት ችግር ወይም ስለ ወደቀበት የዐይን ፍቅር በአሁኑ ጊዜ አስፈላጊው ጥናት ተገባድዷል ። ለዚህ ተብሎ የተቀናጀ የበጎ ፈቃደኞች ስብስብ፥ በቅርቡ ጉዳዩን አጥንቶ ጨርሶ ይነግረናል ። በዚህ ጉዳይ አቶ ቢልልኝ በጣም ነው የተባበሩኝ ። ቢልልኝ ፥ ከሳይኮሎጂ ትምህርት ክፍል — ታውቃቸዋለህ ? "

" አዎን ። እኔንም ጠርተው ስለ አቤል የማውቀውን ያህል እንድነግራቸው ጠይቀውኛል ። "

" የእሳቸው ጥረትና ትብብር አጽናንቶኛል ። ምኞቴ ከንቱ ሆኖ አልቀረም ። ምናልባትም ለአቤል ጉዳይ ይህን



ያህል አትኩሮት መስጠቴ የሌሎች ተማሪዎችንም ግላዊ ችግር መፍትሔ የሚያስገኝ ይሆናል ። እንደ አቤል ያልባሰባቸው ሕመምተኞች ውስጥ ውስጡን ካሉ ማለቴ ነው ።"

ዮናታን ንግግራቸውን አቋርጠው፥ መነጽራቸውን ያለ ምክንያት ከጠረጴዛው ላይ አነሡ ። የመነጽሩን ጠርዝ በጣታቸው እየነካኩ ቀጠሉ ።

" እና አሁን ከአንተ የምፈልገው ትብብር በሁለት ነገር ላይ ነው ። "

" እሺ ! "

" አንደኛ ፥ ከግቢም ሆነ ከውጪ ለአቤል በሀገር ልጅነት ወይም በዝምድና ወይም በጓደኝነት የሚቀርበው ሰው ካለ፥ ለሥነ ልቡና - ጥናቱ ስለሚረዳ እንድትጠቁመን ነው ። በዩኒቨርስቲ ውስጥ እንኳ ከእሱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ይኖራቸዋል ተብሎ የተገመተውን ከአንተ ጀምሮ የጥናት ቡድኑ ያነጋገረ ይመስለኛል ። በተለይ ከውጭ የምታውቀው ካለ ይመረጣል ። "

እስክንድር አሰበ ። ግን ወዲያውኑ በሐሳቡ የመጣለት ሰው አልነበረም ።

" ሁለተኛ ፥ የጥናት ቡድኑ ውጤቱን እስኪነግረን ወይም የትምህርት ክፍሉ ለአቤል ችግር መፍትሔ እስኪያገኝለት ድረስ ፥ የመኝታ ክፍል ጓደኛው እንደ መሆንህ መጠን አቤል ራሱን እንዳይጎዳ በማጽናናት እንድትረዳው አደራ ጥለንብሃል ። "

" አቤልን እንዴት ማጽናናት ይቻላል ? ' ሲል አሰበ እስክንድር ።

" ግን ሁለተኛው ነገር ከባድ ነው " አላቸው ፥ ተስፋ ባጣ ድምፅ ።

' ግድ የለም ። ማለቴ ፥ አንተ በሚቻልህ መጠን በቅርቡ ሁን ። ብቻውን አትተወው ። በተረፈ ብቸኛ የማይሆን

በትን የተሻለ ዘዴ እኔ በዚሁ ሰሞን ውስጥ እፈልግለታለሁ ” አሉ፣ አንዳች የተማመኑበት ነገር በልባቸው እንደ ያዙ ሁሉ ኰራ ብለው ።

እስክንድር ትዕዛዛቸውን በደስታ ተቀበለ ። ደስ አለው ። ከዮናታን ተለይቶ ከሔደ በኋላ፣መንገድ ላይ ብቻውን ከሐሳቡ ጋር ይሟሟቅ ነበር ። ያስደሰተው አቤል በሚረዳበት ጥረት እሱም መግባቱ ነው ። ዮናታን በጠየቁት መሠረት ከዩኒቨ ርስቲ ውጭ አቤልን የሚቀርብ ሰው አሰበ ። ዘመዶቹ ብሎ አቤል ያስተዋወቀው አንዳንድ ሰዎች በሐሳቡ መጡበት ። ነገር ግን አቤል ብዙ አይቀርባቸውም ። ያን ያህል አይጠያ የቁም ። እና፣ ታዲያ ምን ያህል ይጠቅማሉ ?

አንዲት ሴት ትዝ አለችው ። ብርቅነሽ ! የአንድ ቀን አዳር ትውውቅ ቢሆንም፣ከአቤል ጋር ከሌሎች የተሻለ ግን ኙነታቸው ለአቤል በሕይወቱ ውስጥ አዲስ ዐይነት ግንኙ ነት ነውና ።



# ምዕራፍ ሀያስድስት

አቤል በዮናታን መኪና የአራት ኪሎን ቁልቁለት ሲወርድ፣ ወዴት እንደሚሔድ በውል አያውቅም ነበር ። የዮናታን በድንገት ከመኝታ ክፍሉ አስጠርተውት ነው የወሰዱት ። “ ዛሬ ከእኔ ጋር ነህ ” ከማለት ሌላ፣ ወዴት እንደሚወስዱት አልነገሩትም ። እሱም አልጠየቃቸውም ። አብዮት አደባባይ ከመድረሳቸው በፊት ከሚገኝ አንድ የመኖሪያ ሕንፃ ጀርባ መኪናቸውን አቁመው የሕንፃውን ደረጃዎች ወጡ ። ሦስተኛው ፎቅ ላይ ሲደርሱ በሩ ላይ “ 16 ” ቁጥር የተጻፈበትን መኖሪያ ቤት ደወል ደወሉ ። አንዲት ፈረንጅ ከውስጥ በሩን ከፍታ ብቅ አለች ።

“ አቤል ማለት እሱ ነው ” አሏት ዮናታን በጀርመንኛ ።

ሞቅ ካለ ፈገግታ ጋር ሰላምታ ሰጠችው ።

“ ባለቤቴ ናት ” አሉት ዮናታን ።

ከትውውቁ በኋላ ወደ ቤት ገብተው ተቀመጡ ። አቤል ዮናታን ወደ መኖሪያ ቤታቸው ለምን እንዳመጡት ሊገባው አልቻለም ። በልቡ ብዙ ነገር እያሰበ በግድግዳዎቹ ላይ የተሰቀሉትን ሥዕሎች አንድ በአንድ በዐይኑ አዳረሳቸው ። ከዮናታን ባለቤት ጋር በዐይን መሟሟቅ ካልሆነ በስተቀር ቃላት መለዋወጥ አልቻሉም ። እንግሊዝኛ ለመግባቢያ ያህል ትችላለች ። ግን ዮናታን ጀርመንኛ ስለሚያውቁ ቤታቸው ውስጥ የሚነጋገሩት በጀርመንኛ ነው ። አንዳንዴም የምታውቃቸውን ጥቂት የአማርኛ ቃላት በመጠቀም እንግዶቻቸውን እያሟቀች ታዝናናለች ።

"ይኸውልህ እዚህ ፎቅ ላይ ተሰቅለን ነው የምንኖረው" በማለት ዮናታን ፣ ከአቤል ጋር ጨዋታ ከፈቱ ።

አቤል ፈገግ አለ ።

" አንተ ወደፊት ምን ዐይነት ቤት ውስጥ መኖር ነው የምትመርጠው ? " ሲሉ ጠየቁት ።

' ምን ዐይነት ጥያቄ ነው ? ' አለ በልቡ ፣ ' አሁን ባለው የቤት ችግር ሁኔታ አንገት ማስገቢያ ይገኝ እንጂ ፣ የቤት ምርጫ ይጠየቃል እንዴ ? ' ዮናታን ግን እሱን ለማጫወት ሲሉ አፋቸው ላይ የመጣላቸው አርዕስት ሆኖ ነው እንጂ የሚኖሩበትን ሀገር እውነታ አጥተውት አልነበረም ።

" በአሁኑ ጊዜ አንገት ማስገቢያ ከተገኘ ምን ምርጫ አለ ? " አላቸው እየተቅለሰለሰ ።

የመመረቂያው ዓመት ላይ ቢሆንም ፣ ከዩኒቨርስቲዉ ሲወጣ ስለሚገባበት ቤት አስቦ አያውቅም ። ከቤት ጋር የትዳርም ሐሳብ ይኖራል ። ያንንም ቢሆን አስቦ አያውቅም ። በእርግጥም ስለ ቤት ማሰብ የሚችለው የሥራውን ምድብ ቦታ ካወቀ በኋላ ነበር ።

" አይዞህ ፣ የጊዜ ጉዳይ ነው " አሉ ዮናታን ፣ " አሁን ካለንበት ችግር ወጥተን የምርጫችንን የምናገኝበት ጊዜ ይመጣል ። ምን አጣን ብለህ ነው ? ለም ለመሬት አለን ፣ ሀገራችንን ዐልፈው ውጭ የሚፈሱ ወንዞች አሉን ! ተፋቅረንና ተባብረን ጠንክረን ከሠራን ብሩህ ተስፋ ይጠብቀናል ። "

ባለቤታቸው ሻይ ይዛ መጣች ። እሷም ቀስ እያለች ከአቤል ጋር በእንግሊዝኛ መጨዋወት ጀመረች ። ስለ አቤል ብዙ ነገር ታውቃለችና ፣ ሁኔታውን ሁሉ ከመጀመሪያው እስካሁን ባሏ ያጫውቷት ስለ ነበር፣ ለአቤል ደግና አመለካከት አላት ። ሁሉም ለጊዜው ዝም ዝም ቢሉም ፣ እንግድነቱን ለማስታመም ካልሆነ በስተቀር ዝምታው ካለመተዋወቅ የመነጨ አልነበረም ።



አንዳንድ ማኅበራዊ መግባቢያዎችንና ጨዋታዎችን እየተለዋወጡ ሻዩ ተጠጥቶ ስኒዎቹ ተነሡ ።

ከዚያ ዮናታን የቤቱን ክፍሎች ለአቤል ማስጎብኘት ጀመሩ ። ይህ ተግባራቸው ዓላማ ነበረው ። በመጀመሪያ መኝታ ቤቱን ፣ ወጥ ቤቱንና መታጠቢያ ቤቱን አሳዩት ። በመጨረሻም ወደ አንዲት አነስተኛ ክፍል ወሰዱት ። በክፍሏ ውስጥ ብዙ ዕቃ አልነበረም ። አንድ አልጋ እና አነስተኛ ጠረጴዛ ከነወንበሩ ብቻ ይታይበታል ።

" ይህ ደግሞ የአንተ መኝታ ክፍል ነው " አሉት ፍርጥም ብለው ።

አቤል ግር አለው ። ድንጋጤ ይሁን ደስታ ፣ የተሰማውን ለማወቅ አልቻለም ።

" ያሉት አልገባኝም " አላቸው ።

" ይህ ለአንተ ያዘጋጀሁት መኝታ ክፍል ነው ። ለተወሰነ ጊዜ ከእኔ ጋር እንድትኖር ወስኜአለሁ ። ማንኛውም ነገር እዚሁ ሊሟላልህ ይችላል " አሉት ፣ በጥያቄ ሳይሆን በውሳኔ ድምፅ ።

ዮናታን አቤልን እቤታቸው አስቀምጠው ጉዳዩን ለማራመድ የወሰኑት ሰሞኑን ከባለቤታቸውና ከቢልልኝ ጋር ተመካክረው ነበር ። በአንድ በኩል የአካባቢ ለውጥ ለአቤል ጤና ይረዳዋል ብለው ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ፣ አቤል በዚህ ዓመት ትምህርቱን ስለማይቀጥል፣ አጠገባቸው አድርገው ሞራሉን በመጠበቅ ለማበረታታት እንዲመቻቸው ነው ። ዮናታን ከሚስታቸው ጋር ሆነው ይህን የወሰኑት ስለ አቤል የተደረገው የሥነ-ልቡና ጥናት ጥሩ ደረጃ ላይ መድረሱን ካረጋገጡ በኋላ ፣ የመንፈስ ደስታ አግኝተው ነው ። በአቤል ጉብዝና ባላቸው የጠነከረ እምነት በቅን ልባቸው የጀመሩት ጉዳይ ከዚህ ደረጃ ላይ መድረሱ አስደስቷቸው በበለጠ እንዲቀጥሉበት ገፋፍቷቸዋል ።

ዮናታን አቤልን ወደ ቤታቸው ከማምጣታቸው በፊት ይህን ውሳኔአቸውን ያልነገሩት ሆን ብለው ነው ። ውጭ ቢነግሩት በነገሩ ያመነታ ይሆናል ። ቤት ውስጥ ገብቶ የተ

ዘጋጀለትን ክፍል ካየ በኋላ ግን አንድም ሊወደው ይችላል ፤ ያም ካልሆነ ድካማቸውንና የሰጡትን ክብር በማገናዘብ በእሺታ ይቀበለዋል የሚል ግምት ነበራቸው ። እንዳሰቡትም አቤል ክፍሉን ከተመለከተ በኋላ፣የእምቢታ ስሜት አላየለበትም ። ነገር ግን አፉን ሞልቶ “ እሺ ይሁን ” ማለትም አልቻለም ። የተዘበራረቀ ስሜት ሰፈረበት ። ብቸኝነቱን ይወዳል ። እናም ብቸኝነቱን ሊያስታምምበት የሚችለውን ይህን ክፍል ወድዶታል። ግን ደግሞ፣ የዩኒቨርስቲውን ግቢ መልቀቅ ? ከትዕግሥት ዐይን መራቅ ?

“ እንዴት ነው ? ጥሩ ክፍል ነች ? ” አሉት ዮናታን ፣ በላዩ ላይ የሚያንዣብበውን የማመንታት ጥላ በሚገፍ ድምፅ ።

“ ጥሩ ነው ” ሲል ራሱን ነቀነቀ ።

“ የመጻሕፍት ክፍል ከእኔ ጋር በጋራ መጠቀም እንችላለን ” ብለው ፣ ወደ ጥናት ክፍላቸው ወሰዱት ።

መደርደሪያዎቹ በመጽሐፍ ጥቅጥቅ ያሉበት ክፍል ነበር ። መለስተኛ ‘ላይብራሪ !’ የቀለም ትምህርት ፣ የፍልስፍና የምርምር እና ልብ ወለድ መጽሐፎች ፣ እንዲሁም ወርኃዊ መጽሔቶች በመልክ በመልካቸው ተደርድረዋል ። አቤል ስሜቱ ለመንቃት ሲንጠራራ ተሰማው ። ባለ ሦስት ጥራዝ የማርክስ “ ካፒታል ” ከመጽሐፎቹ ሁሉ ጎልቶ ዐይኑን ሳበው ።

“ ይኸው ነው እንግዲህ ፣ ወደ ማታ ዕቃህን ከካምፓስ ማምጣት እንችላለን ” አሉትና ተመልሰው ወደ ሳሎኑ አመሩ ። አቤልም እግሩን በሐሳብ እየጎተተ ተከተላቸው ።

ሻንጣውን ለማምጣት ከዮናታን ጋር ወደ ዩኒቨርስቲዉ ሲሄድ፣ መንገድ ላይ ልቡ ማመንታቱ አልቀረም ። ዩኒቨርስቲዉን ለቅቆ የመውጣቱን ነገር ልቡ ባይቀበለውም ሁኔታውን ሲያመዛዝን፣ዮናታን እሱን ለመርዳት ያደረጉለት ጥረት ከብዶ ታየው ። እናም በባዶ ግትር እምነት ገደል አፋፍ ላይ የቆመች ሕይወቱ በሰው እጅ ጥበቃ ሥር እየዋለች መሔዷ ታወቀው ። የጥገኝነት ስሜት ተሰማው ። ጥገኝነትን አይወድም ነበር ። ከድህነቱ ጋር ሞቶ መቀበር ከልጅነቱ ጀምሮ



ያደረበት ጸባይ ነው ። ግላዊ ነጻነቱን ይሻል ፤ ግን የሌላውን ርዳታ ሳይሻ፣ብቸኛ እና ነጻ ሕይወት የኖረ ሰው በዚህ ዓለም ላይ ማን አለ ?

ከመኝታ ቤቱ ገብቶ ሻንጣውን ሲያወጣ፣ አቤል ሆዱን ባር ባር አለው ። በዚህ መኝታ ክፍል ውስጥ የሆዱን አውጥቶ ለጓደኞቹ በደንብ ያጫወተበት ቀን ወይም በጋራ ያሳለፋቸው ታላላቅ ትውስቶች የሉም ። ነገር ግን ባዶ ትንፋሽም ቢሆን ከለመዱት ሲለዩ ያባባል ። ከርሱ ይበልጥ ሆዱ የባባው እስክንድር ነበር ። ሆኖም የዮናታን ጥረት ለአቤል መልካም ሕይወት ስለሆነ፣ ፊቱ ላይ ምንም ዐይነት ቅሬታ እንዳይታይ ከውስጥ እየታገለ የአቤልን ዕቃዎች አዘገጃጀለት ።

“ ወዴት ሊሔድ ነው ? ” አለ ድብርት ፣ ሁኔታውን አይቶ የመለያየት አዝማሚያ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ።

“ወደ ውጭ ! ከካምፓስ ውጭ ” አለው አቤል ራሱ ፣ ጉሮሮው ላይ አንዳች ነገር እየታገለው ።

“ ምነው ? ” አለና ድብርት ፣ ምናልባት ወድቆ ይሆናል የሚል ሐሳብ ጭንቅላቱን ስለ መታው ፣ ሊጠይቀው ያሰበውን ከምላሱ መለሰው ።

እስክንድር የድብርት ፊት በኀዘን ሲለዋወጥ ተመልክቶ ፣ ‘ ምንም ቢሆን ፣ በአፉ ባይናገርም ፣ ሰው ለሰው ማዘኑ አይቀርም ለካ ! ’ አለ በልቡ ፣ ‘ ግን እንኳንስ በዓመት በሚቆጠር ጊዜ ቀርቶ ለአንዲት ደቂቃም ቢሆን አብረው በኖሩበት ጊዜ ውስጥ፣ በሙሉ ልብ ካልተጨዋወቱና ሐሳብ ለሐሳብ ካልተካፈሉ ፣ ሲለያዩ ማዘኑ ምን ይጠቅማል ? ኀዘኑ እንዲያው ለጊዜው ፣ ከዐይን እስኪርቁ ካልሆነ በስተቀር በልብ ውስጥ ምን ትዝታ ይቀራል ? ’

“ ውጭ ድረስ እንሸኝዋ ” ብሎ ድብርት ቀድሞ ሻንጣውን ሊሸከምለት ያዘ ።

“ ተወው እኔ እይዝለታለሁ ” አለው እስክንድር ። ድብርት እሺ አላለም ። ሻንጣውን ይዞ ቀደመ ።

" ሳምሶንስ የት ሔደ ? " አለ አቤል ፥ ሻንጣውን መኝታው አጠገብ በማየቱ ገና ግቢውን ለቅቆ እንዳልወጣ በመገመት ።

"እኔ እንጃ ፥ ጠዋት ነው የወጣው ። እኔንም ዘግቶኛል ። ይህን ሁለት ቀን ፈገግ ብሎ አነጋግሮኝም አያውቅ " አለው እስክንድር ፥ በልቡ እያዘነም ፥ እየበሸቀም ።

" ምነው ? ለምን ? " አለ አቤል ፥ ግር ብሎት ።

" እኔ ምን ዐውቄ ? "

" አትፍረድበት ፥ ስለ ወደቀ ተናዶ ይሆናል " አለው አቤል ፥ አዝኖ ። እሱን አግኝቶት ቢሰናበተው በወደደ ነበር ፤ ምክንያቱም ሳምሶን የእሱን ጥቃት እንደማይወድና ለእሱ የተለየ ክብር እንዳለው ያውቃል ። ለማንኛውም ለጊዜው አልተገናኙም ።

ሻንጣው ዮናታን መኪና ላይ ሲጫን በአካባቢው የነበሩ ተማሪዎች ከንፈራቸውን እየመጠጡ ዐለፉ ። ምክንያቱን ባያውቁም ፥ ያው ወድቆ ነው በሚል ግምት ነበር ።

እስክንድር አብሮት ሊሔድ መኪናው ውስጥ ገባ ። አቤል በሩን ተደግፎ ቆሞ ለጥቂት ሴኮንዶች ተከዘ ።

ሕይወቱን ከዚህ ግቢ ጋር የተያያዘች አድርጎ ገመተ። ግቢውን መልቀቅ ፈራ ። ልቡ ደግሞ ሊያመነታ ታገለው ። በመኪናው መስታወት ሰርቆ ዮናታንን ተመለከታቸው ። እኚህ ትሁት ፥ ትልቅ ሰው የእሱን ወደ መኪና ውስጥ መግባት በመጠባበቅ ላይ ናቸው ። " ሁሉ ነገር አልቋል " የሚል ስሜት በፊታቸው ላይ ይነበባል ። ምሁራዊ ውበት የሚባል ነገር ካለ ከእሳቸው ገጽታ ላይ ይገኛል ።

' በል እንጂ አቤል ፥ የምን ማመንታት ነው ? ' አለው የገዛ ኅሊናው ። አከላቱ ግን ቶሎ አልተንቃነቁም ። ዐይኑ የሚመለከተው ትዕግሥት ወዳለችበት ወደ ሴቶች መኝታ ሕንፃ ነበር ። አቤል ግቢውን ሲለቅ ትዕግሥት ወጥታ አታየውም? ሰርቃ የምታየውን አጭር ልጅ ለማየት ጓጓ ። ሲሆን ብቅ ብላ ከሩቁ ሰርቃ አይታው ለስንብት ያህል በመሐረብ



ዐይኗን ስታሻሽ ቢመለከት ፥ ካለዚያም ለመጨረሻ ጊዜ ፈገግ ብላለት፥ ያንን የሚሰረጎድ ጉንጯን ቢያይ ፥ ምንኛ መታደል ነበር! " የፍቅር አምላክ ወይም ' ሳይኪክ ፓወር ' ካለ ፥ ትዕግሥትን አሁኑኑ ጎትቶ ያውጣና ያሳየኝ ! " አለ አቤል በልቡ ።

" እህሳ አቤል ፥ አንንቀሳቀስም ? " አሉት ዮናታን ፥ ስሜቱን እንዳይረብሹት በማሰብ ረጋ ብለው ።

" እሺ ፥ እሺ " ብሎ ወደ መኪናው ውስጥ ገባ ።

መኪናዋ ዞራ ስትሔድ ድብርት በስንብት ዐይነት እጇን አውለበለበለት ። አቤልም አጠፋውን መለሰ ።

" አቤል ከእኔ ጋር መሆኑ ጥሩ አይደለም ? " ሲሉ ፥ ዮናታን ጉዞ ከጀመሩ በኋላ፥ እስክንድርን ጠየቁት ።

" ግሩም እንጂ ! " አለ እስክንድር ፥ ፈገግ ብሎ ።

" እንግዲህ አንተም ብቻውን እንዳይሆን እየመጣህ አጫውተው ። "

እስክንድር እንደ ገና ፈገግ ብሎ በእሺታ ራሱን ነቀነቀ።

" ማንኛውም ነገር በቅርቡ ውጤት እንደሚያገኝ እርግጠኛ ነኝ " አሉ ዮናታን ፥ አንዴ ወደ መንገዳቸው አንዴ ወደ አቤል እያዩ ።

አቤል ከመቅለስለስ ሌላ ምንም አልመለሰም ።

" አንጠራጠርም ! " አለ እስክንድር ፥ ከውስጡ አንዳች ስሜት ፈንቅሎት ።

ከዮናታን መኖሪያ ቤት ሲደርሱ፥ ዕቃውን ተረዳድተው አስገቡት ። ሚስትየዋም እንደ ቀድሞው ወርቅ በሆነ ፈገግታ ተቀበለቻቸው ። ምን ጊዜም ከፊቷ ላይ ፈገግታ አይጠፋም ።

" ሊብሊንግ ፥ ይኸው ተመልሰን መጣን " አሏት ዮናታን ፥ የሚስታቸውን ትብብር በሚጠይቅ ስሜት ሻንጣውን እያስረከቧት ።

" እንኳን ደኅና መጣችሁ " ካለች በኋላ ፥ ወደ እስክንድር ፊቷን መልሳ ፥ " ጓደኛው ነህ ? " ስትል በእንግሊዝኛ ጠየቀችው ።

እስክንድር በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ ።

" እንግዲህ ጓደኛህን ነጥቄሃለሁ ። ማንኛውንም ጥንቃቄ የምወስድለት እኔ ነኝ " አለች ፍርጥም ብላ ።

እንግሊዝኛዋ ቢሰባበርም ለመረዳት ከባድ አልነበረም ።

" ፈቅጃለሁ ! " አለ እስክንድርም ፥ ፈገግታዋ ለመልስ ጋብዞት ።

ሳሎኑ ውስጥ ከተቀመጡ በኋላ ፥ ሴትዮዋ ወዲያ ወዲህ ስትንጎራደድ የእስክንድርም ዐይን አብሮአት ይዋልል ነበር ። ' በጣም ፈጣን ናት ፤ ልማድ ሆኖባት ነው መሰል ' የሚያስቸኩል ነገር ባይኖርም ትቸኩላለች። እጅዋ የቆሸሸ ፀር ነው። ቆማ ስትጫወትም ፥ ወዲያ ወዲህ ስትወዛወዝም ፥ እጆቿ ከጠረጴዛው ወይም ከጣውላው ላይ አንዳች እንከን ይፈልጋሉ ። የሳሎን ዕቃዎቹ አቀማመጥና አደራደር የወይዘሮይቱን እጅ ያስመሰግናሉ ። አንዳችም ነገር ተዝረክርኮ አይታይም ። ሌላዎቹ ውጤቶቿ ደግሞ በግድግዳው ላይ ዐልፎ ዐልፎ የተንጠለጠሉት የሚያምሩ የእጅ ሥራዎቿ ነበሩ ። የሳሎኑን ማዕዘኖች በአበባ ተክል ሞልታቸዋለች ። ቅልጥፍና እና ጥንቃቄ ገጽታዋ ላይ ይነበባሉ ።

" ሻይ ወይስ ቡና ? " ብላ ስትጠይቃቸው ፥ ክንዷን አቤል ትከሻ ላይ አሳርፋ ነበር ።

አቤል አልደነገጠም ። የምትከብድ ፍጥረት ስላልሆነች አልከበደችውም ። ትከሻው ላይ ያረፈው እጅዋ ወንድነቱን የሚፈታተን ዐይነት የተቃራኒው ጾታ እጅ ሆኖ አልተሰማውም ። የእኅትን ጣዕም ስለማያውቅ፥ የእናት እጅ ያረፈበት ነው የመሰለው ። ግትር መንፈሱ፥ የዚችን ሴት ግልጽ ልብ በፍጥነት መረዳቱ ወይም መቀበሉ ለራሱም አስገረመው ።



ለጥያቄዋ መልስ በመጠበቅ ዐይነት ሞስቴንም ተመለከተችው ። ዐይኖቿ አንድ ቦታ አይረጉም ። በነጭ ቆዳዋ ላይ ሰማያዊ መሳይ ሥራሥሮቿ ዐልፎ ዐልፎ ይታያሉ ። ገጽታዋ ላይ ፍቅርና ትሕትና ይነበባል ።

ዮናታንና እስክንድር ቡና ሲመርጡ፥ አቤል ሻይ አለ ።

ሚስታቸው ወደ ጓዳ ከመሔዷ በፊት ዮናታን ክንዷን ይዘው እጅዋ ላይ ሳም አደረጓት ። ለመልካም መስተንግዶዋ ምስጋናቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነበር ።

እስክንድር ዐይኑን ማመን አቃተው ። ወይም ያየው ነገር ሕልም መሰለው ። እውነት ፍቅር ይሆን ? አለ በልቡ ። የትዳር ዕድሜአቸውን ለማወቅ ጓጓ ። እፍላ ፍቅረኞች ካልሆኑ በስተቀር ተጋብተው በቆዩ ሰዎች መሐል አይቶ የማያውቀውን ሁኔታ ማየቱ ነው ያስደነቀው ። ያውም በእንግዳ ፊት !

" ሊብሊንግ ሚስቴም እናቴም ናት ። የሕይወት ጣዕም የሚታወቀኝ እሷን አጠገቤ ሳገኛት ነው " አሉ ዮናታን ፥ ሚስታቸው ወደ ጓዳ ከገባች በኋላ ። " ሰውን ማስደሰት መቻል ቀላል ነገር አይደለም ። ሊብሊንግ ይህን ችሎታ በተፈጥሮዋ ታድላዋለች ። ሁል ጊዜ ደስተኛ ነች ። እንደሚገባኝ ፥ ደስታዋን የምታገኘው ሰዎችን በማስደሰት ነው ። አቤል ሁኔታዎች እስኪመቻቹለት ከእኛ ጋር እንዲኖር ሐሳቡን ቀድማ ያቀረበችልኝ እሷ ናት ።

አቤል በጥያቄ መልክ ዐይኑን አቁለጨለጨ ።

' ከአሁን በፊት የት ታውቀኛለች ? ' ብሎ ነበር ራሱን የጠየቀው ። ማንኛውም ነገር በዮናታን ሊደርሳት እንደሚችል ወዲያው ገመተ ። ወደዚህ ቤት የመምጣቱ ሐሳብ ከእሷ መመንጨቱን ሲሰማ፥ በልቡ ውስጥ ለሴትዮዋ ልዩ ስሜት ተፈጠረበት ።

" ከተጋባችሁ ? " ሲል እስክንድር ፈራ ተባ በሚል ድምፅ ጠየቀ ።

" አ ! ስድስት ዓመት ያህል ሆኖአል ። በርሊን በነበር ኩበት ጊዜ፣አንዴ ታምሜ ተኝቼ ሐኪም ቤት ውስጥ አስታማ ሚዬ ሆና ነው ያገኘኋት ። "

ዮናታን ይህን ሲናገሩ ድምፃቸው የተለየ ቃና ነበረው ። የፍቅረኞች የመጀመሪያ ትውውቅ በልባቸው ታላቅ ትውስት ጥሎ ያልፋል ። ዮናታንም ለእስክንድር በሰጡት መልስ ሳቢያ ከስድስት ዓመት በፊት የተፈጸመ ትውስት ውስጥ ገቡ.....

ዮናታን በምሥራቅ ጀርመን ውስጥ በሚገኘው ትልቅ ዩኒቨርስቲ የድኅረ ምረቃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ፣ ለተወሰኑ ዓመታት በሁምቦልት ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና መምህር ሆነው አገልግለው ነበር ። እዚያ ሳሉ አንድ ጊዜ የሆድ ውስጥ ሕመም ያድርባቸውና በርሊን ቤክ እሚባለው ሆስፒታል ይገባሉ ።

በርሌን ቤክ ከመሃል ከተማው ሀያ ኪሎ ሜትር ያህል ይርቃል ። ውስጡ በአምስት ግቢዎች ተከፍሎ ፣ በጠቅላላ ዐሥር ሺህ አልጋዎች ያሉት ሰፊ ሆስፒታል ነው ። ዮናታን የተኙት ፣ "ታይል አይንስ" በሚባለው ግቢ ፣ " እስታስዩን አይን ሁንደርት ሲ " ክፍል ውስጥ ነበር ።

በማገገም ላይ እንዳሉ፣ አንዲት ነርስ ሲያዩ ልባቸው ይደነግጣል ። ይህች ነርስ ፊቷ ላይ ፈገግታ የተሳለ እንጂ እንደ ሌላው ሰው አንዳንድ ጊዜ ብቻ የምትሥቅ አትመስልም ። ሕሙማንን ለመንብኘት ስትገባ በሕመም የደከመ ስሜታቸውን በፈገግታዋ ታነቃቃዋለች ። በውስጥ ቁስል የዳመነ ፊታቸውን ፈገግታዋ ብርሃን ሆኖ ያፈካዋል ። መስተንግዶዋ ፍቅር የሞላበት በመሆኑ፣በክፍሏ ሕሙማን ዘንድ ተወዳጅ ነበረች ። ወደ በሽተኞቹ ክፍል ለመግባት የጉብኝት ወይም የመድኃኒት ዕደላ ሰዓት እስኪደርስ ፣ ወይም እነሱ በደወል እስኪጠሩዋት አትጠብቅም ። ብቅ ጥልቅ እንዳለች ነው የምትውለው ። ልማድ ሆኖባት ሁሌ ትቸኩላለች ። እናም አንድ ቦታ ቆማ አትቆይም ።

ዮናታን ልባቸው ከደነገጠላት ጊዜ ጀምሮ ይህን ችኮላዋን አልወደዱላትም ። ክፍላቸው ገብታ ስትወጣ ፀሐይ ብልጭ ብላ ድርግም ያለች ያህል ስሜታቸው ይከፋ ጀመር ።



ሥራዋን ጨርሳ ወደ ቤትዋ ልትሔድ በሽተኞቹን ስትሰናበታቸው፣ የዮናታን ልብ ይረበሽ ነበር ። ሌሊት አልመዋት አድረው ጠዋት ዐይኗን የሚያዩበትን ጊዜ መናፈቅ ሲጀምሩ ፣ ልባቸው ፍቅር ፍለጋ ዳዴ እያለ መሆኑን ገመቱ ። ሞኒካ የሚለው ስም አሁንም አሁንም ጆሮአቸው ውስጥ ይደውል ጀመር ።

አንድ ቀን ከሥራ በኋላ እንደ ልማዷ ልትሰናበታቸው ወደ ክፍላቸው ስትገባ፣ ዮናታን እጅዋን ያዝ አድርገው ቅሬታቸውን ተነፈሱላት ።

" ቆይ እንጂ አትቸኩዪ ። ትንሽ አጫውችኝ ። ሁሌ መቸኮል ምንድነው ? " አሏት ።

ሞኒካ ፈገግ ብላ ፍቃዳቸውን ለመፈጸም አልጋቸው አጠገብ ትንሽ ቆመች ።

" እውነት ለምንድነው እንዲህ የምትቸኩዬው " ሲሉ ጠየቋት ።

" ልማድ ሆኖብኝ ነው ። በምሠራበት ጊዜ ፍጥነቴ አይታወቀኝም " አለችና ፣ ትንሽ አስብ አድርጋ ፣ " በዚህ በአራት ዓመት ውስጥ ያፈራሁት ጸባይ ነው " አለቻቸው ።

" ግን ምነው ፣ ለምን ? " አሏት ።

"ለአፍላ ፍቅሬ ያገኘሁት ማካካሻ ፣ ራሴን ከወዲያ ወዲህ በማራወጥ ዕረፍት መንሣት ነበር " አለቻቸው ፣ ስሜቷን ግልጽ አድርጋ ።

ከዚህ ንግግሯ ጋር ፊቷ ፍም ሲመስል ተመለከቱት ። ስሜቷ መጨፍገጉን ከገጽታዋ ላይ አጠኑ ። ሰው ሠራሽ የሚመስሉት ዐይኖችዋ፣በቅርቧ ያለውን ነገር ለማየት የተከለ ከሉ ይመስል በመስኮቱ ማዶ ከሚታየው ባዶ ሰማይ ላይ ዐረፉ ።

" ነገሩ እንዲህ ነው " ስትል ቀጠለች ። " ከአራት ዓመት በፊት አፈቅረው የነበረው ወጣት የመጀመሪያዬ

ነበር ። በመሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ሙሉ ልቤንና ፍቅሬን ሰጥቼው ነበር ለማለት እደፍራለሁ ። ነገር ግን ሁለት ዓመት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ ጥሎኝ ጠፋ ” አለችና ዝም !

“ የት ነው የጠፋው ? ” አሏት ዮናታን ፥ ተመስጠው ።

“ ወደ ምዕራብ ጀርመን። እኔ የሰማሁት ጠፍቶ ከሔደ በኋላ ነው እንጂ ምንም ያማከረኝ ነገር አልነበረም ። በእርግጥ ልቡ መሸፈቱን በአንዳንድ ንግግሮቹ ገምቼ ነበር ። አብዛኛውን ጊዜ በአስተሳሰብ እንጋጫለን ። እኔ በፋሽስቶች ላይ ከፍተኛ ጥላቻ አለኝ ። ፀሂትለር ዘመን በናዚዎች ታስሮ የማቀቀው አባቴ ቆስሎ በእኔም ላይ ከባድ ተጽዕኖ ነበረው ። ፍቅረኛዬ ግን ያለፈው ትውልድ በፋሺዝም ምን ያህል እንደ ተሠቃየ ለማጤን ደንታ አልነበረውም ። በአፍላ ስሜት ግፊት እንደሚንቀሳቀስ እገምት ነበር ። እናም መጨረሻውን እንደዚያ አደረገው ። ”

ዮናታን በኀዘን ከንፈራቸውን መጠጡ ።

“ አያሳዝነኝም ። ልቤን አሳዝኖት ነው የሔደው ” አለች ሞኒካ ፥ ራሷን እየነቀነቀች “ ነገር ግን እሱን ብጠላውም ልቤ ውስጥ የተተከለውን ፍቅር በቀላሉ መንቀል አልቻልኩም ነበር።ስለዚህ ራሴን በሥራ በማቆከብ ልረሳው ሞከርኩ ። በሚረባውም ፥ በማይረባውም ነገር ነበር ራሴን የማደክመው ። በማያስፈልግበት ቦታ እፈጥን ነበር ። እየቆየ ሲሔድ ይህ ልማድ እውስጤ ሥር እየሰደደ መጣ ። አሁን ያለ ሥራ ለአጭር ጊዜም ቢሆን መቀመጥ አልችልም ። መንፈሴም የሚረካው ፈጠን ፈጠን እያልኩ ከሠራሁ ነው ” አለቻቸውና ፥ ደመናውን ከፊቷ አባርራ ፈገግ አለች ።

ታሪኳ ዮናታንን አጥንታቸውን ሰርስሮ ገብቶ ወደ ፍቅር መዳህ የጀመረ ልባቸውን አደፋፈረው ። ነገር ግን፥ በአፍላነቱ የተጐዳውን የሞኒካን ልብ ለማዳን መቻላቸውን እርግጠኛ አልነበሩም ። ዕድሜአቸውን ለማመዛዘን ሞከሩ ። በዐሥር ዓመት ያህል ይበልጧታል ። ይህ ሁሉ የአእምሮ ማመንታት ነው እንጂ ፥ ፍቅሩ ያለ ምንም ፍርሀት በልባቸው ውስጥ እያደገ መጥቷል ።



ሞኒካም ዮናታን ታሪኳን በተመስጦና በትካዜ ካዳመጡዋት ጊዜ ጀምሮ፥ስሜታቸውን በማጤን ልቧ ውስጥ ለየት ያለ አዲስ ስሜት ሲያብብ ተሰማት ፥ እና የእሷም ልብ እንደ እሳቸው ልብ ወደ ፍቅር በመዳህ ላይ ሳለ መንገድ ላይ ተገናኙ ።

የዘመን መለወጫ በዓል ሲከበር፥ዮናታን እዚያው ሐኪም ቤት ውስጥ ስለ ነበሩ፥ ሞኒካ ለሌሎቹ ሕሙማን የሥዕል ካርድ ስትሰጥ፥ለእሳቸው ግን በነርስ ልብሷ ሥራዋ ላይ የተነሣችውን ፎቶ ሰጠቻቸው ። ምስሏን ስመው ተቀበሏት ። ከዚያች ደቂቃ ጀምሮ እንደ ሌላው ሕመምተኛ ሲስተር ሞኒካ ሊሏት አልፈለጉም ። ለመጀመሪያ ጊዜ “ ሊብሊንግ ” ብለው ጠሯት ። (በእንግሊዝኛ “ ዳርሊንግ ” የሚለውን ትርጉም የሚሰጥ ጀርመንኛ ቃል ነው ። ) ይህን የፍቅር መጠሪያ የሁልጊዜ ስሟ አደረጉት ።

ዮናታን ከሆስፒታሉ ከወጡ በኋላ፥ ከሞኒካ ጋር በቅርብ መገናኘት ቀጠሉ ። አንድ ዓመት ያህል ሲተዋወቁና ሲቀራረቡ ከቆዩ በኋላ ተጋቡ ። በመጨረሻም ዮናታን ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ሞኒካ አብራቸው አዲስ አበባ ገባች ።

“ ልጆች የሏችሁም እንዴ ? ” ሲል ፥ እስክንድር በድንገት ከቀን ሕልማቸው አባነናቸው ።

ጥያቄው በዮናታን ፊት ላይ የኀዘን ደመና ጣለባቸው ። እስክንድርም ይህን እንዳጤነ ምላሱን ረገመ ። የአፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም ነው ነገሩ ። ቤቱ ውስጥ አንድም ልጅ ወይም የልጅ ዕቃ ካለማየቱ ጋር ሁኔታውን ሳያመዛዝን አፉ ላይ የመጣለትን ነበር የጠየቀው ። የዮናታንን መተከዝ ተመልክቶ አቤልም በጥያቄው ተሸማቀቀ ።

“ ልጆች አልወለድንም ። እንግዲህ መካን መሆናችን ነው መሰለኝ ” አሉ ዮናታን በተከፋ ድምፅ ።

“ ምንም አይደለም ” አለ እስክንድር ፥ ዮናታንን ከጨመራቸው ትካዜ ውስጥ ለማውጣት ምርጥ ቃላት ያገኘ ይመስል ።

“ ምንምስ ነው ፣ ትዳር የሚጣፍጠው ልጆች ሲኖሩበት ነው ። ግን ሳይሆን ሲቀር ፥ ችግሩን ለሳይንስ ዕድገት ከመተው በስተቀር ምን እናደርገዋለን ? ”

አቤልና እስክንድር የመካንነት ነገር ሲነሣ ትዝ ያለቻቸው ብርቅነሽ ነበረች ። መካንነት ከትዳሯ አፈናቅሎ ፥ ከትውልድ መንደሯ አባርሮ ለሴትኛ አዳሪነት የዳረጋት ብርቅነሽ ። በዚያን ዕለት ምሽት ያጫወተቻቸው ሁሉ ታወሳቸው ።

መካን የሚሆነው ወንዱ ወይም ሴቷ ከሁለት አንዳቸው ናቸው ። እና ሐቀኛ ፍቅር ካለ ፥ ሴቷ ከሌላ ወንድ እንድትፀንስ ወይም ወንዱ ከሌላ ሴት ወልዶ እንዲያመጣ ለምን አይደረግም ? መተሳሰብና መተማመን በመሐከላቸው ካለ ለጋራ ጥቅማቸው ከሌላ ጋር የሚደረግ የአጭር ጊዜ — ከደቂቃዎች የማይበልጥ ጊዜ የወሲብ ግንኙነት ምን ይጎዳቸዋል ?

አቤል ይህን ሲያስብ በስሜቱ ውስጥ ቅናት አፍጥጦበት ከፊቱ ቆሞ ተመለከተው ።

‘እስኪ በናትህ ፥ እንደገና አስብ አቤል ። ለአንዲት ሴኮንድም ቢሆን ፥ የሚወዳት ሚስቱን ለሌላ ወንድ አሳልፎ የሚሰጥ ፥ ‘ የሠለጠነ ’ ወንድ ማነው እሱ ? ወይም ደግሞ ልጅ ለማግኘት ብላ ባሏን ለአንዲት ደቂቃም ቢሆን ለሌላ ሴት የምትለቅ ፥ ‘ ትሑት ’ ሚስት ማን ናት እሷ ? አሁን ለምሳሌ አንተ ትዕግሥትን ፥— ሆሆይ ! የአንዲት ሴኮንድ ግንኙነት አብባ ’ኮ ነው ታላቅ ፍቅር የምትሆነው ። ካልቀኑ ፍቅር የለም ! ’

‘እሺ ግንኙነቱ በድብቅ ቢደረግስ ? እና ፥ የሰው ጠላቱ የገዛ ዐይኑ ነው ማለት ነው ? ’

ሞኒካ ያፈላችውን ሻይና ቡና ይዛ በፈጣን ርምጃዋ ስትገባ ልብ የሚማርከው ፈገግታዋ ሐሳቡን ባይጠልፈው ኖሮ ፥ አቤል የጀመረው የሕይወት እንቆቅልሽ መቆሚያ ባጣ ነበር ።

እስክንድር ሲገባ የጀመረውን በባልና ሚስቱ ላይ ያለውን አድናቆታዊ አመለካከት ቡና በሚጠጡበት ጊዜም



አልተወም ነበር ። በተለይም ደግሞ ፥ ልጅ ሳይወልዱ ይህን ያህል ጊዜ ቆይተው የፍቅራቸው ሙቀት አለመቀነሱ አስገረመው ። ፊታቸው ላይ አንዳች ትርጉም ያለው ነገር ያገኘ ይመስል ፥ አንዴ ወደ እሷ አንዴ ወደ ዮናታን እየተመለከተ አነጻጸራቸው ። ምናቸውም አይመሳሰል ። የእሳቸው ቀለም ጠይም ፥ ለጥቁር የቀረበ ፥ የእሷ ግን ነጭ ነው ። ውስጣቸው ግን በአድራጎታቸው ተከሥቶ ሲታይ ሁለትነቱ ቀርቶ አንድ የሆነ ይመስላል ። በሁለት አካል የሰፈረ አንድ የሚያስቀና ሕይወት ከፊቱ የተቀመጠ መሰለው ።

በነጭና በጥቁር ጋብቻ ላይ የነበረው አቋም ድንገት በሐሳቡ ብልጭ አለበት ። ማርታ ፥ “ ዋናው ነገር ፍቅር ነው” ያለችው ትዝ አለው ።

“ አዎ ፥ ለነገሩማ ጉዞአችንስ ወደ ዓለም አቀፋዊነት አይደል ? የቀለምና የወሰን ችግርን የፈጠሩት የሰው ልጆች ናቸው ። ይህን ችግር ማጥፋት ያለባቸውም እነሱ ናቸው ። ሰውን በመደብ የከፈለውና በድንበር የለየው ፥ ‘ ሥልጣኔ’ የሰው ልጅን መልሶ አንድ ማድረግ አለበት ። የዓለም ሰዎች ነጠላ ሕዋስ ሁሉ አንድ ነው ፤ የዓለም ሰዎች እስትንፋስ ሁሉ አንድ ነው ። በሰው ልጆች መሐል ከሰውነት ውጭ የሆነ ነገር የለም ። የዓለም ሰዎች በጋራ መቋቋምና ማሸነፍ ያለባቸው በሚኖሩበት ምድር ላይ የሚገጥማቸውን የተፈጥሮ ችግር ነው ። የሰው ልጅ ግቡ ተፋቅሮና ተባብሮ አካባቢውን ድል መምታት ፥ ተፈጥሮን በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ ነው ” እያለ እስክንድር በሐሳቡ ሲዋዥቅ ፥ የእነ ዮናታንን ጨዋታ በሙሉ ልቡ አላደመጠም ነበር ። ወይዘሮ ሞኒካ በአማርኛ “ ተቱ” ብላ ቡናውን ስታመለክተው ፥ ወይም “ተቻወቱ” ስትለው ብቻ በግማሽ ስሜት ጥርሱን ብልጭ ሲያደርግ ነው የቆየው ።

በመጨረሻም ከመሔዱ በፊት አቤል መኝታ ክፍሉን አስጎበኘው ።

“ ፐ ! ያስቀናል ። ብቸኛ ክፍል ። ጣፋጭ ሕይወት እንደሚጠብቅህ እርግጠኛ ነኝ ” አለው እስክንድር ፥ በክፍሏ ከልቡ ተማርኮ ።

" የካምፓሱን ሕይወት ለእናንተ ትተናል " በማለት አቤልም ቀለደ ።

ከአቤል አፍ ለዛ ያላቸው የቀልድ ቃላት ከልባዊ ፈገግታ ጋር መውጣት ካቆሙ ወራት ዐልፈዋል። እናም፣ እስክንድርን የአሁኑ የአቤል ጅማሬ ደስ አሰኘው ። ምናልባትም የሕይወቱ ለውጥ መጀመሪያ ይሆናል ሲል ገመተ ።

ቀልዱ ለቀልድ ጋብዞት እስክንድርም ፣ " የትዕግሥትንስ ነገር ? " ለማለት ከጅሎት ነበር።ከምላሱ ነው የመለሰው! በአሁኑ ሰዓት አቤል ለትዕግሥት ያለውን ስሜት ለማወቅ ቢጓጓም ይህን አርዕስት ከማንሣት ተቆጠበ ።

አቤል እስክንድርን ትንሽ መንገድ ሸኝቶት ከተለያዩ በኋላ ወደ አዲሱ ቤቱ ሲመለስ ስለ ወላጆቹ እያሰበ ነበር ። እናቱ ትዝ አሉት ። መልስ ያልሰጠበት ደብዳቤያቸው ታወሰው ። አዲስ ወላጆች ስለ ማፍራቱ ደብዳቤ ሊጽፍላቸው አሰበ ።



# ምዕራፍ ሀያሰባት

አቤል ካምፓሱን በለቀቀ ማግሥት ሳምሶንም ጓዙን ይዞ ስለ ወጣ ፣ እስክንድር ፊቱን ወደ ዩኒቨርስቲው ማዞር አስጠልቶት ሦስት ቀን ያህል መኖሪያ ቤቱ ነበር የሰነበተው ። እዚያም ሆኖ የአቤልን ጉዳይ ለማስፈጸም ወዲያ ወዲህ ማለቱ አልቀረም ። ብርቅነሽን አነጋግሮአት አቤል ያካፈላትን ምስጢር ለቢልልኝ እንድትነግራቸው አድርጓል ። መጀመሪያ ብርቅነሽ ፍርድ ቤት የመቅረብ ያህል ቆጥራው እምቢ ብላ አስቸግራው ነበር ። በብዙ ውትወታና ማሳመን ነው ወደ ቢልልኝ የወሰዳት ። ከእሷም ሌላ አቤል ቀድሞ በርቀት ካስተዋወቀው ሰዎች መሐል ለሥነ-ልቡናው ምርምር ጥቂት ይረዳሉ ብሎ የገመታቸውን ከቢልልኝ ጋር በመመካከር አነጋግሮአቸዋል ። እሱም እንደ ዮናታን በጓደኛው በአቤል ጉዳይ ውስጥ እጁን ማስገባቱና አንዳንድ ጠቃሚ ውጤቶች ማስገኘቱ አስደስቶት የበለጠ እንዲገፋበት እያደረገው ነበር ።

በአራተኛው ቀን ወደ ካምፓስ ሲገባ ሁለት ሴቶች በጥብቅ ሲፈልጉት እንደ ሰነበቱ ድብርት ነገረው ። ቶሎ ሐሳቡ ውስጥ የመጣችበት ማርታ ነበረች ።

" ምን ዐይነት ሴቶች ? " አለው ፣ ለማወቅ ቸኩሎ ።

" አንዷ ወፍራም ቀይ ፣ አንዷ መጠነኛ ወይም ሁለቱም አጭሮች " ካለው በኋላ ፣ የነገሩትን ስም አስታውሶ ፣ ድብርት " ቤተልሔምና ትዕግሥት የሚባሉ " አለው ።

" አሃ ! " አለ እስክንድር ። የተፈለገበት ምክንያት ምን እንደሆነ ለመገመት ጊዜ አልወሰደበትም ። ነገር ግን በጣም የጓጓው ስለ አቤል የሚቀርብለት ጥያቄ ከትዕግሥት ከራሷ አፍ ይወጣ እንደሆን ለመስማት ነበር ።

ሁለቱም በምሳ ሰዓት ወደ መመገቢያው አዳራሽ ሊገቡ ሲሉ አገኟቸው ።

" በእግር በፈረስ ስትፈለግ የት ነው እንዲህ የጠፋ ሽው ? " አለችው ቤተልሔም ።

" በመኪና ብትፈልጉ ፣ ታገኙኝ ነበር ! " ሁለቱም ሴቶች በቀልዱ ሣቁ ።

" ማርታ 'ኮ ሔደች ! " አለችው ቤተልሔም ፣ ሣቋን ገታ አድርጋ ።

" የት ? " አላት የደመ - ነፍሱን ።

" ወድቃ ፣ ትላንት ሻንጣዋን ይዛ ግቢውን ለቀቀች ። "

' እና ? እና ታዲያ እኔ ምኗ መሰልኳት ፣ የማርታን መርዶ የጨዋታ መክፈቻ የምታደርግልኝ ' አለ እስክን ድር በልቡ ።

" በራሷ ጥፋት ነው " አለች ቤተልሔም ፣ ከእስክን ድር መልስ ስታጣ ።

" እንዴት ? "

" ጸባይ የላትም ። ጸባይ ቢኖራት ኖሮ — ሀእ ! " አለ ችው ፣ እንደ ሕፃን ልጅ ለምቦጭዋን ጥላ ።

' ጸባይ ወይስ ጭንቅላት ? ' አለ እስክንድር በሐሳቡ ። ምን ለማለት እንደ ፈለገች ገብቶታል ። ወዲያው ትዝ ያለው ማርታ ለማን አጥላልታ ያወራችለት ነገር ነበር ።

" ያንተስ ጓደኞች ? " አለችው ትዕግሥት በድንገት ። ስለ አቤል ለማወቅ ካላት ጉጉት የተነሣ ፣ ሌላውን ጨዋታ ለመስማት ትዕግሥት አጥታ ነበር ።

" ሳምሶን ወድቆ ተባረረ " አላትና አቋረጠ ።

ቤተልሔም የሳምሶንን ስም ሲጠራ እሱ ራሱ አጠገቧ የቆመ ያህል ሽምቅቅ አለች ። ከፍርሀቷ ብዛት ተደብቃው



ከርማ ግቢውን ለቅቆ መሔዱን ካረጋገጠች በኋላ ነበር ከመኝታ ክፍሏ መውጣት የጀመረችው ።

እስክንድር የሳምሶንን መባረር ብቻ ተናግሮ ስለ አቤል ምንም ነገር ሳያነሣ ያቋረጠው ሆነ ብሎ ነበር ። ትዕግሥት ደፍራ ትጠይቀው እንደሆን ሊፈትናት ፈልጎ ነበር ።

ትዕግሥት ዐይን ዐይኑን አየችው ። የምትፈልገውን እንዲነግራት በዐይኗ ለመነችው ። ነገር ግን ከእስክንድር አፍ ጠብ ያለ ነገር አልነበረም ።

"አቤልስ ? " አለችው ደፍራ ። ድምጿ ግን ድክምክም ብሎ ነበር ።

እስክንድር ደስ አለው ። ትዕግሥት ለመጀመሪያ ጊዜ የአቤልን ስም በጓደኛው ፊት መጥራቷ በእርግጥም ትልቅ ለውጥ ነበር ። ደስታው ስላስደነገጠው ቶሎ መልስ አልሰ ጣትም ። የእሱም ድምፅ እንደ እሷው እንዳይደክክም መጠ ንቀቅ ነበረበት ።

" አቤል እንኳ አልወደቀም ። ግን እሱም ካምፓሱን ለቅቆ ወጥቶአል " አላት ።

እስክንድር ይህን ሲናገር፣ከትዕግሥት ፊት ላይ የጠበቀ ውን ለውጥ አልተመለከተም ። አቤል ግቢውን መልቀቁ ያስደነግጣታል ብሎ ነበር ። ነገር ግን ትዕግሥትም ሆነች ቤተልሔም ለዚህ ዜና እንግዳ አልነበሩም ። አቤል በዮናታን መኪና ሻንጣውን ጭኖ የወጣ ዕለት፣በሩቅ ያዩት ተማሪዎች ወሬውን ቀምመው ሲያራቡ ነው የሰነበቱት ። እና አሁን የትዕግሥት ጉጉት የአቤል መውደቅ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ ብቻ ነበር ።

" ታዲያ ካልወደቀ ለምን ካምፓሱን ለቅቆ ወጣ ? " አለችው ትዕግሥት - በጥርጣሬ ።

" በሌላ ምክንያት ነው " አላትና እስክንድር ፣ ለአመ ላለስ ተቸግሮ ፣ " ሰፊ ነው ነገሩ ፤ በቁም ጨዋታ የሚያልቅ አይደለም " አለ ።

አላመነችውም ፤ ፊቷ ላይ ጥርጣሬ አነበበ ። የተከፋው ገጽታዋ አቤል ወድቋል ብላ እንደ ደመደመች ይናገራል ። ይህ እስክንድርን ብዙ አላስጨነቀም ። ጊዜውን ጠብቆ ሁሉን ነገር እንድታውቀው ይደረጋል ። ዋናው ነገር በሩ መከፈቱ ነው ፤ የአቤልን ስም እንሥታ በግልጽ መጫወት ጀምራለች ።

‘ ግን ምን ይሆን ፣ ወይስ ማን ይሆን ያደፋፈራት ? ’ ሲል አሰበ ።

ከደስታው የተነሣ ምሳውን በሚበላበት ጊዜ ፣ ጉዳይ እንዳለበት ሰው እየተጣደፈ ቶሎ ቶሎ ነበር የጎረሰው ። ምግቡን ቶሎ ጨርሶ ፣ ያንን ሰው የበዛበት አዳራሽ ለቅቆ ወጥቶ ፣ ብቻውን ከሐሳቡ ጋር እየተሟሟቀ ለመፈንደቅ ካልሆነ በስተቀር ፣ ሌላ የሚሔድበት ቦታ አልነበረውም ።

መኝታ ክፍሉ ገብቶ እንደ ወትሮው አጭር የቀን እንቅልፍ ለመተኛት ቢሞክርም አልሆነለትም ። ከውጭ ይዞት የገባው ደስታ ጠፍቶ ትካዜ ተጫጫነው ። ከክፍሉ ውስጥ አቤልንና ሳምሶንን ማጣቱ ቅር ቅር አሰኘው ። ወና ቤት ውስጥ የገባ ይመስል ሰውነቱን ቀፈፈው ። ለሚቀጥሉት አራት ወራት በዚህ ክፍል ውስጥ የሚያሳልፈው ሕይወት በጣም ብቸኛ ሆኖ ታየው ። በእርግጥ አጠገቡ ድብርት አለ ፤ ግን ድምፁ ከማይሰማ ሰው ጋር እንዴት ይኖራል ?

ሳምሶን “ ጉልቤው ” መኝታ ክፍሉን ምን ያህል ያደምቀው እንደ ነበር የገባው አሁን ነው ። እየፈሳም ሆነ እየዘለለ ወይም ድብርትን እያበሸቀ ለክፍሉ ሕይወት ይሰጠው ነበር ። መቼም መለያየት ክፉ ነው ፤ እንደዚያ የሚያበሽቀው ድብርት እንኳ ሳምሶን ሲባረር ተገላገልኩ አላለም ። ከልቡ ነበር ያዘነለት ።

እስክንድር እንደ ተጋደመ ስለ ሳምሶን ሲያስብ የተለያዩበት ቀን ትዝ አለው ። በሰላም አልነበረም የተለያዩት ።

ሳምሶን ሰው ሳያየው ተደብቆ ካምፓሱን ለመልቀቅ ከሌሊቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ዕቃቸውን ሲያስነዳዱ እስክንድር ድንገት ከእንቅልፉ ባነነ ። ሆኖም አዝማሚያው



ስለገባው ፣ እስኪ መጨረሻውን ልመልከት ብሎ ፊቱን ከአንሶላው ውስጥ ሳያወጣ ጭጭ ብሎ ያዳምጥ ጀመር ። ሻንጣውን አዘገጃጅቶ ጨርሶ ሊወጣ በሩጋ ሲደርስ ከአንሶላው ውስጥ አሾልቆ ተመለከተውና ፣ “ ሳምሶን ! ” ብሎ በኃይለ ቃል ጠራው ።

“ ምነው ? ! ” አለው ሳምሶን ዘወር ብሎ ፣ ከቁጣ ባልተለየ ድምፅ ። ስለ ተንቃበት ተናዶ ነበር ።

“ ምን ሆንሃል ? ”

“ መሔዴ ነው ። ”

“ ታዲያ እንዲህ ነው እንዴ የሚኬደው ? ምነው ሳምሶን ? የተወሰነ ጊዜም ቢሆን በጓደኝነት አሳልፈናል ። ቻው ብለኸን በሰላም ሸኝተንህ ብንለያይ ምናለበት ? መውደቅ በአንተ አልተጀመረ ! ” አለው እስክንድር ፣ ሆድ ብሶት ።

“ ሸኝ አልፈልግም ! ያው ሰፈር እንገናኛለን” ! ብሎ ጥሎት ሔደ ።

‘ ሰው ለምን ድክመቱን ለመሸፈን ሲል አውሬ ይሆናል ? ’ አለ እስክንድር በልቡ ። በሳምሶን አልበሸቀበትም ። እንዲያውም ፣ ‘ በዚህ በንዴቱ ሰዓት ምግብ ቢቀርብለት እንደ ቀድሞው ይበላ ይሆን ? ’ ብሎ አስቦ ሣቅ አለ ። ‘ ጥር ሳሞኝ ! ’ ሲል በሐሳቡ ታየው ።

ሰው የሚገናኝበት አጋጣሚና የሚለያይበት ሁኔታ ሲመዛዘን መለያየቱ ይከብዳል ። እስክንድር የዩኒቨርስቲ ሕይወቱን በሐሳብ ሲዳስስ ፣ ግቢው አስተዋውቆት ጊዜ ያለያየው ብዙ ተማሪዎች ታወሱት ። በተቀራረበ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎች የሚገኙበት ግቢ በመሆኑ፣ አብዛኛውን ጊዜ የጋራ የሆኑ ስሜቶች ይንጸባረቃሉ ። ይህ ሳይሆን አይቀርም - በትምህርት ዓመታት ላለፈው የጋራ ኑሮ ጣዕም የሚሰጠው ። ለጊዜው ሆዱን ያባባው ሳምሶንና አቤል ግቢዉን መልቀቃቸው ነው ። ነገር ግን ከአራት ወራት በኋላ እሱም ራሱ ግቢዉን ይለቃል ። አብረውት የነበሩት ሁሉ በተለያየ የሥራ

መስከ ተብታችነው በየፊናቸው የግል ጎጆአቸውን መቀየስ ይጀምራሉ ። የዩኒቨርስቲ የጋራ ሕይወት የሩቅ ትዝታ ሆኖ ይቀራል ።

ለክፉም ለደጉም አሁን ከእስክንድር አጠገብ ያለው ሰው ድብርት ነው ። አብሮት ሴሚስተሩን ሊያሳልፍ የሚችል ሰው እሱው ነው ። እናም የግዱን እንዲጫወት ይጎተጉተው ጀመር ።

" እንዴት ነው ? ውጤትህን ለወላጆችህ ነገርካቸው ? " ሲል ጠየቀው ።

" ለማን እነግራለሁ ብለህ ነው ? " አለ ድብርት ኀዘን በተቀላቀለበት ድምፅ ።

" እንዴት ? "

" አባቴ ቢሰማም ግድ የለኝም ። እሱም ግድ የለው " አለው ድብርት ። ምን ስሜቱን ፈንቅሎ እንዳናገረው ገረመው ።

" ታዲያ ለእናትህ አትነግራቸውም ? "

" እኔ እናት የለኝም ፣ የእናት ጣዕም አላውቅም " አለው ምርር ብሎ ።

እስክንድር ከተጋደመበት ቀና አለ ። ወሬው ጆሮውን ብቻ ሳይሆን መላ ሰውነቱን አነቃቃው ።

" ምነው ? ለምን ? " አለው እስክንድርም እዝን ብሎ ፣ ወዲያውም የምስጢሩን ካዝና ለመሰርሰር ጓጉቶ ።

' ድብርት ' ቶሎ አልመለሰለትም ። ሲያመነታ ቆየ ። ሁሉን በሆዱ ይዞ እንደ ቆየ ሁሉ፣ አሁንም የቀረችዋን አንዲት ሴሚስተር እንደ ታፈነ መጨረስ ፈለገ ። ነገር ግን የእስክንድር አጣያየቅ ከበደው ።

' ወይ ቀድሞውኑ ጫፍ ባላስያዝኩት ኖሮ ! ' አለ በልቡ ። በአፉ ባይናገረውም በልቡ ለእስክንድር ፍቅርና



ክብር ነበረው ። እንደ ሌሎቹ ስለማይተናኮለው ብቻም ሳይሆን ፣ ከአብዛኛው ድርጊቱ የሚያይበት ብስለት፣ፍቅር አሳድሮበታል ።

" ማለቴ ፣ እናትህ በቅርብ የሉም እንዴ ? " አለው እስክንድር እንደገና ፣ ኀዘኔታ አዝሎ በሚያውጣጣ የአነጋገር ስልት ።

" በልጅነቴ ነው እናቴ የሞተችው " አለ ድብርት ፣ " እሷ ስትሞት ነፍስ አላውቅም ነበር ። ለዚህ ነው ጣዕሙን አላውቅም ያልኩት ። "

እስክንድር ከንፈሩን መጠጠ ። ሌላ ማስተዛዘኛ መንገድ አልነበረውም ።

" ደኅና አባት ቢኖረኝ ኖሮ እንኳ፣ የእናቴ ሞት ያንያህል ባልጎዳኝ ነበር " አለው ድብርት ፣ የእስክንድርን ማዘን አይቶ ።

" አባትህ . . . "

" አባቴ አረመኔ ነው !! "

እስክንድር ቃላቱ ሰቅጥጦት ጭጭ አለ ። አጠገቡ ሆኖ የሚያወራው ሰው፣የድሮው ድብርት ሊመስለው አልቻለም ። ልሣኑ መከፈቱ ብቻ ሳይሆን ፣ የአነጋገር ስልቱም ነው የተቀየረበት ። ታፍኖ ቆይቶ የፈነዳ ነገር ነው የሆነበት ። ' ቁስል መጥፎ ነው ፤ ዲዳንም ያናግራል ' አለ በልቡ ። በዚህ ረገድ መኝታ ክፍሉ ውስጥ ሁለቱ ብቻ መቅረታቸውን ወደደው ። ብቻቸውን ባይሆኑ ኖሮ እንዲህ ምስጢሩን እያወጣለትም ነበር ።

" ከእናቴ የተወለድነው እኔና አንዲት እኅቴ ነን ። አባቴ ለሁለታችንም አስተዳደግ ደንታ አልነበረውም ። በጥረታችን ነው ያደግነው ማለት እችላለሁ ። እኔ እንደምንም ተፍጨርጭሬ ዩኒቨርስቲ ገባሁ ። እኅቴ ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል ወድቃ አሁን የአውራ መንገድ አውታታ ሆናለች ። "

" አባትህ ከእናትህ ሞት በኋላ ሌላ ሚስት አላገቡም ማለት ነው ? "

" ምን ያገባል ? ! እሱ ሁሏም ሚስቱ ነች ። እኛን በገረድ ነው ያሳደገን ። ለዚያውም ደም " አለና ድብርት ፣ ሊቀጥል ያሰበው ነገር ለራሱም አስጠልቶት አቋረጠ ።

በአባታቸው ግድየለሽነት ሳቢያ ድብርትና እኅቱ በቤት ሠራተኞችም እየተሠቃዩ ነበር ያደጉት ። ገረዶች ሲለዋወጡባቸው ነበር የኖሩት ። የሚቀጠሩት የቤት ሠራተኞች እነ ድብርትን ለመጀመሪያ ጊዜ በደንብ ይመግቧቸዋል ። ውለው ሲያድሩ ግን የአባታቸውን ፍቅረ-ቢስነት ይመለከቱና እነሱም ቸል ይሏቸዋል ። አባታቸው ሰክረው ሲመጡ ቤት ውስጥ የተገኘችውን ሠራተኛ ፣ " እግርሽን ታጠቢ ፤ ከእኔ ጋር ነው የምትተኚው " ይሏታል ። ከዚያ በኋላ በቃ ! ሠራተኛዋ የቤት እመቤት ትሆንና ልጆቹን ቁልቁል ማየት ትጀምራለች ። ከእነሱ ይልቅ እሷ ተሰሚነት ይኖራታል ። በተለይ ድብርት አባቱ ፊት ምንም ቃል እንዲተነፍስ አይፈቀድለትም ነበር ።

ለልጆቹ የሚያዝኑ አንዳንድ ደግ ሠራተኞች ቢገቡም ብዙ አይቆዩም ። የተለመደው ፣ " እግርሽን ታጠቢና " ሲከተል ሠራተኛዋም በወር ውስጥ ፣ " አረገዝኩ " ትላለች ። ይኼኔ የድብርት አባት ፣ " ጓዝሽን ጠቅልይና ውጪ ! " ብለው ያባርሯታል ። አብዮቱ ከፈነዳ ወዲህ እንደዚያ መቀጠል ስላልቻሉ ፣ በተለይ አንዲት ሠራተኛቸው በቀበሌ ማኅበር ክስ ስላስቀጣቻቸው ፣ ገረድ መቅጠሩን እርም ብለው ትተውታል ። ልጆቹ ራሳቸው አብስለው እንዲበሉ ተገደዱ ።

ታዲያ ድብርትና እኅቱ በልጅነታቸው በሠራተኛ ተጨቁነው ሲርባቸው ፣ ይመካከሩና ሠራተኛዋ ሳታይ መሶብ ከፍተው ይበላሉ ። ነገሩ ተንቅቶባቸው አባታቸውጋ ሲደርስ ድብርት ድርቅ ብሎ ይክዳል ። እኅቱ ትፈራና እውነቱን ታወጣለች ። ከዚያ በኋላ በድብርት ላይ የሚወርደው የዱላ ውርጅብኝ አያድርስ ! ጭንቅላቱን ከመሬት ጋር አጣብቀው ይቀጠቅጡታል ። ይረግጡታል ። አመታታቸው የአባት ዐይነት አልነበረም ። እሱ ግን ገና ለገና እመታለሁ ብሎ ራብ ሲጥረመረው መሶብ ከፍቶ መብላቱን አልተወም ። ጭራሽ ጋግርታም እየሆነ ሔደ ። አባቱ ፊት ቀርቦ ሲጠይቁት ፣ አፉን



ዘግቶ ድርቅ ፣ ድፍን ሲልባቸው አሳቸውንም ያስፈራቸው ጀመር ። ይህ ጸባይ እያደገበት ሔዶ በቤት ብቻ ሊወሰን አልቻለም ። ውጭም ባለው ማኅበራዊ ግንኙነት ድብርት ሆኖ ቀረ ።

" ግን አባትህ ጤነኛ ናቸው ? " ሲል እስክንድር በመገረም ጠየቀው ።

" በግድ በመጠጥ ኃይል ራሴን ላሳብደው ካላለ፣ ጤነኛ ነው ! " አለ ድብርት በምሬት ድምፅ ።

እስክንድር ዘልቆ ሊጠይቀው አልፈለገም ። ድብርት በአባቱ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ እንዳለው ካወቀ በኋላ፣ ለሚጠይቀው ሁሉ ጤናማ መልስ እንደማይሰጠው ገመተ ። እስክንድር የድብርትን አባት ጸባይ ሊያይ የሞከረው በተለየ መልክ ነበር ። ድብርት ለአሁኑ ጸባዩ ምክንያት የሆነው ያን ዐይነት ሥር ካለው ፣ አባቱም ያንን ዐይነት ጸባይ ያበጁበት ሥር ያለው ምክንያት ይኖራቸው ይሆን የሚል ጥርጣሬ አደረበት ። ምናልባት የሚስታቸው መሞት አእምሮአቸውን ረብሾት ነካ አድርጎአቸው ይሆናል የሚል ሐሳብ ገባው ። ነገር ግን ፣ ' እረ ባክህ እስክንድር ፣ ምንስ ቢሆን ይህን ያህል በወለዳቸው ልጆች ላይ አውሬ የሚሆን አባት ? ' ሲል የኅሊና ሙግት ገጠመው ።

በአንጻሩ የራሱ ሟች አባቱ በሐሳቡ መጡበት ። እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ከእስክንድር ጋር በፍቅር ነበር የኖሩት ። ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ከአባቱ ጋር ገበታ ቀርቦ ፣ የሔዱበት እየተከተላቸው ነው ያደገው ። በተለይ ወንድ ሆኖ በመፈጠሩ ይኮሩበት ነበር ። ስለዚህ ጠጅ ቤትም ፣ ዕድርና ዕቁብ ቦታም ቢሔዱ እያስከተሉት ፣ ነጻ ስሜት እንዲኖረው አድርገው ነው ያሳደጉት ። እንዲያውም እናትየዋ ፣ " ልጄን አባለከብኝ " ሲሉ ዘወትር ጸብ ነበር ። አሁን የድብርትን አባት ታሪክ ከሰማ በኋላ፣ አባቱን ይበልጥ በልቡ አመሰገናቸው ።

" አይዞህ ፣ ለማንኛውም አሁን አንተ ራስህን ከምትችልበት ደረጃ ላይ ደርሰሃል " ሲል አጽናናው ።

" ነገሩ ነው እንጂ ፣ እሱማ የት ይቀራል ? " በማለት ድብርትም ራሱን ነቀነቀ ።

እስክንድር ተክዞ ቀረ ። በየቤቱ ስንት ድብቅ ልብ አለ! በማለት ተገረመ ። ሁላችንም ብንሆን በጉልምስናችን ዘመን የምናሳየው ጸባይ ራሱን የቻለ መሠረት አለው ። ግማሹን ከወላጆቻችን ደም ፥ ግማሹን ደግሞ ከምንኖርበት አካባቢ ይዘን የመጣነው ጸባይ ነው - አሁን የምናንጸባርቀው ። እና ፥ ማርታም ለቅናት ቅንድቧ የሚርገበገብበትና ለሐሜት ጆሮዋ የሚቆምበት ፥ ሳምሶንም የምግብ ፍቅርና የጉልበተኝነት ጸባይ የሚታይበት ፥ ሁሌም ከበስተጀርባው ለማንነቱ ሳቢያና ምክንያት አለው ። በዚህ ዓለም ላይ ከአካባቢው ነጻ ሆኖ የሚኖር ሰው ማን አለ ?

የድብርትን ታሪክ ከሰማበት ደቂቃ ጀምሮ እስክንድር በዚህ በቅጽል ስሙ መጥራቱን አቆመ ። የቅጽል ስሙ ራሱ መጥፎ ሥነ ልቡናዊ ተጽዕኖ እንዳለው ገምቶ፥አሥራት በሚለው ትክክለኛ ስሙ ይጠራው ጀመር ።

የእስክንድር ስሜት አሥራትን ለማስደሰት ቸኮለ ። ይህን የተደበቀ ልቡን ከፍቶ ያጫወተውን ሰው ፍቅሩን በምን መንገድ ሊገልጽለት ይችላል ? የመጋበዝ ሐሳብ መጣበት ። ግን ምን ? ያው መጠጥ ነዋ ! ከአካባቢው የወረሰው ልማድ ሆኖበት ፥ ሰውን ማስደሰት ሲያስብ መጠጥ መጋበዝ ነው የሚታየው ። ነገር ግን ሐሳቡን እስቦ በእደ ኅሊናው ኪሱን ቢዳብስ ፥ ቤሳ ቤስቲን አልነበረውም ።



# ምዕራፍ ሀያስምንት

ቢልልኝና ረዳቶቻቸው በስብሰባው አዳራሽ ቀድመው ቦታቸውን ይዘዋል ። ከዩኒቨርስቲው አስተዳደርና ትምህርት ክፍል በአቤል ላይ የተካሔደውን የሳይኮሎጂ ጥናት እንዲያዳምጡ የተጋበዙት እንግዶች እየተንጠባጠቡ ገቡ ።

ዮናታን ፈገግታ በፈገግታ ሆነው አዳራሹ መግቢያ በር ላይ ከእስክንድር ጋር ቆመው ለእንግዶቻቸው ሞቅ ያለ ሰላምታ በመስጠት ላይ ነበሩ ። እስክንድር ከዮናታን ግዙፍ ቁመና ሥር ገብቶ አንድ ፍሬ ልጅ ይመስላል ። እንግዶቻቸውን አስገብተው ከጨረሱ በኋላ እነሱም ገብተው ተቀመጡ ።

ቢልልኝ ንግግሩን ለመክፈት ተነሥተው ጉሮሮአቸውን ሲስሉ አዳራሹ ጸጥ አለ ።

“ እንግዶቻችን ፥ እንኳን ደኅና መጣችሁ ፥ የዛሬው አርዕስታችን በዐይን ፍቅር የተለከፈ ወይም የተጠመደ አንድ ወጣት ነው ። የሥነ - ልቡና ጥናት ክፍላችን በዚህ ወጣት ችግር ላይ ዐቅሙ በፈቀደ መጠን ጥናት አድርጎ ውጤቱን ይዞ ቀርቧል ። ”

እንግዶቹ መሐል ጥናቱ የተካሔደበት ወጣት ማን እንደሆን የሚያውቁ ስለነበሩ፥ በስሜታቸው ውስጥ ወጣቱን የማወቅ ጉጉት ያዛቸው ። አቶ መአምርና ዶክተር አጥናፉ እንዲሁም ሌሎች ከአሁን በፊት ዮናታን የአቤልን ጉዳይ ያማከሯቸው ሰዎች ቸል ያሉት ጉዳይ አድጎ እዚህ መድረሱ ሳያስደንቃቸውም ሳያሳፍራቸውም አልቀረም ። የአንድ ተማሪ የዐይን ፍቅር ችግር፥ ክብደት ተሰጥቶት ይህን ያህል መጠናቱ አስገርሞአቸው አዳራሹ ውስጥ እንዲያው ለትዝብት የተቀመጡም አልጠፉም ።

“ በመጀመሪያ ለዚህ ተማሪ ግላዊ ችግር አትኩሮትና ክብደት ሰጥተውት ሳይታክቱ ጥረት በማድረግ ለደከሙ

ለት ለፍልስፍና መምህር ዮናታን ምስጋና እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ ።”

ሞቅ ያለም ባይሆን ድጋፉን የሚገልጽ መጠነኛ ጭብጨባ ሲሰማ ፣ ዮናታንም ሳያስቡት ለራሳቸው እያጨበጨቡ ነበር ።

“ ዮናታን ፣ በዕውቀቱ የሚተማመኑበት ጎበዝ ተማሪያቸው ሲደክም ወይም ሲሰንፍ እያዩ ቻል ቢሉት ኖሮ፣የአቤል ውስጣዊ ችግር ተዳፍኖ ውጤቱ ከዩኒቨርስቲው መባረር ነበር ። በዚህም ሆነ በሌላ ተመሳሳይ ችግር ከአሁን በፊት በርካታ ጎበዝ ተማሪዎች በአጭር እንደ ቀሩ ጥርጥር የለውም።

“ በመደበኛ ተማሪነት ወደ ዩኒቨርስቲያችን ከሚገቡት መሐል አብዛኛዎቹ ወጣቶች ናቸው ። ጥሩውንና ገንቢውን ነገር በፍጥነት እንደሚቀበሉ ሁሉ ፣ ለአደጋና ለአፍራሽ ነገሮችም በቀላሉ ይጋለጣሉ። በዩኒቨርስቲያችን በተካሔደው የሳይኮሎጂ ጥናት መሠረት የተማሪዎቹ ዋነኛ ችግሮች ሦስት ናቸው ። አንደኛ ፣ ወላጆቻቸው ችግረኞች በሆኑ ተማሪዎች ላይ የሚታየው የኢኮኖሚ ችግር ነው ። ይኸው ችግር እያስገደዳቸው የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን እያቋረጡ የወጡ ተማሪዎች አልጠፉም ። ሁለተኛ ፣ የማርክ ወይም የደረጃ ችግር ነው ። ማንኛውም ተማሪ አነስተኛ ውጤት ማግኘት አይፈልግም ። ነገር ግን ፉክክር እስካለ ድረስ መበላለጥ አለ ። ይህን ሐቅ መቀበል አቅቷቸው ፣ ወይም ለጥናት የሚያደርጉት ጥረትና የሚያገኙት ውጤት አልገጣጠም እያላቸው ከራሳቸው ጋር የሚጣሉም ሞልተዋል ። ሦስተኛ በሁለቱ ትርጉም ጾታዎች ግንኙነት ላይ የሚታየው ችግር ወይም በድፍን ፣ “ ፍቅር ” እየተባለ የሚጠራው ነው ።

“ ዛሬ ይዘን የቀረብነው በዚህ በሦስተኛው ችግር የተጠመደ ወጣት አርዕስት ነው ። ወደ ወጣቱ ጉዳይ ከመግባታችን በፊት ፍቅር የሚለውን ቃል ለማተት እንገደዳለን ። እዚህ ላይ የማተኩረው በሁለቱ ጾታዎች መካከል ዕድሜን ተከትሎ በሚመጣው ፍቅር ላይ ነው ።

“ ፍቅር በልባችን ውስጥ ታላቅ ቦታና ክብደት ያለው ፣ ከልባችን ውጭ ግን የሚገባውን ክብደትና አትኩሮት የነ



ፈግነው ጉዳይ ነው ብል ማጋነን አይመስለኝም ። አንድ ፈላስፋ እንዳለው ፣ ዓለምን የሚያንቀሳቅሷት ፍቅርና ረሃብ ናቸው ። አንጋፋው ሳይኮሎጂስት ፍሮይድ የፍቅርን ክብደት ሲገልጽ ፣ ‘ ጥላቻ ማለት ሞት ነው ፤ ፍቅር ደግሞ ከጥላቻ የጠነከረ ነው ። እናም ፍቅር ከሞት ይጠነክራል ማለት ነው ’ ይለዋል ። በመሠረቱ ጤናማ የሆነና ጤናማ ያልሆነ የፍቅር ዐይነት አለ ። ሌላው የሥነ-ልቡና ጥናት ሊቅ ሆርኒ እንደሚለው ፣ ጤናማ ያልሆነው የፍቅር ፍላጎት ጠንክሮ ሊገለጽ የሚችለው ለፍቅር ባለን ከመጠን ያለፈ ግምት ነው ።

“ ለመሆኑ ፍቅር ምንድን ነው ? ከባድ ጥያቄ ነው ። አብዛኛዎቻችን ፣ ‘ ፍቅር ዕውር ነው ’ እንላለን ። ነገር ግን ፍቅር ዕውር አይደለም ። ፍቅርን በግድ ዕውር የምናደርገው እኛው ነን ። ወይም በፍቅር ላይ ዕውራን እኛው ነን ለማለት እደፍራለሁ ። ይህም ራሱን የቻለ ምክንያት አለው ። የባህል ኋላ-ቀርነታችን ፍቅርና ወሲብን ውስጥ ውስጡን እንድናደርጋቸው እንጂ በአደባባይ እንዳንወያይባቸው ስለሚያፍነን ፣ ወይም ከልጅነታችንና ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ በትምህርት መልክ ስለማይሰጥ ይመስለኛል ዕውር የሚሆንብን ። አሁንም ሌላው ሳይኮሎጂስት አንግያል እንዲህ ይላል ። ‘ እውነተኛ ፍቅር ዕውር አይደለም ፤ እንዲያውም ዐይናማ ነው ። ሌሎች የማያዩትን ያያል ። ’

“ በርካታ የሥነ-ልቡና ጥናት ሊቃውንት ለፍቅር በቅርጽ የተለያየ በይዘቱ ግን የተቀራረበ ትርጓሜ ሰጥተውታል ። ይሁንና አብዛኛዎቹ ‘ ፍቅር መተሳሰር ነው ’ በሚለው የተስማሙ ይመስላል ። ሆርኒ እንደሚለው ፣ ፍቅር ራስን በግብታዊነት ለሌላው የመስጠት ችሎታ ነው ። ከአብዛኛው የቀን ተቀን ገጠመኞችን እንደምንረዳው ፍቅር የመለማመድም ውጤት ነው ።

“ ይህ እንግዲህ በጥቅሉ ለፍቅር ያለን ግምት ነው ። ወደ ዋናው አርዕስተ-ነገራችን ስንመጣ ፣ አቤል የተጠመደው በዐይን ፍቅር ሆኖ እናገኘዋለን ። ”

ከተሳታፊዎቹ መሐል አንድ ሰው እጁን ሲያወጣ አይተው ቢልልኝ ንግግራቸውን አቋረጡ ። ሰውየው ይቅርታ ጠይቆ ጥያቄውን ቀጠለ። “ የዐይን ፍቅር የሚለው አርዕስት

እንግዳ ነው የሆነብኝ ። ደሞም ለፍቅር ከተሰጠው ሐተታ ጋር የሚጋጭ መሰለኝ ። እና በመጀመሪያ ይህንን ሊያብራሩልን ቢችሉ ? ”

ጠያቂዉ እጅ ነሥቶ ተቀመጠ ። ቢልልኝ ቀጠሉ ።

“ ወደዚያ ልመጣ ነበር ። በእርግጥም ‘ የዐይን ፍቅር ’ ለብዙዎቻችን እንግዳ አርዕስት እንደሚሆን እገምታለሁ ። በሌላ ስያሜ አስቸጋሪ በመሆኑ ነው በዚሁ ስሙ ለመጥራት የተገደድነው ። ዐይነቱ የደመ - ነፍስ ፍቅር ነው ። አንድን ነገር አይቶ በመውደድ ስሜት ልብ ሲደነግጥ ! ማንኛውም ዐይነት ፍቅር የሚጀምረው ከዐይን ‘ኮ ነው ። ‘ ያላዩት ሀገር አይናፍቅም ’ ይባል የለ ! አይተው ሳያልሙ መላመድ ሆነ መተባበር አይኖርም ። የሚወዱት ነገር ዐይን ውስጥ ከተቀረጸ በኋላ ነው መተሳሰሩ የሚቀጥለው ። ነገር ግን አይቶ በመውደድ ስሜት ልብ የደነገጠለትን ሰው ተቀራርቦ በአካልና በመንፈስ መተሳሰሩ ቀርቶ በዐይን ልማድ ላይ ብቻ ሲወሰን ፥ ከዐይን ፍቅር የተሻለ ስያሜ አናገኝለትም ።

“ ይህ ዐይነቱ ሁኔታ ነው በአቤልና በወደዳት ኮረዳ መሐል የታየው። በጥናታችን እንደ ደረስንበት ፥ አቤል ትዕግሥት አዳነ የምትባለዋን የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ አይቶ ልቡ ውስጥ ከቀረጻት ጀምሮ እነሆ ለአራት ወራት ያህል ያለአንዳች የተቀራረበ ግንኙነት በዐይኑ ብቻ ወዶአታል ። በቅርቡ ለውጡን ከተከታተሉት ሰዎች መረዳት እንደቻልነው ፥ አቤል ትዕግሥትን ቀርቦ ባያነጋግራትም ፥ ቀጥተኛ የአፍቃሪ ስሜት ይታይበት ነበረ ። በቂ ያለመብላት ፥ እንቅልፍ ማጣት ፥ ትምህርቱን መጥላትና ብቸኛ መሆን በዐይን ፍቅር ከተጠመደ ወዲህ ያሳያቸው የጸባይ ለውጦች ናቸው ። ልጅቷን ሳያያት ውሎ ማደር አይችልም ። ነገር ግን ይህን እይታውንም ሆነ ውስጣዊ መውደዱን ሰው እንዳያውቅበት በመጠንቀቅ ብቻውን ተሠቃይቷል ። ደረጃው ይለይ እንጂ ትዕግሥት ራሷም ከቀን በኋላ የዐይን ፍቅር እንደ ያዛት ደርሰንበታል ። ሁለቱም እንደ አፍላ ፍቅረኞች



ይነፋፈቃሉ ፤ ተፈላልገው ይተያያሉ ፤ ነገር ግን መነጋገር ቀርቶ ሰላምታ አይለዋወጡም ። ”

በአዳራሹ ውስጥ ማጉረምረም ተሰማ ። ጉርምርምታው መደነቅንም ፥ ሣቅንም የያዘ ነበር ። የአቤልና የትዕግሥት ግንኙነት ለብዙዎቹ እንቆቅልሽ ሆነባቸው ። በአንጻሩ ፥ የሁኔታውን እሙንነት ተረድቶ ፥ የግል ቁስሉን የነኩትን ያህል እየተሰማው ጸጥ ብሎ የሚያዳምጥም ነበር ። ዮናታንና እስክንድርም ሁኔታው በቢልልኝ ሲተረክ እንደ እንግዳ ፈዘው ነበር የሚያዳምጡት ።

“ የእኛ ጥናት የሚያተኩረው የሁኔታውን ምንጭ አጥንቶ መፍትሔ ከመፈለጉ ላይ ነው ። አቤል በመጣበት መንገድ ሌሎች ተማሪዎች እንዳይመጡ በገንቢ ሁኔታ ምንጩን ከማድረቅ ላይ ነው ። በዚህም መሠረት አንዳንድ አስፈላጊ ጥያቄዎችን አንሥተን እንድንመረምር ተገደናል ። አቤል ከዐይን ፍቅር ወደ ተግባራዊ ፍቅር ለመሸጋገር ለምን አልቻለም ? የትዕግሥት መልክ ወይም ቁመና እንዴት ሳበው ? መውደዱን ከሰው በመደበቅ ለምን ይሠቃያል ? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ተመርኩዘን ጥናቱን አካሔድን ። እንደሚታወቀው ፥ የሳይኮሎጂ ጥናት ሁለገብ ነው ። አንድና ሁለት ሰው ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ አካባቢው በመተባበር የሚሠራው ሥራ ነው ። በመሆኑም አቤል በዩኒቨርስቲ ሕይወቱ በቅርብ የሚያውቁትንና ጎንደር ውስጥ እሱ ባደገበት አካባቢ የሚኖሩትን ሰዎች በማፈላለግ አንዳንድ መረጃዎች ለማግኘት ችለናል ። በተለይም ደግሞ አቤል አንድ ቀን ብቻ አብሮአት ካደረው ሴትኛ አዳሪ ብዙ ፍንጮች አግኝተናል ። ”

እስክንድር በሐሳቡ ብርቅነሽ ድቅን አለችበት ። አቤል ምስጢሬ ብሎ ያጫወታትን ሁሉ ፥ “ውይ ፥ ምስኪን የሆነ ልጅ ! ምንም አያውቅም‘ኮ ! ” እያለች ፥ ከንፈሯን እየመጠጠች ለቢልልኝ ስትዘከዝክላቸው ታየችው ። ‘ ለመሆኑ ፥ ክብረ ንጽሕናውን መውሰዷንስ ነግራቸው ይሆን ? ’ ሲል አሰበ ።

“ የአቤልን የአካዳሚክ ሕይወት ስናጠና ፥ በትዕግሥት መልክ እስከ ተማረከባት ጊዜ ድረስ በጣም ጎበዝ ተማሪ

ሆኖ እናገኘዋለን ። ከትምህርቱ ውጭ ብዙ ማኅበራዊ ግን
ኙነት የለውም ። ከመረጃዎቻችን መገምገም እንደ ቻልነ
ውም ከትዕግሥት በፊት ሴት ወዶ አያውቅም ። ይህ ማኅ
በራዊ ልምድ ማጣት አቤል በያዘው የዐይን ፍቅር አጥብቆ
እንዲሠቃይ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ነው የሚል ግምት
አለን ። የአቤል ችግሩ የወደዳትን ልጅ እንዴት ብሎ መቅ
ረብና ማነጋገር እንደሚችል አለማወቁ ነው ።

"ከጓደኞቹ ወይም የቅርቡ ከሆኑ ሰዎች ለችግሩ ዘዴ እን
ዲያገኝ ደግሞ የልቡን አፍረጥርጦ ለሰዎች ማማከሩን አልታ
ደለውም ። ግልጽ የሆነ ጸባይ የለውም ። በራሱ ላይ ከፍ ያለ
መተማመን ስላለው ማንኛውንም ችግር በግሉ የሚወጣው
የተሳሳተ እምነት ያሳደረበት በአካዳሚክ ሕይወቱ የተደነቀ
ጭንቅላት መያዙ ነው ። ነገር ግን የአካዳሚክ ጉብዝናና ማኅ
በራዊ ችግርን የመቋቋም ችሎታ የተለያዩ ነገሮች ናቸው ።
እንዲያውም በማኅበረሰብ ውስጥ የሚገጥሙዋቸውን ቀላል
ችግሮች መቋቋም አቅቷቸው ፣ ከራሳቸው ጋር ከሚጣሉት
ውስጥ አብዛኞቹ በአካዳሚክ ሕይወታቸው የተደነቀ ጭን
ቅላት ያላቸው ናቸው ።

" ፍቅር ማኅበራዊ ነው ። በተለይ በስሜት ውስጥ
እድገና ዕድሜውን ጠብቆ ለሚከሠተው የሁለቱ ጾታዎች
ፍቅር የተዘጋጀ ሥፍራ በውስጣችን አለ ። ይህ ስፍራ በአ
ንድ ወቅት የግድ ፍቅር ሊሰፍርበት ይገባል ። አለዚያ ርካታ
አይኖርም ። ይህን ስሜት ጨቁኖና በግል አፍኖ ውስጥ
ውስጡን መሠቃየት ትርፉ የአቤል ዐይነት መድኃኒት
አልባ በሽታ ነው ።

" አቤል ፍቅሩን አፍኖ መሠቃየቱ አካባቢው የፈጠረ
በት በሽታ ነው ። ተወልዶ ያደገው የሴትና የወንድ ፍቅር
በምስጢር እንጂ በግልጽ ማድረግ በሚያስነውርበት አካባቢ
ነው ። በአቤል እምነት ስላፈቀራት ሴት በግልጽ ማውራት
አሳፋሪ የሆነበት ይህ የባህል ተጽዕኖ በአእምሮው ውስጥ
ተቀርጾ ስላደገ ነው ። ደረጃው እድጎ አቤልን ለሥቃይ ከመ
ዳረጉ በስተቀር ይህ ዐይነቱ ሕመም በብዙዎቻችን ውስጥ
ያለ ነው ። አብዛኞዎቻችን ለወደድነው ሰው ቀጥተኛና
ግልጽ አይደለንም ።



" ሕመሙ በአቤል ላይ ሊጠነክርበት የቻለው ፍቅሩ
ከዐይን ባለማለፉ ነው የሚል ግምት አለን ። የዐይን ፍቅር
የሚጠነክርበት ምክንያት የውጭውን ወይም ያንጓውን
ክፍል ብቻ ስለሚወድ ነው ። ተቀራርቦ ውስጣዊ ገጽታዎ
ችን የሚተያዩበት አፍላ ፍቅር የሕመም ኃይሉ ሊቀንስ ይች
ላል ፤ ምክንያቱም በሰዎች መልክም ሆነ ባህርይ ፍጹምነት
የለምና ነው ። ለዐይን ፍቅር አቤል የመጀመሪያ ሰው አይ
ደለም ። ችግራቸው እድጎ እንዲህ አደባባይ ባይወጣም የዚህ
በሽታ ምርኮኞች ጥቂት አይደሉም ። መልካሙ ተበጀ ፣
" ሰላምታ አልሰጠኋት ፣ አላነጋገርኳት ፣ በዐይን ብቻ እያ
የሁ አንድ ዓመት ወደድኳት " እያለ የሚጫወተው ዘፈን
በብዙ ሰዎች መወደዱና በዘፈን ምርጫ ፕሮግራም በተደጋ
ጋሚ መቅረቡ ፣ ችግሩ በጥቂት ሰዎች ብቻ ያልተወሰነ መሆኑን
ያስገነዝበናል ። "

ቢልልኝ ንግግራቸውን አቋርጠው ለጥያቄ ፋታ ሰጡ ።
ነገር ግን ሁሉም በተመሳሳይ ከማዳመጥ በቀር ለጥያቄ እጁን
ያወጣ አልተገኘም ።

" መልካም ! " ሲሉ ቀጠሉ ቢልልኝ ፤ " የአቤል ፍቅር
ከዐይን ያላለፈበትንና ስሜቱን ደብቆ በግሉ የሚሠቃይባ
ቸውን ምክንያቶች በመጠኑ አይተናል ። እስቲ ደግሞ የት
ዕግሥት መልክ ወይም ቁመና አቤልን እንዴት ሳበው ?
ወይም ትዕግሥት አቤል ዓይን ውስጥ እንዴት ልትገባ
ቻለች ? የሚለውን ነጥብ እናንሣ ። ለዚህ ጥናት እንዲረዳን
የትዕግሥትን ፎቶግራፍ ወስደን ከአቤል የሕይወት ታሪክ
ጋር ለማስተያየት ሞክረን ነበር ። ሆኖም ፣ በሀገራችን የሥነ
ልቡና ጥናት አሁን ካለበት ዝቅተኛ ደረጃና የኢኮኖሚ
ችግር አንጻር ፣ አቤል ከጎንደር ሕይወቱ ጀምሮ የተቀራ
ረባቸው ዋና ዋና የሴት ምስሎች ማግኘት አስቸጋሪ ሆኖ
ብናል ። በጎንደር ውስጥ አንድ ዋርካ ሥር አዘውትረው
ይገናኙ የነበሩ ሁለት ፍቅረኞች በአቤል የልጅነት ጭንቅላት
ው ስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዘው ይገኛሉ ። ምናልባትም የል
ጅቷ መልክ ወይም ቁመና ከአሁኗ ትዕግሥት ጋር የሚመሳ
ሰልበት አለ የሚል ግምት አለን ።

“ አቤል አንድ ቀን አብሯት ላደረው ሴትኛ አዳሪ
እንዳጫወታት ከሆነ ፣ ትዕግሥትን ከዱሮ ጀምሮ የሚያው
ቃት ይመስለዋል ። ነገር ግን አቤልና ትዕግሥት በተለያየ
ክፍለ ሀገር ስላደጉ፣የቆየ ትውውቅ ሊኖራቸው አይችልም ።
ቁም ነገሩ ፣የእሷን የመሰለ መልክ ከልጅነቱ ጀምሮ ሳያስበው
ጭንቅላቱ ውስጥ ተቀርጾበታል ማለት ነው ። ፍሮይድ እን
ደሚለው ፍቅር የሚጀምረው በልጅነት ነው ። በልጅነታ
ችን የምናፈቅረውና የምንፈልገው ሰው በጭንቅላታችን
ውስጥ ተደብቆ አድጎ ነው - በጉልምስናችን ጊዜ ምርጫችን
የሚሆነው ። የመልክ ወይም የውበት ማነጻጸሪያችንም የሚ
መሠረተው ባደግንበት አካባቢ ዓይነ ነው ። በሀገራችን
በተዘዋዋሪም ቢሆን ይህን ሐቅ የሚያንጸባርቁ አንዳንድ
አባባሎች አሉ ። ለምሳሌም ፣ ‘ ባልና ሚስት ከአንድ ውሃ
ይቀዳሉ ’ ሲባል በሁለቱም ውስጥ ተቀርጾ ያደገና ከተገ
ናኙ በኋላ የዳበረ ተመሳሳይ ስሜትና ምርጫ መኖሩን ያሳ
ያል ። ሌላው ደግሞ ፣ ‘ እናትህን የመሰለች እስከታገኝ
ሚስት አታገባም ’ የሚለውም አነጋገር የሚያሳየን የው
በት ማነጻጸሪያዎቻችን ከልጅነት ጀምሮ ጭንቅላታችን
ውስጥ የሚቀረጹት ወላጆቻችን ወይም ሌሎች በአካባቢው
በቅርብ የምናገኛቸው ሰዎች መሆናቸውን ነው ።

“ ጀርመናዊው ፈላስፋ ሾፐንሀወር የፍቅረኛ ምርጫን
በሚመለከት እንዲህ ብሎ ነበር ‘ ለፍቅር ምክንያት ከሚ
ሆነው ነገር ዘጠኝ አሥረኛው በአፍቃሪው ውስጥ ያለ ነው ።
አንድ አሥረኛው ምናልባት በተፈቃሪው ላይ ይኖር ይሆ
ናል ። ’ ይህም የሚያሳየን አንድ ሰው አፍቅሮ የሚመር
ጠው ራሱ ወይም በውስጡ ያለውን ስሜት እንጂ ከውጭ
አለመሆኑን ነው ። ለማንኛውም ይህ የአፈቃቀር ሁኔታ
ለእኛ እንጂ ለአቤል ችግር የለውም ።

“ ዐይን አይከለከልም ፣ አቤል አይቷል ። መውደድ
አይከለከልም ፣ ያያትን ወዷል ። ነገር ግን ፣ ፍቅሩ በዐይን
በመወሰኑ ፣ ማስደሰቱ ቀርቶ ትርፉ ሕመም ሆኖበታል ።
እና አሁን እንዴት እንርዳው ነው ጥያቄው ። ዮናታን
አቤልን ለመርዳት በግላቸው ብዙ ጥረዋል ። ከትዕግሥት
ጋር አሁን ያለበት ሁኔታ ጤናማ መልክ እንዲይዝ ለማድረግ
ከተቻለ እኛም ከመርዳት ወደኋላ አንልም ። ሆኖም በትም



ህርቱ ረገድ ለሚኖረው ችግር የአካዳሚክ ኮሚሽኑን ርዳታ
እንጠብቃለን ። አቤል በልጅቷ ፍቅር ከተጠመደበት ጊዜ
ጀምሮ ፣ ‘ ትምህርቱ ላይ በጤናማ አዕምሮ ባለመቀመጡ
በርካታ ማስረጃዎች አሉ ። ምግብ አዳራሽ ውስጥ ከተማሪው
መሐል ወድቆ ታሟል ፤ በአእምሮ ንክነት ሳይኪያትሪስት
ድረስ ተወስዶ ታክሟል ። እኚህንና የመሳሰሉትን ማስረ
ጃዎች በመደገፍ አቤል በዚህ ሴሚስተር የተከታተላቸው
ኮርሶች ተሰርዘውለት በሚቀጥለው ዓመት እንደገና እንዲጀ
ምራቸው የአካዳሚክ ኮሚሽኑን ፈቃድ እንጠይቃለን ።

“ በእኛ በኩል ያለው ዝግጅት ይኸው ነው ። አስተያ
የትም ሆነ ጥያቄ ካለ መድረኩን ለሌሎች እለቃለሁ ። ”

ቢልልኝ ጨርሰው ከተቀመጡ በኋላ ፣ ለተወሰኑ ደቂቃ
ዎች ያህል ከጎን ለጎን መወያየት ያለፈ ጥያቄ አልነበረም ።
ዮናታን ተነሥተው አሁን አቤል ያለበትን ሁኔታና ከእሳቸው
ጋር ለተወሰነ ጊዜ እንዲኖር መወሰናቸውን ለስብሰባው
ገለጹ ። ይህ ሁኔታ የብዙዎቹን ስሜት ለእርዳታ ገፋፍቶ
ነበር ። ዮናታንን ተከትሎ አንድ ሌላ ሰው ለመናገር ተነሣ ።

“ ትንሽ ነገር እንድናገር ይፈቀድልኝ ። በእውነት
ይህ ጉዳይ አትኩሮት ተሰጥቶት ለዚህ መድረክ መቅረቡ
ደስ ያሰኛል ። እኔ እስከማውቀው ድረስ ኀበዝ ተማሪዎቻችን
በፍቅርም ሆነ በሌላ ማኅበራዊ ችግር እየተደናቀፉ ትምህ
ርታቸውን ሲያቋርጡ እስካሁን ዩኒቨርስቲያችን ብዙም
ትኩረት አልሰጣቸውም ። አንድ ተማሪ ያፈቀራት ልጅ
ገድሎ ጓደኛውንም ለመግደል ሲፈልግ ፣ ሌላው ሲያብድ ፣
የሥነ - ልቡና ጥናት መሰሎችም ሆኑ ዩኒቨርስቲው በቸልታ
ነው የተመለከቱት ። ወይም ድርጊቶች ከተከናወኑ በኋላ
ዜናውን ከማዳነቁ ላይ ነው የተተኮረው ። ለመሆኑ ፣ ኀበዝ
ተማሪያችን በትምህርቱ ሲደክምና ደረጃው ሲቀንስ ፣ ያገኘ
ውን ስጥተን ባወጣ ያውጣህ ከማለት በቀር ተማሪውን በግል
ጠርተን ለማጤን ወይም ችግሩን ለማማከር የሞከርን ስን
ቶቻችን ነን ? ይህ ለማንም መምህር የሚከብድ ርዳታ አይ
ደለም ። የለም ! የሚያሳዝን ቸልተኝነት ያለብን ይመስለ
ኛል ። አሁን ግን መልካም አጀማመር ነው የታየው ። እንግ

ፋብት እላለሁ ። እኔም ማንኛውንም ዐቅሜ የሚፈቅደውን ርዳታ ለማድረግ ከጎናችሁ እቆማለሁ ።”

ሰውየው ከኋላ ስለነበር፣ዮናታን ዘወር ብለው በአድናቆት ተመለከቱት ። እንግዳ አልነበረም ። እዚያው ግቢ የታሪክ መምህር ነው ። ‘ወይ ልብ ለልብ አለመተዋወቅ !’ አሉ ዮናታን በሐሳባቸው ።

ቢልልኝ የሰውየው ሐሳብ የግድ እንዲናገሩ ገፋፋቸው ። “ መልካም ነው ። ድጋፍህን ተቀብለናል ። ሆኖም እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት የእኛ ዓላማ የሚያተኩረው ግለሰቦችን በማስታመም ላይ ሳይሆን ችግራቸውን ወስደን አጠቃላይ መፍትሔ ከመፈለጉ ላይ ነው ። ይህ ደግሞ በዩኒቨርስቲያችን ውስጥ ብቻ ሳይሆን ፤ ከዚህ ውጭም መጠናትና መታሰብ ያለበት ነገር ነው ። የዩኒቨርስቲው አባላት ከማኅበረሰቡ የወጡ ናቸው ። ችግሩንም ይዘው የሚመጡት ከማኅበረሰቡ ነው ። ለምሳሌ ፤ በየአካባቢውና በየትምህርት ቤቱ ፍቅር በማኅበራዊ ኑሮ ክፍልነቱ ግልጽ ተደርጎ ትምህርት ቢሰጥበት ፣ ሁለቱም ጾታዎች መፋቀሪያ ጊዜያቸው ላይ ሲደርሱ እንዲህ ዐይነት ችግር አይገጥማቸውም ። ግልጽና ጤናማ ዜጋ ለማፍራት ከአካባቢው ከሥር ከመሠረቱ ነው መኮትኮት ያለበት ። እናም ኋላቀር አስተሳሰብ ከፈጠረብን ችግር ለመላቀቅ የሁላችንም ጥሪ የሚያተኩረው የባህል አብዮት ላይ ነው ። ”

ስብሰባው እንዳለቀ፣ዮናታን የቸኮሉት ይህን መልካም ዜና ለሚስታቸው ለማብሠር ነበር ። ስብሰባው በጥሩ ሁኔታ ማለቁ ብቻ ሳይሆን፣ከስብሰባው ውጭ በዮናታን ጥሪት የተደነቁ ሰዎች አቤልን ለመርዳት ያላቸውን በጎ ፈቃድ ሲገልጹላቸው ደስታቸው ገደብ አጣ ። የአቤልን የትምህርት ጉብዝና ያውቁ የነበሩ ሰዎች፣አቤል ዮናታን ቤት መሆኑ ከተገለጸላቸው በኋላ ፤ ትምህርቱን እንደገና እስኪጀምር ድረስ እንደ የዐቅማቸው ገንዘብ በማዋጣት እንደሚተባበሯቸው ነው-የነገሩዋቸው ።

“ ይኸኛውን ርምጃችንን በጥሩ ሁኔታ ተወጥተነዋል ” አሉት ዮናታን እስክንድርን ። “ የሚቀጥለው ጉዳይ አቤልን ከትዕግሥት ጋር ማገናኘቱ ወይም ማለያየቱ ነው ። አንድም በጥሩ መንፈስ ልቡ ውስጥ እንድትታሰብ ማድረግ ፤ ካልሆነም ከልቡ ውስጥ ፈንቅሎ ማውጣት ! ”

እስክንድር ራሱ ይህን ጉዳይ እያሰበበት ነበር ። ስብሰባው እንዳለቀ ፣ ዮናታን ሁኔታውን ለሚስታቸው ለማብሠር ስሜታቸው ሲቻኮል ፣ የእሱ ስሜት ደግሞ ዘሎ ያረፈው ትዕግሥት ላይ ነበር ። አፍ አውጥታ ስለአቤል ከጠየቀችው ጊዜ ጀምሮ፣እኒህ የዐይን ፍቅረኞች የሚቀራረቡት የተስፋ ጭላንጭል በልቡ ውስጥ እየፈነጠቀ ነበር ። እናም ለትዕግሥት ስለ አቤል ለማጫወት ወይም እሷ ስለ አቤል ያላትን ጥልቅ ስሜት ለመስማት አጋጣሚ ነበር የሚጠብቀው ።

“ አቤልና ትዕግሥትን ማገናኘት ነው እንጂ፣ ማለያየቱ ምን ሲደረግ ይታሰባል ? ” አላቸው እስክንድር ፣ ፈገግ ብሎ ።

“ ለሕይወቱ እንቅፋት ከሆነችበት አራርቆ እንዲረሳት ማድረጉ ይመረጣል ብዬ ነዋ ! ” አሉ ዮናታን ፣ ግራ በተጋባ ስሜት ።

“ እዬዬ ! ልቡ ውስጥ ገብታ ካደገች በኋላ መፈንቀሉ አስቸጋሪ ነው ። ለጊዜው ርቆአት ሊረሳት ቢሞክርም ወደ ዩኒቨርስቲ በሚመለስበት ጊዜ፣ ሲያያት ቁስሉ የሚቀሰቀስበት ይመስለኛል ። የአፍላ ፍቅርን ዛፍ ከሥሩ መቁረጥ የሚቻል አይመስለኝም ። ”

“ ታዲያ ምን ይሻላል ? ” አሉት ዮናታን በተጨነቀ ስሜት ።

“ ሁለቱን አገናኝተን ፣ ፍቅራቸው ከዐይን ተሻግሮ በቅርብ እንዲተሳሰሩ ማድረግ ነዋ ! ”

“ ከተቻለማ ጥሩውም መንገድ እሱ ነበር ። ”

“ አይጠራጠሩ ! ” ሲላቸው ፣ የተማመነበት ነገር ምን እንደሆነ ለራሱም በደንብ ግልጽ ሆኖ አልታወቀውም ነበር ።

ዮናታን ቤታቸው ሲደርሱ፥ሞኒካ የስብሰባውን ሁኔታ ለመስማት ጓጉታ በሕንፃው መናፈሻ በኩል ቁልቁል እየተመለከተች መምጫቸውን በመጠባበቅ ላይ ነበረች ።

" እንዴት ነው ? " አለቻቸው ፥ ከፊቷ ላይ የማይጠፋ ፈገግታዋን ብልጭ አድርጋ ።

" ደስ የሚያሰኝ ስብሰባ ነበር ። በብዙ ሰዎች ላይ ቀና ስሜት አሳድረናል " አሏት ፥ እጅዋን ይዘው ወደ ውስጥ እየገቡ ። " ጥናቱንም ቢልልኝ በጥሩ መልክ አቅርበውታል ። የጥናቱን ጽሑፍ ከእሳቸው ተውሼ ሰሞኑን አመጣልሻለሁ ። "

ሞኒካ ስብሰባው ላይ ለመገኘትና በአቤል ላይ የተካሔደውን ጥናት ለማዳመጥ ከፍተኛ ጉጉት ነበራት ። ጥናቱ የቀረበው በአማርኛ ስለ ነበር በደንብ የማትሰማው ቋንቋ ሆኖባት ነው የቀረችው ።

" አካዳሚክ ኮሚሽኑስ ምን አለ ? " ስትል ጠየቀቻቸው ።

" የእነሱ መደበኛ ስብሰባ ገና ከአራት ቀን በኋላ ነው ። ሆኖም ስብሰባችን ላይ የነበሩት የኮሚሽኑ አባላት በግል ተስፋ ሰጥተውኛል ። እና ጥሩ ውጤት እጠብቃለሁ ። "

ዮናታን ከሚስታቸው ጋር እያወሩ ልባቸው አቤልን ለማየት ጓጉቶ ነበር ። ሳሎን ውስጥ ሲያጡት የት እንዳለ ለማወቅ ሞኒካን መጠየቅ አላስፈለጋቸውም ። በቀጥታ ወደ መጻሕፍት ክፍላቸው ሔዱ ። በሩን በዝግታ ከፍተው ሲገቡ፥አቤል በሚያነበው መጽሐፍ ክፉኛ ተመስጦ አገኙት ። ሊረብሹት አልፈለጉም ። በሩን በዝግታ ዘግተው ለመመለስ ቢያስቡም እጃቸው የበሩን እጀታ መንተት አልቻለም ። ለአቤል አንዳች ነገር ሊነግሩት ፈለጉ ። ግን ምን እንደሚነግሩት ወይም ደስታቸውን እንዴት እንደሚገልጹለት እያውቁም ነበር። አቤል በእሱ ጉዳይ ስብሰባ መካሔዱን እያውቅም ። ጉዳዩ ክብደት ተሰጥቶት አደባባይ መቅረቡ በአንድ በኩል ሊያስደስተው ቢችልም ፥ በሌላ በኩል ደግሞ የሚደብቀው የዐይን ፍቅር መጋለጡ ስሜቱን ሊጎዳው ስለሚችል፥ይህን በማመዛዘን ዮናታን ሆነ ብለው ነበር ያልነገ



ሩት ። አሁንም ይህን ሊነግሩት አልፈለጉም፣። እንዲሁ ብቻ በፈገግታ የደስታ ስሜታቸውን ሊያስተላልፉለት አሰቡ ።

ወደ ውስጥ የጫማቸው ድምፅ አቤልን ከተመሰጠበት አባነነውና ካቀረቀረበት መጽሐፍ ቀና አለ ። ፈገግታቸውን ሲያይ ፥ ምን አገኙ ይሆን ? ብሎ አልተደነቀም ። ንባብ ላይ ተቀምጦ በማግኘታቸው የተደሰቱበት መሰለው ።

" እንደምን ውለሃል ? " አሉት ፥ እንዲህ የሳበው መጽሐፍ ምን እንደሆነ ለማወቅ ዐይናቸውን ወደ ርዕሱ እየወረወሩ ።

" ደኅና ፥ ሲገቡ አልሰማሁዎትምኮ " አላቸው ፥ የደረሰበት ገጽ እንዳይጠፋው ማዕዘኑ ላይ እያጠፈ ።

የሚያነበው " ማን አጌንስት ሂምሰልፍ ! " " ሰው ራሱን ሲጻረር ! " የሚለው የዶክተር ሜኔንገር መጽሐፍ ነበር ። ዮናታን ይህን አርዕስት ሲያዩ ደነገጡ ። ካልጠፋ መጽሐፍ ይኸን ለምን መረጠው ? የሚል ጥርጣሬ አደረባቸው፤ፈገግታቸው በአንድ አፍታ ጠፋ ። ፈጥነው ሊጠይቁት ግን አልደፈሩም ። ከውጭ ይዘውት የመጡት የደስታ ስሜት ከውስጥ ጥቀርሻ ሲለብስ ተሰማቸው ።

" ወደ ውጭ ወጣ ብለን እንናፈስ ? ዛሬ ንባብ ላይ ብዙ የቆየህ ይመስለኛል " አሉት ፥ ስሜቱ በመጥፎ ነገር ተወጥሮ ከሆነም ወጣ ብሎ መናፈሱ ይሻለዋል በሚል ግምት ።

" በደስታ ! " አላቸው ፥ ከተቀመጠበት እየተንጠራራ ።

አመላለሱም ሆነ የፊቱ ብርሃን ከውስጡ መጥፎ ስሜት የወጠረው ሰው አይመስልም ። ዮናታን በግምታቸው ግራ ተጋቡ ።

" ሊብሊንግ ፥ ሸርጥሽን አውልቂና ወጣ እንበል " አሏት ሚስታቸውን ፥ ወደ ሳሎኑ ተመልሰው ።

ሞኒካ ቤት ውስጥ ከሆነች ከወገቧ ነጭ ሸርጥ አይጠፋም ።

" አቤልስ ይወጣል ? " አለቻቸው ፤ ፈቃደኛነቱን ለማረጋገጥ ።

" አዎ ፤ እወጣለሁ ብሏል " አሏትና ፤ ወደ ጆሮዋ ጠጋ ብለው ፤ " የዛሬ ውሎው እንዴት ነው ? " አሏት ። የመጽሐፉ አርዕስት እየከነከናቸው ነበር ።

" ደኅና ነው የዋለው ። እንዲያውም ንባብ ከመጀመሩ በፊት እሱ ባደገበት አካባቢ ያለውን የጋብቻ ሥነ - ሥርዓት ሲያጫውተኝ ነበር " አለቻቸው ፤ ሽርጢን እየፈታች ።

ዮናታን ውጭ ውለው ቤት ሲገቡ ፤ ስለ አቤል ሁኔታ መጠየቅ ልማዳቸው ነበር ። አቤልም ዮናታን ቤት መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ያሳየው ለውጥ ቀላል አልነበረም ። አብሯቸው ሲኖር ሳምንት ሆኖታል ። ከእራሱ ጋር መታረቅ ጀምሯል ። ለውጡ የሞኒካ የድካም ውጤት ነው ማለት ይቻላል ።

ለመጀመሪያው ሁለት ቀን አቤል ራሱን ገዝቶ ቤት ውስጥ መቀመጡ በጣም አስቸግሮት ነበር ። ትዕግሥት በሐሳቡ እየመጣችበት ብረር ብረር ይለው ነበር ። ሲጠላው የነበረው ዩኒቨርስቲ ይናፍቀዋል ። ትንሽም ቀለል የሚለው እስክንድር መጥቶ አጫውቶት ሲሔድ ነበር ።

ዮናታንና ሚስታቸውም ይህን ችግሩን ሳይረዱለት አልቀሩም ። ሐሳቡን ከትዕግሥትም ሆነ ከሌላ መጥፎ ስሜት ለማዘናጋት የተጠቀሙበት ዘዴ መንፈሱን በሥራ መወጠር ነበር ። ለቀን ተቀን እንቅስቃሴው ፕሮግራም አውጥተውለታል ። ሞኒካ ምግብ በምታበስልበት ሰዓት አብሯት ሆኖ የምግብ አሠራሯን እያጠና በአንዳንድ ማኅበራዊ አርዕስቶች ላይ ይወያያሉ ። በቀን የተወሰነ ሰዓት እሷ ጀርመንኛ ታስተምረዋለች ። እሱም በፊንታው ለተወሰነ ሰዓት አማርኛ ያስተምራታል ። ይህ አቤል ከመምጣቱ በፊት የዮናታን ሥራ ነበር ። ስለዚህ ማታ ማታ ሞኒካ ቀን የተማረቻቸውን አንዳንድ አዳዲስ የአማርኛ ቃላት ስትናገር፤ ዮናታን ወደ አቤል እየመተለከቱ ፤ " ጥሩ ረዳት አገኘሁ ። እንዲያው ከኔ የተሻለ ዘዴ ሳይኖርህ አይቀርም " በማለት ይክቡታል ። በመጀመሪያ ለንባብ የተመ



ደበለት የተወሰነ ሰዓት ነበረው ። ውሎ ሲያድር ወደ ማንበቡ ፍቅር ሲመለስ ግን፤ለንባብ ከተቀመጠበት ስፍራ የሚነሣው በቀስቃሽ ሆነ ። ከንባብ ውጭ ለመዝናናት ያህል በቤት ውስጥ የሚያገኛቸውን የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ሥዕላዊ መግለጫ የያዙ መጻሕፍት ማገላበጡ በመንፈሱ ውስጥ የጥሩ ሕይወት ስሜት ያሳድርበት ነበር ። የሀገር ውስጥና የውጭ ሙዚቃ በሙሉ ጆሮው ሰምቶ ለማድነቅ የቻለው በዚሁ ሳምንት ውስጥ ነው ። ትርጉሙም ሆነ ጣዕሙ ሊገባው ያልቻለው፤ዮናታን የሚያደንቁትና በተመስጦ የሚያደምጡት፤የእነ ቫግነርና ቤትሆቫን ክላሲካል ሙዚቃ ነው ። ቤት ውስጥ ሙዚቃ ማዳመጡ ቢያስደስተውም ፤ አንዳንዴ ትካዜ ስለሚጫነው ፤ ለመቆጠብ ወይም ብቸኝነት በማያጠቃው ሰዓት ብቻ ለማዳመጥ ተገዶ ነበር ።

ቀን በዚህ ዐይነት ውሎ ፤ ወደ ማታ ላይ ሦስቱም ነፋስ ለመቀበል ወደ ከተማው ጸጥታማ ቦታዎች ብቅ ይላሉ ። አሰልሠው ሲኒማ ይገባሉ ። ይህን የመሰለው የሕይወት እንቅስቃሴ አቤልን ከብቸኝነት ስሜቱ በማዘናጋት ፤ ሐሳቡ አንድ ነገር ላይ ብቻ በማተኮር እንዳይሠቃይ ከፋፍሎለታል ። ያም ሆኖ ትዕግሥትን እያሰበ ሳይጨነቅ አያድርም ። ግን ጭንቀቱ እንደ ቀድሞው አልነበረም ። በሥራ በተወጠረ አእምሮ ወይም ደክሞ እንቅልፍ በፈለገ ጭንቅላት ስለሆነ የሚያስባት ፤ ያን ያህል አይረብሽም ።

አቤል ከብርቅነሽ ቀጥሎ በሕይወቱ የገጠመችው ግልጽ ሴት ሞኒካ ነች ። በአንድ ምሽት ዕድሜም ቢሆን የብርቅነሽ ትሑትና ግልጽ ተፈጥሮ በልቡ ተቀርጿል ። ምናልባትም የብርቅነሽ ግልጽነት ከማይምነቷ ጋር የተያያዘ የልብ ክፍትነትና የጥሬነት ውጤት ሊሆን ይችላል ። የሞኒካ ግልጽነት ግን ምሁራዊ ጥልቅ ትርጉምና ድምቀት አለው ። ከአኳኋኗ መረዳት እንደሚቻለው ፤ " የምንፈጽመው ጥሩም ሆነ መጥፎ ነገር የህልውናችን ነጸብራቅ ነው ፤ ስለሆነም እኛነታችንን ደብቀን መሠቃየት የለብንም ፤ መጥፎ የምንለውን አምቀን ጥሩ የምንለውን ብቻ የምንተነፍስ ከሆነ፤ውስጣችን ገምቶ ደማችን ይደፈርሳል " የምትል ትመስላለች ። አቤል በቀላሉ ነው የተግባባት ። አንዳንዴ ፤ በንጹሕ ጨዋታዋ ሲመሰጥ ፤ ስሜቱን ደብቆ የሚወጣጠር ተፈጥሮውን

ይረግማል ። እያደር ራሱን መደበቅ ከማይችልበት ደረጃ እየ
ደረሰ ነበር ። የእሷ ግልጽነትና ማብቂያ የሌለው ጣፋጭ
መስተንግዶ ሳይወድ በግድ ልቡን እየከፈተበት መጥቷል ።

በተለይ አንድ ቀን ሞኒካ ከዮናታን ጋር ስላላት ግንኙነት
ግልጽ ሆና ያጫወተችው ነገር ጭንቅላቱ ውስጥ ተቀርጾ
ቀርቷል ። ዮናታን ለንባብም ሆነ ለጥናት ሥራ ቤታቸው
ውስጥ አንዴ ከተቀመጡ ወጣ ብሎ የመዝናናቱ ነገር አይ
ታያቸውም ። የሕይወታቸውን አብዛኛውን ክፍል ለአካዳ
ሚክ ጥረት ስለሰጡ ፥ ደስታ የሚሰጣቸው ከጠረጴዛ ተጣ
ብቆ መዋሉ ነበር ። ሞኒካ ደግሞ መጫወት ትፈልጋለች ፤
መዝናናት ትፈልጋለች ፤ ለውጥ ያምራታል ። ይህ ልዩነት
ለተወሰነ ዓመታት አብሮአቸው ቆይቷል ። ከዚህ በላይ የከ
በደው ልዩነት ደግሞ በግብረሥጋ ግንኙነት ረገድ ያለው
ነበር ። የዮናታን የጠነከረ የአካዳሚክ ሕይወትና የዕድሜ
ያቸው መግፋት የወሲብ ፍላጎታቸውን ስለሚያደክምባቸው፥
ጥማታቸው ከሞኒካ ጋር እኩል አይሆንም ። ቀዝቃዛ ይሆኑ
ባታል ። አንዴ ሞኒካ መኝታዋ ውስጥ ገብታ ዮናታንን በመ
ጠበቅ ብዙ ቆየች ። በመጨረሻም በሽቃ ዕርቃኗን ከመኝ
ታዋ ወጥታ ወደ መጻሕፍት ክፍሉ ሔደች ። ዮናታን መጽሐፍ
ላይ እንዳቀረቀሩ ነበሩ ። ስሜቷ ተወጣጥሮ ቢያሠቃያትም
ጎሊናዋን ስላልሳተች ፥ እንዳትረብሻቸው ፈርታ ወደ ኋላዋ
ተመለሰች ። ነገር ግን ብሽቀቱ ልቧ ውስጥ እንደ ተቀበረ
ስለ ነበር፥ ሳሎኑ ጠረጴዛ ላይ ያገኘችውን የዕብነ በረድ የሲ
ጋራ መተርኮሻ በደመ ነፍስ አንሥታ ስትወረውር፥ የብፌ
ውን መስታወት ከሰከሰችው ። ደገመችና ብፌው ውስጥ
የነበሩትን ስኒዎች አንከታከተቻቸው ።

ዮናታን ደንግጠው ከጥናት ክፍላቸው እየሮጡ ሲደርሱ
ሚስታቸው ዕርቃኗን ተገትራ ፥ የመስታወቱ ድቃቂ መሬት
ተዘርግፎ ተመለከቱ ። ጸጉሯ ተበታትኖ ፥ ነጭ ፊቷ ፍም
መስሎ ሲያዩዋት ልዩ ፍጥረት መሰለቻቸው ። “ ምን
ሆንሽብኝ ሊቢሊንግ ? ” አሏት ። ዐይኗን ከማፍጠጥ ሌላ
ፈጥና አልመለሰችላቸውም ። የማይጠገብ ትሕትናዋን
ያህል ፥ የተናደደች እንደሆን አያድርስ ነው ። የቤት ዕቃ
አይተርፋትም ። በብሽቀት ጊዜ ሰው እንዳታስቀይም ወይም
እንዳትጎዳ የስሜት እሳቷን የምታበርደው ዕቃ በመሰባበር



ነው ። ያን ዕለት ችግሯን ለዮናታን ፍርጥርጥ አድርጋ ነገ
ረቻቸው ። ከዚያ ጊዜ በኋላ፥ ዮናታን የምሽት የንባብ ጊዜያ
ቸውን ቀይረው እሷን ቀድመው መኝታ ውስጥ እየገቡ ይጠ
ብቋት ጀመር ።

አቤል ይህን ከእሷው አፍ መስማቱ ነው ያስደነቀው ።
ድርጊቷን ስትነግረው በልጅነቱ ሴት አያቱ ፥ “ ሴት ልጅ
ካልተገረዘች ዕቃ ትሰብራለች ” የሚሉት ፈሊጣቸው ነበር
ትዝ ያለው ።

ሞኒካ ለአቤል ሌሎችም ነገሮች በግል ባጫወተችው
ቁጥር፥ በዚህ ጥቂት ቀናት ውስጥ ስሜቱ በቀላሉ ታዛዥዋ
እየሆነ መጣ ። አቤል በሞኒካ የሚደነቅበት ሌላዉ ነገር
ደግሞ፥ የቤት ውስጥ እንቅስቃሴዋ ነው ። ዐርፋ አትቀመ
ጥም ። ደስታዋ የሚመነጨው ከሥራና ሰውን ከማስደሰት
ይመስላል ።

ሞኒካ ከሀገሯ እንደ መጣች ለሁለት ዓመት ያህል በጥ
ቁር አንበሳ ሆስፒታል በነርስነት ሠርታለች። ነገር ግን፥ ከጊዜ
በኋላ የመድኃኒት ሽታ ለጤንነቷ ስላልተስማማት ፥ ይኸን
ሥራዋንለማቆም ተገደደች ። ያ ሲቀር የቤት አስተዳደር ሥራ
ኮስተር ብላ ያዘች ። ለእሷ ትልቁ ሥራዋ ምግብ ማብሰል
አይደለም ። ለቤቷ ሕይወት ለመስጠት ነው የምትደክመው ።
ለዐይን እንዳይሰለች ትጥራለች ። ጥልፍ የመሳሰሉት የእጅ
ሥራዎቿ አንድ ግድግዳ ላይ ከተወሰነ ጊዜ በላይ አይቆዩም ።
ይለዋወጣሉ ። የቤት ውስጥ የአበባ ተክሎቿን መከርከምና
ውሃ ማጠጣት ሕፃን ልጅ አቅፎ እንደሚጫወት ነው የሚያ
ስደስታት ። ከአልጋ ጀምሮ የቤት ዕቃዎች አቀማመጥ በተ
ለያየ ጊዜ ትለዋውጣለች ። የመኖሪያ ቤት ዕቃዎች አቀማመጥ
መቀያየር በነዋሪው ላይ ምን ያህል መንፈስ የማደስ ኃይል
እንዳለው ታውቃለች ። ዐይን በቀላሉ ይወዳል ፤ ዐይን በቀ
ላሉ ይጠላል ፤ ዐይን በቀላሉ ይታለላል ። ዐይን ከረካ፥ የውስጥ
ስሜት በጥላቻ አይደፈርስም ። መኖሪያ ቤቱ የሚስብ ከሆነ
ልብ ወደ ውጭ አይኮበልልም ። ይህን መመሪያዋ አድርጋ
የያዘች ትመስላለች — ሞኒካ ። ቤቱን አዘገጃጅታ ስትጨርስ
መጽሐፍ ታነባለች ። የየወቅቱን የውጭ መጽሔቶች እያነ
በበች ለዮናታን ሥራ የሚጠቅም አርዕስት ስታገኝ መርጣ

ታስቀምጥላቸዋለች ። ጀርመን ካሉት ዘመዶችዋ ጋር ደብዳቤ መጻጻፍ የሚያስደስታት ጊዜ ማሳለፊያዋ ነው ። አኗኗትላ ስትጽፍ አቤል እየገረመው ምን እንደምትጽፍ ለማወቅ ይጓጓል ።

ይህ ሁሉ የሞኒካ ሁኔታ በአቤል ላይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያሳያ ረበት የአስተሳሰብ ተጽዕኖ ቀላል እንዳልሆነ ዮናታን በሚገባ ይከታተላሉ ። ሕይወትን ከመናቅና ከመ ጥላት ሕይወትን ወደ ማድነቅ እየተሸጋገረ መሆኑን ከአን ዳንድ ድርጊቶቹና ጨዋታዎቹ ለማወቅ ችለዋል ። (ዛሬም ትንሽ ያስደነገጣቸው ይዞ ያገኙት ከወትሮው ለየት ያለ ዐይነት መጽሐፍ ነው ። )

“ መሔድ እንችላለን ” አላቸው አቤል፣ከመኝታ ክፍሉ ወደ ሳሎን ብቅ ብሎ ጸጉሩን ሲያበጣጥር ነበር የቆየው ። ዮናታንና ሚስታቸው ተሰናድተው እሱን በመጠበቅ ላይ ስለ ነበሩ፣ ወዲያው ተያይዘው ወጡ ። አቤል ፊት ላይ ከወ ትሮው ለየት ያለ ይነበብ ነበር ። ምን ተሰምቶት ይሆን ? ዮናታንና ሞኒካ ስሜቱን መጋራት ፈለጉ ። ሆኖም ደረጃውን ለመውረድ አሳንሰሩ ውስጥ እስኪገቡ ድረስ ምንም ቃል አልተነፈሱም ።

“ የዛሬው ንባብህ እንዴት ነበር ? ” ሲሉ ዮናታን ፈገግ ብለው ጠየቁት ።

“ ጥሩ ነበር ። እንዲያውም . . . ” ብሎ አቋረጠ ።

የሚቀጥለውን ለመስማት ቢጠብቁትም መልሶ ዋጠው ። መደበቅ ፈልጎ ሳይሆን እንዴት እንደሚነግራቸው ተቸግሮ ነበር ።

“ ያንን ይዘኸው የነበርከውን መጽሐፍ እንዴት ወደ ድከው ? ” ሲሉ ዮናታን ደግመው ጠየቁት ።

“ እንዳጋጣሚ መጽሐፍ ስመርጥ ነው ያገኘሁት ። ገና “ ማን አጌንስት ሂምሰልፍ” ( ‘ ሰው ራሱን ሲጻረር ’ ) የሚ ለውን አርዕስት ሐሳቤ ውስጥ “ ማን ፎር ሂምሰልፍ ” (ሰው ራሱን ሲያፈቅር ) በሚል አርዕስት የመጻፍ ስሜት



አደረብኝ ። እንዴት እንደሆን እንጃ ! ላላስበው ስሜቴን ቀሰ ቀሰብኝ ። ስለዚህ ፣ ሰው ለራሱ ወዳጅ የሚሆንበትን ሁኔታ ለመጻፍ ፣ በመጀመሪያ ሰው ለራሱ ጠላት የሆነባቸውን ሁኔታዎችና ምክንያቶች ማወቅ ይጠቅማል ብዬ ነው - እሱን በማንበብ ላይ ያለሁት ። እና እንዲያውም ከማንበብ ወደ መጻፍ ልሸጋገር ሳይሆን አይቀርም ። ”

ዮናታን ደስ አላቸው ። ከአቤል ጋር የሚያወሩት በአ ማርኛ ስለ ነበረ ፣ ለሞኒካ ተረጎሙላት ።

“ በእርግጥ ? ” አለች በእንግሊዝኛ ፣ የእሷም ደስታ ገደብ አጥቶ ዐይኖችዋን እያቁለጨለጨች ።

“ በእርግጥ ! ” በማለት አቤል ጨዋታው ውስጥ እሷም እንድትሳተፍ በእንግሊዝኛ ቀጠለ። “ በዚህ አርዕስት የመጻፍ ሐሳብ ጭንቅላቴን ወጥሮ ይዞታል ። አሁን ገና ሳልጀ ምረው ችግር የሆነብኝ የጊዜ ጉዳይ ነው ። መሠረት የሚሆኑ ኝን መጽሐፎች አንብቤ ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ያስፈልጋል ። እና ጊዜ የሚያንሰኝ መሰለኝ ። ”

ከአሳንሰሩ ወጥተው ወደ መኪናቸው አመሩ ።

“ ገድየለህም እስቲ ጀምረው ” አሉ ዮናታን ፣ የጊ ዜው ነገር አይቸግርዎ ። መቼም ይኸን ሴሚስተር ትምህርት ህን ማቋረጥህ የታወቀ ነው ። ስለዚህ እስከ አዲሱ ዓመት ድረስ ስድስት ወር ያህል ነጻ ጊዜ ይኖርሃል ። ”

በሰበቡ ትምህርቱን የማቋረጡን ውሳኔም መናገራቸው ነበር ። አቤል ግን ይህንን ቀድሞም አላጣውም ። የሁለተ ኛው ሴሚስተር ትምህርት እንደ ተጀመረ ያውቃል ። ዮናታን ቤታቸው ያመጡት እንዴ ቢሮአቸው ጠርተውት ፣ “ ትምህ ርትህን ማቋረጥ አለብህ ” ያሉትን ነገር ተግባራዊ ለማ ድረግ መሆኑ እየገባው መጥቷል ። ሆኖም ጥረታቸው ሁሌ ለእሱ ጥቅም መሆኑን በማወቁ ውሳኔአቸውን ለመቀበል በቅቷል ። ለወላጆቹ ደብዳቤ ሲጽፍ እጁን ይዞ ያስቸገረው “ ትምህርቴን ለጊዜው አቋርጬአለሁ ” የሚለው ዐረፍተ ነገር ነበር ። ሲውል ሲያድር ግን ነገሩን አቅልሎ እንዲመለከ ተው ተገዷል ።

“ ዐውቃለሁ ። ግን ስድስት ወሩም የሚበቃኝ አይመስለኝም ። አእምሮዬ የጀመረውን ሐሳብ ሳስበው ብዙ ነው ” አላቸው ።

“ አይዞህ ፤ አንተ ጽሑፉን ከጀመርክ ጊዜን ወደኋላ የሚጎትት ነገር እንፈጥራለን ” አሉት ዮናታን ፤ ደስታው ለቀልድ ጋብዞአቸው ።

አቤል ፈገግ አለ ። ጤናማና ልባዊ ፈገግታ ! የሞኒካም ፊት እንደዚያው ነበር ።

“ ዛሬ ለለውጥ ያህል ኳስ ጨዋታ ብንመለከትስ ? ” አሉ ዮናታን መኪና ውስጥ ከገቡ በኋላ ፤ የሚስታቸውንና የአቤልን ፈቃደኝነት በሚጠይቅ ድምፅ ።

ሁለቱም በፈገግታ ፈቃደኝነታቸውን ገለጹላቸው ። ዮናታንና ሞኒካ ዐልፎ ዐልፎ ኳስ ጨዋታ መመልከት ይወዳሉ ።

“ ወድያውም ፎቶግራፎችን ደርሶ እንደሆን እግረ መንገዳችንን እንጠይቅ ” አለች ሞኒካ ።

ሦስቱ አንድ ላይ ፎቶ ተነሥተው ፊልሙን ለማሳጠብ ሰጥተው ነበር ። አቤልም ይህንኑ ፎቶ አብሮ ለመላክ በማሰብ ለወላጆቹ የጻፈውን ደብዳቤ ገና አልሰደደውም ።

ፎቶው ቤት ሲጠይቁ ደርሶላቸው አገኙት ። ግሩም ሆኖ ነው የታጠበው። አቤልን ከመሐላቸው አቁመው ባልና ሚስቶቹ ትከሻውን አቅፈው ነበር የተነሡት ። በስተጀርባቸው የአትክልት ስፍራ ስለ ነበረ፣ ለፎቶው ልዩ ድምቀት ሰጥቶታል ። አቤል ፎቶውን ሲመለከት በሐሳቡ የመጡበት እናቱ ነበሩ ። ‘ ትደሰት ይሆን ? ወይስ ልጄን ቀሙኝ ብላ ትቀና ይሆን ? ’ ሲል አሰበ ።

“ ነገ ጠዋት ከደብዳቤው ጋር ወደ ወላጆቼ እልከዋለሁ ” አላቸው ፍርጥም ብሎ ።

“ ጥሩ ” አሉና ዮናታን ፤ ቦርሳቸውን አውጥተው ፤ ስማንያ ብር ቆጥረው ፤ “ ይህንንም ጨምረህ ላክላቸው ” አሉት ።



“ ምንድነው ? ” አላቸው ተደናግጦ ።

“ ገንዘብ ነዋ ! ” አለችው ሞኒካ ። ሰሞኑን ዮናታንና ሞኒካ ተመካክረው ያሰቡበት ነገር ነበር ።

አቤል መቀበሉ ከበደው ።

“ ሥራ ስትይዝ የምትከፍለው ዕዳ ነው ፣ አይዞህ ” አሉና ዮናታን ቀለዱበት ።

አቤል ምንም አልመለሰም ። ዝምታን መረጠ ። ደስታ ገደቡን ሲያልፍ በቃላት መግለጽ እንደማይቻል ገባው ። እነሱም የእሱ ዝምታ እንደ ተጋባባቸው ሁሉ ጸጥ አሉ ። ሾፌሳቸው ብቻ ማቃሰቷን አላቋረጠችም ።

አቤል ጭንቅላት ውስጥ በደስታ የታጀበ የተለያየ ሐሳብ ተፈራረቀበት ። ነገር ግን የአንዱንም ጭራ መያዝ አልቻለም — ከመኪናዋ ፍጥነት ጋር የሐሳብ ግልቢያ ብቻ !

“ ጋሽ ዮናታን ፤ ነገ ቢሮዎ ሲገቡ እስታውሰው፣ ከአሁን በፊት የሰጡሁዎትን የጥናት ጽሑፍ ወረቀቶች ያምጡልኝ ” አላቸው ሲያስብ ቆይቶ በድንገት ።

“ ለምን ፈለግካቸው? እንደ ገና እርመህ ልትሠራቸው ነው ? ” አሉት ዮናታንም ፤ አጠያየቁ ጤናማ መልክ እንዳለው በማገመት ።

“ ብቻ ያምጡልኝ ” አላቸው ፤ ‘ ሙያ በልብ ነው ’ የሚል ኩራት በያዘ ድምፅ ።

“ እሺ ፣ በደስታ ! ” አሉትና ዮናታን ፣ ትንሽ ቆይተው ፣ “ ሌላስ ከዩኒቨርስቲ የምትፈልገው ነገር የለም ? ” ሲሉ ጠየቁት ።

“ ምን ? ” አላቸው መልሶ ። ነገሩ ቶሎ አልገባውም ። ከኋላ ስለ ተቀመጠ፣ ዮናታን በመስታወቱ ውስጥ የፊቱን ለውጥ እየተመለከቱት ነበር ።

“ ከፈለግክ ትዕግሥትም ትመጣልሃለች ” አሉት በአዝጋሚ ድምፅ ። ፊቱ በመጠኑ ሲለወጥ በመስታወት ውስጥ ተመልክቱት ።

“ ምን ታረግልኛለች ? ! እሷ ጠላቴ ነች ። እሷን ማየት ካቋረጥኩ ጀምሮ አእምሮዬ በደንብ መሥራት ጀምሯል ” አላቸው በሻከረ ድምፅ ።

ዮናታን አመነቱ ። እውነት ሰላም ካገኘ፣እሷ ብትቀርበትስ ? ብለው አሰቡ ። ወዲያው ግን ከእስክንድር ጋር የተወያዩት ነገር ሐሳባቸውን አፈረሰባቸው ።

“ ትዕግሥት ፍቅርህ እንጂ ፣ ጠላትህ አይደለችም ። ጠላትህ ስለ ፍቅር ጠልቀህ እንዳታውቅ ጨቁኖ ያሳደገህ አካባቢህ ነው ” አሉት ፣ የቢልልኝ ድምፅ ጆሮአቸው ውስጥ እየደወለ ።

አቤል መጥፎም ፣ ጥሩም አልመለሰም ። አንገቱን አቀርቅሮ እንደገና ፎቶአቸውን ይመለከት ጀመር ።



# ምዕራፍ ሀያዘጠኝ

ከገና ማዕበል ያመለጠው ተማሪ፣የዩኒቨርስቲ ውስጥ ዕድሜው መራዘሙን ካረጋገጠ በኋላ መረጋጋት ይታይበታል ። የሁለተኛው ሴሚስተር ትምህርት ቢጀመርም፣ገና ሞቅ ሞቅ ባለማለቱ አንገቱን መልሶ ቀለም ላይ የደፋ ተማሪ እምብዛም ነው ። ሆኖም ፋታ ፈጥሮአቸው የነበሩት ቀልድ ፣ ትችት ፣ ውንጀላና ተረብ ተግ ብለዋል ።

ትዕግሥት ማጥናት አልጀመረችም ። የወረቀት ዘር ማየት ያስጠላት ትመስላለች ። ትምህርት ክፍሉ ውስጥ እንኳ ከመምህራኑ ገለጻ ሙሉ በሙሉ ማስታወሻ መውሰዱን ትጠራጠራለች ። ምክንያቱም አንዳንዴ ሐሳቧ እያመለጣት ወደ ውጭ መብረር ጀምሯል ፤ በግልጽ ያልተከሠተላት ስሜት ሲፈታተናት ይሰማታል ። ከውስጧ አንዳች ነገር የጎደለ ይመስላታል። ምናልባት በቢልልኝ አገላለጽ ለፍቅር የተዘጋጀው ሥፍራ ሳይሆን አይቀርም የሚረብሻት ።

አቤል ሕመሙን አጋብቶባት እንደ ሄደ ለመገመት ብዙ ጊዜ አልወሰደባትም ። መኝታ ክፍሏ መግባት መውጣቱም አስጠልቷታል ። ጸባይዋ ቢንቋሸሽም ፣ በመጠኑ ለምዳት የነበረችው ጓደኛዋ ማርታ ነበረች ። እሷ ከተባረረች ወዲህ በደንብ ቀርባ የምትጫወተው የሴት ጓደኛ አላገኘችም ። ከቤተልሔም ጋር ዐልፎ ዐልፎ ይገናኛሉ ። ሆኖም በግቢው ውስጥ የቤተልሔም ስም እየቆሸሸ ስለ መጣ፣ትዕግሥት አብራ እንዳትታማ በመፍራት ቀስ በቀስ እየራቀቻት ነበር ። አቤል ግቢውን ለቅቆ ከወጣ ወዲህ ለዐይኗ ማባረፊያ ያገኘችው ሰው እስክንድር ነው ። ሳታየው ወይም አግኝታው የተለመደውን ፣ “ ታዲያስ ፣ ታዲያስ ” ሰላምታ ሳትለዋወጥ ውላ አታውቅም ።

እስክንድርም ቢሆን፣የትዕግሥትን መግቢያና መውጫ ሰዓት ጠብቆ ነው የሚያገኛት ። ከመኝታ ክፍሉ ጠዋት

ሲወጣ በለ አቤል ሁኔታ ፍርጥርጥ አርጎ አጫውቷት መፍትሔውን እንዲወያዩበት ሊለምናት ያስብና ፣ በሚያገኛት ጊዜ ልቡ ይከዳዋል ። በዮናታን ፊት የፎከረውንና እሷን ሲያገኛት ምላሱ መተሳሰሩን ሲያመዛዝን ራሱን ታዘበው ። ‘ አቤልስ ቢደነግጥላትም ቢፈራትም ወዷት ነው ፤ እኔ ደግሞ ያሰብኩትን ልነግራት መፍራቴ ለምንድን ነው ? ’ እያለ ከራሱ ጋር መሟገቱ አልቀረም ። ግን ለእስክንድር አልታወቀውም እንጂ ፣ ስለ አቤል ጠልቆ ሳያነሳባት ከትዕግሥት ጋር ግንኙነቱን ማጠናከሩ ለዓላማው ጥሩ መንገድ አመቻችቶለት ነበር ። በአንዴ ነጥቡ ላይ ደርሶ ዱብ ዕዳ ከማውረድ ፣ ቀስ በቀስ እለማምዶ ከነጥቡ ላይ መድረሱን መልሱ የእሽታ እንዲሆን ይበልጥ ይረዳል ።

ትዕግሥትን ከአቤል ጋር ለማገናኘት አማራጭ መንገዶችን ዮናታንና ቢልልኝ ተነጋግረው ነበር ። ትዕግሥትን ድንገት ወስዶ አቤል ፊት ማቅረቡን ቢልልኝ አልደገፉትም ። ምናልባትም ካለፈው ልምዳቸው በመነሣት ሊሆን ይችላል። አንዴ እንዲሁ ተመሳሳይ ችግር የገጠመው ተማሪ የሚፈልጋትን ልጅ አቅርበው እናስተዋውቅህ ሲሉት ፣ ካልገደልኳት ብሎ የተጋበዘው ነገር ምንጊዜም አይረሳቸውም ። እና አሁን ያቀረቡት ሐሳብ በመጀመሪያ አቤል ስለ ትዕግሥት ቀና አመለካከት እንዲኖረው መኮትኮትና ፣ አጠገቡ ከመድረሷ በፊት በስልክ እንድታነጋግረው ወይም ደብዳቤ እንድትጽፍለት ማድረግ ነበር ። ደብዳቤ መጻፍዋ የተሻለ መንገድ ሆና ተመረጠ ። ይህን ለማስፈጸም በሙሉ ልብ ኃላፊነቱን የወሰደው እስክንድር ነበር ። ታዲያ አሁን ተግባሩ ላይ ሲደርስ የምን ወገቤን ያዙኝ ነው ?

ሲያምጥ ከርሞ ፣ አንድ ቀን እንደ ምንም ደፍሮ ሔደ ። ከመኝታ ክፍሏ አስጠራትና ፣ “ ለጥብቅ ጉዳይ እፈልግሻለሁ ” አላት ። በቆይታ የሚያወሩበት ቦታም ችግር ነበር ። እነትዕግሥት ቀድሞ ያጠኑበት የነበረው ከዋናው ቤተ መጻሕፍት ጀርባ ያለው ዋርካ አካባቢ ታየው ። ግን ሁለታችንን ብቻ እዚያ ዋርካ ሥር ሲያዩን ተማሪዎች ምን ይሉናል ? የሚል ሥጋት አደፈበት ። በመጨረሻም ካወጣ ካወረደ በኋላ ሌላ ቦታ በማጣቱ ፣ “ ያሉትን ይበሉ ” ብሎ ፣ ወደ ዋርካው ሥር ይዟት ሔደ ።



እንዴት እንደሚጀምርላት ግራ ገብቶት ትንሽ ተጨነቀ ። ግን ዝም ማለትም አልቻለም ። ዐይኖችዋ ውስጥ የጥያቄ ምልክቶች ተደርድረው ያየ መሰለው ።

“ ሁለታችንም ሳንጠላው የምንሸሸው አርዕስት ነው ” አላት በድንገት ።

“ ምን ? ” አለችው ፣ ነገሩ ቢገባትም ከእሱው ይምጣ በሚል ስሜት ።

የአቤልን ነገር ሁለቱ በተገናኙ ቁጥር ዳር ዳር ሳይሉ ስለማይለያዩ ፣ አሁን ስለእሱ ሊያወራት መሆኑን ትዕግሥት አላጣቸውም ። ስሜቷን ደብቃ ነው እንጂ ወሬውን ለመስማት ቸኩላለች ።

“ ስለ አቤል በደንብ ላጫውትሽ ብዬ ነው ” አላት ።

ፈቃደኛነቷን በአፏ ሳይሆን በዐይኖቿ ነው የገለጸችለት ።

አጫወታት ነው ረበሻት የሚባለው ? የለም ! ማጫወት ላይ ላዩን ሲሆን ነው ። ከሥር ከመሠረቱ ጀምሮ ልብን እያናጉ ፣ መንፈስን እያወራጩ ፣ ቁስልን እየቀሰቀሱ ፣ ስሜትን እያንገላቱ የሚናገሩት ነገር ፣ “ መረበሽ ” የሚለውን ቃል ቢይዝ ይሻላል ። እስክንድር እንደዚያ ነው ያደረገው ። ሳያስበው የእሱም ስሜት አርዕስተ - ነገሩ ውስጥ ሰምጦ እየተንገላታ ስለ አቤል የሚያውቀውን ሁሉ ነገራት ። እሷን ካየበት ዕለት ጀምሮ በግሉ የተቀበለውን ሥቃይ ፣ አሁን የት እና በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ዘረዘረላት ።

እያወራላት ገጽታዋን ገመገመ ። ከንፈሯ በቅጽበት ሲከስል ታየው ። ፊቷ በአንዴ ጠወለገ ። አዲስ ነገር ተናግሮ አልረበሻትም ። አብዛኛው የምታውቀው ነገር ነው ። አብዛኛው ከአቤል ጋር አንድ ሴሚስተር ሙሉ በዐይናቸው የተለዋወጡት የጥናት ፣ የቁጣ ፣ የሥቃይና የእልህ ድምፅ አልባ ግንኙነት ነው ።

“ ታዲያ ጥፋተኛው ማነው ? ” አለችው ፣ ንግግሩን መጨረሱን ካረጋገጠች በኋላ ።

ዐይኖችዋ ያቀረሩትን ዕንባ ሲያይ ስሜትዋ ተጋባበት ። ግን እሱ የማልቀስ ችግር አለበት ፤ ዕንባው ቶሎ አይመጣለትም ።

" ለፍርድ አስቸጋሪ ነው ። ሁለታችሁም ጥፋተኞች አይደላችሁም ። እየተፈላለጉ መራራቅን ፥ ' የፍቅር እንቆቅልሽ ' ብንለው ይሻላል " አላት ።

ዝም አለችው ። እሱም ዝም ብሎ ተመለከታት ። የአቤልን ስሜት ያደነዘዘውን የመልኳን ውበት ማጥናት ፈለገ ። ግን ከጸመነ ፊቷ ላይ ውበት ለማጥናት መሞከሩ አስቸጋሪ ሆነበት ።

በረዥሙ ተነፈሰች - የጭንቅ አተነፋፈስ ። የታባቱ ! በሥቃይ የታመቀው አየር ወጣ ።

" አሁን አንገብጋቢው ' ጥያቄ ፥ ጥፋተኛው ማነው ?' ሳይሆን ፥ ' መፍትሔው ምንድነው ?' ይመስለኛል " አላት እስክንድር ።

" ምን መፍትሔ አለው ? " አለችው ፥ ተስፋ በቆረጠ ድምፅ ።

" አለው እንጂ ። አቤል ይወድሻል ፥ ይፈልግሻል ። ማወቅ የሚፈልገው ያንቺ ምላሽ ምን እንደሆን ነው ። ካንቺ መረዳት እንደ ቻልኩት ደግሞ አንቺም ትፈልጊዋለሽ ፤ ትወጂዋለሽ ። ይህን ስሜትሽን በደብዳቤ ብትገልጪለት ችግሩ ይቃለላል ። "

" ደብዳቤ " አለችው ፥ ሳይተዋወቁ የምትጽፍለት ደብዳቤ ምን እንደሚሆን ግር ብሏት ።

" አዎ ደብዳቤ ! "

" ምን ብዬ ? "

" በቃ ፥ ለእሱ ያለሽን ስሜት ነዋ ! "

አሰበች ፤ ደብዳቤ ። አዎ ፥ ጥሩ መንገድ ነው ። ስትጽፍ አጠገቧ የምታፍረው ወይም የምትፈራው አቤል አይኖርም ። ወረቀቱ ላይ የምታስፍራቸው ቃላት ፈንቅለዋት ማልቀስ



ቢዳዳትም ማልቀስ ትችላለች ። ታዛቢ አይኖርባትም ። የምትጽፈው ነገር ከጭንቅላቷ ውስጥ እየፈለቀ አሁን አሁን አሰኛት ።

" ካልሆነም ረቂቁን እኔ ልጻፍልሽ " አላት እስክንድር ፥ ዝም ስትልበት ጊዜ የቸገራት መስሎት ።

" ግድ የለም ፤ እኔው እሞክራለሁ " አለችው ፥ በሐሳቧ የምትጽፍበትን ቦታ እየመረጠች ። ምቹ ቦታ የለም ። የመኝታ ክፍል ጓደኞቿ ከተኙ በኋላ ፥ ሌሊት ተነሥታ የመጻፍ ሐሳብ መጣላት ።

" ጥሩ እንግዲህ ፥ ጻፊና ስጪኝ ። እኔ አደርስልሻለሁ " አላት ። ፈገግ ብላ በእሺታ ራሷን ነቀነቀች ።

እስክንድር በልቡ እየቦረቀ ትዕግሥትን መኝታ ክፍሏድረስ ሸኛት ። ምን ዐይነት ደብዳቤ እንደምትጽፍ ለማወቅ ልቡ ክፉኛ ጓጓ ። ' በፖስታ ታሽገው ይሆን ? ' አለ ፥ አቤል ጋ ከማድረሱ በፊት ለማንበብ አሰቦ ።

ትዕግሥትን ሸኝቶ ሲመለስ ከሩቅ ስሙን የምትጠራሴት ሰማ ። ከመኝታ ክፍሏ መስኮት በኩል አይታው የጠራችው ቤተልሔም ነበረች ። ዘወር ብሎ ሽቅብ አያትና ለሰላምታ የጠራችው መስሎት እጁን አውለበለበ ።

" ቆየኝ ፥ እፈልግሃለሁ ! " አለችው ።

' ለምን ይሆን የፈለገችኝ ? ' ብሎ አሰበ ። መከረኛ ልቡ ያለ ምክንያት ሲነጥር ተሰማው ።

ፎቁን ወርዳ ድክ ድክ እያለች አጠገቡ እስክትደርስ ቆሞ ጠበቃት ።

" ኡ . . . ፍ ! ያደክማል " አለች አጠገቡ ስትደርስ ፥ ተራራ የወጣች ያህል ቶሎ ቶሎ እየተነፈሰች ።

በነጠላ ጫማ ስለ ነበረች ፥ ከእጥረቷ ጋር በማይጣጣመው ውፍረቷ ይብሱን ቁልቁል ተቀብራበት አጭር በርሜል መሰለችው ። በገጽታዋ ላይ መጠነኛ ለውጥ አስተዋለ ። የተከፋች ትመስላለች ። የምትለውን ለመስማት ቸኮለ ።

" አንተ ሲፈልጉህ አትገኝም " አለችው ።

" ይኸው ፣ አለሁ " አለ እስክንድር ፣ ፍርጥም ብሎ ።

" አትቀልድ እባክህ ! "

" ቀልድኩ እንዴ ? " አለ እስክንድር ፣ በልቡ አኳኋኗ ግራ ገብቶት ። አኳኋኗ ሁሉ ያኮረፈች ሚስት ዐይነት ሆነበት ።

በዝምታ ትንሽ ቆየች ። ስትንደረደር እንደ መጣችው ያሰበችውን በአንዴ መዘርገፍ አልቻለችም ። አጀማመሩ ቸገራት ።

" እስቲ ሻይ ጋብዘኝ ? "

" ፍራንክ አለኝ ብለሽ ነው ?! " እያለ ኪሱን ዳበሰ ። ተአምር ይፈጥር ይመስል ፣ ' አታዋርደኝ ኪሴ ! ' አለ ። ግን ኪሱ ባዶ መሆኑን አላጣውም ።

" ከሌለህ ግድ የለም ! እኔ ልጋብዝህ " አለችው ፣ ጭንቀቱ ታውቋት ።

" እም ፣ ይሻላል " አላት ፣ መደናገጡን ለመሸሸግ እየሞከረ ። ' የለኝም ' ማለት ለምን እንደሚያሳፍረው ወይም እንደሚያስደነግጠው ለራሱም ይገርመዋል ።

ግቢ ውስጥ ወደሚገኘው ሻይ ቤት ሔደው ትንሽ ከቆዩ በኋላ ፣ ቤተልሔም ሻይዋን ፉት እያለች ፣ ጨዋታዋን ጀመረች ።

" ባገኘሁህ ቁጥር እነግርሃለሁ እያልኩ " — አለችና አቋረጠች ።

" ምን ? " አላት ።

" ጓደኛዬ እንድትሆን ! "

የሐፍረት ሣቅ ሣቀች ። ስሜቱን ለማጥናት ዐይኖቿን ፊቱ ላይ ተከለች ።



ከእስክንድር አፍ ጥያቄም ሆነ መልስ አልወጣም ። የሚያባብሉ ዐይኖቿን ማየት አፍሮ አንገቱን ሰበረ ። የተቆጣ እንዳይመስል በግድ ፈገግ አለ ። ምን ለማለት እንደ ፈለገች በውል ሊገባው አልቻለም ።

" አየህ እስክንድር ፣ እኔ እዚህ ግቢ ውስጥ ስሜ ጠፍቷል ። ኃጢያቴ አልገባኝም ። አንተ አስተዋይ ሰው ነህ ። በግቢው ውስጥም ጥሩ ስም አለህ " አለችው በአንዴ ልውጥ ብላ ፣ ጭራሽ ድምጿ ወደ ለቅሶ እያደላ ።

'እና እስክንድር የተበላሸ ስም አዳሽ ነው እንዴ ?' አለ በልቡ ። ግልጽነቷ ግን አስገረመው ። ምርጫ ሲኖረን ነው ራሳችንን የምንደብቀው ። ምርጫ ማጣት ሰውን ምን ያህል ግልጽ እንደሚያደርገው ተረዳ ።

" አባባልሽ በደንብ አልገባኝም " አላት ፣ አፍ አፉን ስታየው የሚናገረው ጠፍቶት ።

" መቼም እኔ እዚህ ግቢ ውስጥ በለማ እንደምታማ ታውቃለህ " ?

" አዎ ! አዎ ፣ ዐልፎ ዐልፎ አንዳንድ ወሬ እሰማለሁ " አላት ፣ አጠያየቋ የሚያውቀውን ለመካድ አስቸግሮት ።

እንዴት እንደምትቀጥል ተቸገረች ።

" ለመሆኑ ፣ ከአስተማሪ ጋር መውጣት ወንጀል ነው እንዴ ? " ስትል እሱኑ ጠየቀችው ።

" እንደዚያ ሳይሆን፣ ግንኙነቱ ከጥቅም ጋር ስለ ተያያዘ ነው ። እ ፣ እንደምታውቂው ፣ እዚህ ግቢ ውስጥ የማርክ ነገር የተማሪዉ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው ። እንኳንስ በሌላ ግንኙነት በጭንቅላትም መበለጥ አይወድም ። እና ፣ የጥላቻው ምንጭ ይኸ ይመስለኛል " ሲል ፊቷ ከፉኛ ተለዋወጠ ።

" እምልሽ ፣ እኔ ተማሪዉ ሲያወራ የሰማሁትን ነው " አለ ፣ እንዳያስቀይማት ፈርቶ ።

" ምቀኝነት ነው ! " አለች ፣ ሳግ እየተናነቃት ። "እኔ ማንም ተማሪ በዚህ መንገድ ይተረጉምብኛል ብዬ አላሰ

ብኩም ነበር ። ለማንኛውም አሁን ከለማ ጋር ግንኙነታችን ተቋርጧል ። ”

“ በቃ ? ”

“ አዎ ፣ ከእንግዲህ በዚህ ዐይነት የምንቀጥል አይመስለኝም ። በእሱ የተነሣ ነው ፣ እንዲህ ስሜ የጠፋው ። ”

ሁለቱም ዝም አሉ ። እስክንድር ለሁኔታው ያልተዘጋጀበት ሆኖ ነው - ለአፋጣኝ ጥያቄም ሆነ መልስ የተቸገረው። ቤተልሔም ግን በዝምታው መርከብ ተሳፍራ ወደ ኋላዋ ከለማ ጋር እተጣሉበት ቀን ላይ ደርሳ ነበር ።

የሁለተኛዉ ሴሚስተር ትምህርት ተጀምሮ ለማ ምንም ኮርስ እንደማያስተምራት ካረጋገጠች በኋላ ፣ ቤተልሔም ሽርተት ለማለት ትጀምራለች ። ጭራሹን ለአንድ ሳምንት ያህል ትሰወርበታለች ። ለማ ልቡ ይጠረጥርና በዚያው ሳምንት ግቢ ውስጥ ፈልጎ ካገኛት በኋላ ፣ ቤቱ ድረስ እንድትመጣ ነብር ሆኖ ይቀጥራታል ። ቤቱ ስትሔድም ነብር ሆኖ ይቀበላታል ።

“ ምን ሆነሽ ነው እንዲህ የጠፋሽው ! ” እንደ ብራቅ ጮኸባት ።

“ ስላልተመቸኝ ነው ። ”

“ ይሽው ነው መልስሽ ? ” አላት በሽቆ ።

ዐይኗን ሰብራ ዝም አለች ። አኳኋኑ አስፈራት ። ገላጋይ በሌለበት ባዶ ቤት ውስጥ የያዛት እንደሆን ማን ይደርስላታል ? ሽንቷ ወጠራት ።

“ ምን መሰለህ ለማ ” አለችው ፣ እንባ በተናነቀው ድምፅ ። “ ዩኒቨርስቲዉ ውስጥ ስሜን እያጠፉ ነው ። ከአንተ ጋር ባለኝ ግንኙነት ክፉኛ ታምቻለሁ ። ሰላም ይሉኝ የነበሩ ተማሪዎች ሁሉ ዘግተውኛል ። ”

“ እና ? ”

“ እና ፤ ለአንተም ስም ሆነ ለእኔ ይህን ግንኙነታችንን ብናቋርጠው ይሻላል ብዬ ነው ። እኔ እዚያ ግቢ ውስጥ መኖር አልቻልኩም ። ሰውነቴ አለቀ ” አለችው ፣ ለቅሶ እየቃጣት



እንዲሁ ነች ። እስክንድርን ጠርታ ፣ “ ጓደኛዬ ሁን ” እንዳለችው መሆኑ ነው ። ብልጠቷ ስልት የለውም ። ይህ ስልት ያጣው ብልጠቷ ለማን አብከንክነው ።

“ ስሚ ! ” አላት ። መቀጠል አልቻለም ። ጉሮሮው ላይ የሆነ ነገር ተናነቀው ። ከወጣትነት ባለፈ ዕድሜው የእልህ ዕንባ እንዳያነባ ፈራ ። እናም ከምላሱ ይልቅ እጁን ማንቀሳቀስ መረጠ ። የራስጌ ኮመዲኖውን ከፍቶ አንድ ወረቀት አወጣና ሰጣት ።

“ ምንድነው ? ” አለችው ።

“ አንብቢው ! ” አላት ፣ ዐይኑን አፍጥጦ ።

በዚሁ ሳምንት ውስጥ ቢሮው ውስጥ በድብቅ ተጥሎ ያገኘው ወረቀት ነበር ። ቤተልሔም ተቀብላው ማንበብ ጀመረች .....

ጽሑፉ በቅጡ አልተቀነባበረም ። በግጥም ይጀምርና ፣

“ ...ምሁር ለማ ዘቀጠ ...

ጎሊናውን ለሴት ሸጠ ... ”

ካለ በኋላ ፣ በስድ ንባብ ይቀጥላል ። ቃላቱ ተስፋ መቁረጥን ያመለክታሉ ። በለማ ላይ የተደረደሩ ተራ ስድቦች ነበሩ ። በመሐል ደግሞ ፣

“ . . . ወሲብ አንጎል ሆኖ ሲያስመርቅ እያየሁ ፣ የእኔ ጥናት ከንቱ እንዲያው ተሠቃየሁ አወይ እኔ ፣ አወይ እኔ ! ሴቷ አለ መሆኔ ! . . . ” ይልና ፣ ተመልሶ ስድቡን ይቀጥላል ።

እንብባ ጨርሳ ቀና ስትል ፣ የምትናገረውን ለመስማት ዐይን ፀይኗን ተመለከታት ። ለእሷ ሲል የተጋፈጣቸው ችግሮች በውስጧ ኀዘን እንዲፈጥሩባት ነበር ሐሳቡ ። እንዲህ ዐይነት ነገሮችን ሥራዬ ብሎ ነው የሚነግራት ። አንዶም በመጀመሪያው ሴሚስተር አንድ ጓደኛው መቼም የቅርቤ ነው ብሎ ሊመክረው ፣ “ ለማ እዚህ ግቢ ውስጥ በአንዲት ልጅ ምክንያት ስምህ እየተበከለ ነው ” ብሎ ሲጀምር ፣ ለማ በሽቆ ፣ “ ስለዚህ ጉዳይ ምንም አታንሣብኝ ። ተፈጥሮን ተመክሮ አይመልሰውም ! ማንም የፈለገውን ሊል ይችላል ”

ብሎ ዘግቶታል ። ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ መምህራንም እየታዘቡት መሆናቸውን ሊነግረው ነበር — ጓደኛዉ የፈለ ገው ። ነገር ግን ለማ የሚበገር ሰው አልሆነም ።

በወቅቱ ይህንንም ለቤተልሔም አጫውቷታል ። " በእንቺ የተነግ ያየሁት አበሳ " ዐይነት መሆኑ ነው ። ታዲያ ያኔ ቤተልሔም አዝና ከንፈሯን መጥጣለች ነበር ።

" አበሻ ነገር መፈትፈት ልማዱ ነው ! አትጨነቅ " በማለትም አበረታታዋለች ። አሁን ግን ግጥሙን እንብባ የዚያን ዐይነት መልስ አልሰጠችውም ። እንዲያውም ለእ ፍራሽ ሐሳቧ መንገድ የጠረገላት ነው የመሰላት .....

" ... እና ፣ ከዚህ ሁሉ ነገር በኋላ ወዴት ነው ሽርተት የምትዬው ? " አላት አፍጥጦ ።

" እኔስ የፈራሁት ይህንኑ አይደል ? " አለችና ጽሑፉ ክፉኛ እንደ ቀረቀራት ሁሉ ዐይኗን አሸች ። ዕንባው ደግሞ ራሱ ካልፈቀደ እንደ ፈለጉት አይመጣ ! ዐይኗን ምራቅ እንዳትቀባ ለማ አጠገቧ ተቀምጧል ።

" መጀመሪያ ለምን ነበር የቀረብሽው ? " አላት እስ ክንድር ።

" ፈራሁኛ ! "
" ምን ? "

" ማትስ እንዳልወድቅ ። እኔ የቁጥር ዘር ጠላቴ ነው ። "

ፍቅር ብቻ ሳይሆን እልህ ጭምር ነበር የያዘው ። እስ ተያየቱ አላማራትም ። ጡንቻው ላይ አባብጠው የተጋደሙት የደም ሥሮቹ አስፈሯት ። ከተቀመጠችበት ቀስ ብላ ተነ ሣችና ወደ በሩ አመራች ።

" የት ልትሔጂ ነው ? " አለና ፣ አጠገቡ የነበረውን የአምቦ ውሃ ጠርሙስ አንሥቶ ግንባሯ ላይ አነጣጠረ ።

" ውይ ፣ ለማ ! " ብላ ጮሃ ፣ ጣውላው ላይ ቁጭ አለች ።

" ሽርሙጣ ! " አላት ፣ አጠገቧ ደርሶ ቁልቁል እየተ መለከታት ።



የሚለማመጡና የተቆጡ ዐይኖች ሽቅብና ቁልቁል ተፋ ጠጡ ። ለማ ደፍሮ እጁን ሊያሳርፍባት አልቻለም ። ዐቅፎ ለማባበልም ልቡ ያን ያህል አላላም ።

" ስሚ ! በሦስት ቀን ውስጥ አስበሽበት መልሱን ንገ ሪኝ ። የሦስት ቀን ዕድሜ ሰጥቼሻለሁ ! " አላት እንዳፈጠጠ ።

ቤተልሔም ከጣውላው ላይ ቶሎ አልተነሣችም ። በድ ንጋጤ ከጭኗ ሥር ሽንት ጠብ ያለ ስለ መሰላት ፣ እንዳይ ታይባት ፈራች ። ነገር ግን ሰውነቷን ዐልፎ ጣውላው ላይ የደረሰ ነገር አልነበረም ...

ያን ዕለት እንደ ምንም ከክፍሉ ከወጣች በኋላ ፣ መንገድ ላይ በጉዳዩ አሰበችበት ። የማይሆን ጨዋታ ነው ። የለማ ኮንትራት አልቋል ። አብራው ከቀጠለች ለሚቀጥሉት ዓላማ ዎቿ ዕንቅፋት ይሆንባታል ። ከአንድ ወንድ ጋር ብዙ መቆ የት ሌሎች የጥቅም መንገድን መዝጋት ነው ። ጥቅሙን የሚ ያሳድድ ሰው በአንድ ነገር ላይ መርጋት አይችልም ። ትር ፉን ከኪሳራው እያሰላ በሚያዋጣው መንገድ መንቀሳቀስ አለበት ... እና ለማ እስኪረሳት ድረስ ከዐይኑ ለመሰወር ወሰነች ። ከዚህ ውሳኔ በኋላ ስሟን ለማደስ በግቢው ውስጥ አብራው የምትታይ ተማሪ ስታስብ ፣ እስክንድር በሐሳብዋ ብቅ አለ ። ብዙ ተማሪዎች ከሀዷት በኋላ ፣ እሱ ሳይለወጥ እንደ ወትሮው ሰላም ይላት ስለ ነበር ነው የታሰባት .......

እስክንድር በሆዱ ሣቀ ። የግልጽ ሰው ሳይሆን የብልጥ እንበሳ ምስል ከፊቱ የቆመ መሰለው ። ለጥቅሟ የቆመች እንበሳ ! ማር ባየችበት ሁሉ የምታንነብስ በግ ! ግን ደግሞ እንስሳ ለማዳ ነው ፤ ያበላውን ያጠጣውን ፣ የቀረበውን ቶሎ ያፈቅራል ።

" ግን ታዲያ አብራችሁ ስትቆዩ ከለማ ጋር ፍቅር አል ያዘሽም ? " ሲል ጠየቃት ።

" ኤጭ ! " አለች በንቀት ።

" እሺ ፤ እሱስ ፍቅር ቢይዘው ኖሮ ? "

" እአይ ፤ እኔ አስቀድሜ ነግሬዋለሁ " አለች ፣ ግን ባሯን አኮማትራ ።

" ምን ብለሽ ? "

" አሜሪካ የመሔድ ሐሳብ እንዳለኝ ። እጮኛዬ እየጠበቀኝ ነው ። "

ማቁ እንዳያመልጠው እየሞከረ ፣ " ዋና ይዘሽ በትርፍ እየተጫወትሽ ነዋ ! " አላት ።

ፈገግ ብላ ዝም አለች ።

"የእኔም ጓደኝነትስ ምሽን እስካሳድስልሽ ድረስ ነዋ !" አላት ድንገት ግልፍ ብሎት ።

" ወይኔ ! ካንተ ጋር ' ኮ እንዲሁ ጓደኝነት ነው " አለችው ፣ ድንገተኛ ቁጣው አስደንግጧት ።

' እንዲሁ ጓደኝነት ብሎ ነገር ምንድነው ? ' ሲል አሰበ። ሐሳቡ ከውስጥ ጥቀርሻ እየለበሰ ሲመጣ ተሰማው ። የአሁኗ ቤተልሔም ሳትሆን ፣ ነገ የምትይዘው ቦታና የምትፈጽመው ተግባር ነው የታየው ። በዚህ ዐይነት ብላሽ ጥበብ ከዩኒቨርስቲ የምትመረቅ ሴት ፣ በሥራ ዓለም ስትሠማራም መሰሎቿን ታፈራና ትመለምል እንደሆን እንጂ ፣ ያስተማራትን ሕዝብ ምን ያህል ትረዳለች ? '

' አንቺና መሰሎችሽ ተመርቃችሁ በምትይዙት ቦታም የኅብረተሰቡ በሽታ ነው የምትሆኑት ! ' ሊላት ፈለገ ። ግን በምላሱ እንዲህ አምርሮ ሊያስቀይማት አልደፈረም ። ' ይልቅስ ለምን ቀርቤያት ከጥፋቷ እንድትማር አላደርጋትም ? ሴት ልጅ ውበቷንና ገላዋን ለፍቅር እንጂ ለጥቅም መሸጥ የለባትም ፣ ካለዚያ ውሎ ሲያድር እንደ ዕቃ መቆጠር ይመጣል ብዬ ለምን አልመክራትም ? እንዲህ ዐይነቱ ከንቱ ብልጠት ከቤተልሔም ጋር አብሯት አልተወለደ ፤ ከኖረችበት አካባቢ የቀሠመችው በሽታ ነው እንጂ ፣ እና ከማግለል ማስተማሩ አይሻልም ? ' የሚል የኅሊና ሙግት ገጠመው ።



ከሐሳቡ በስተጀርባ የችኮላ ስሜት ወጥሮት ነበር ። ወደ ፊት ለመሔድ እንደ ቸኮለ አልገባውም። የሚሔድበትም ጉዳይ አልነበረውም ። ከትዕግሥት ጋር የተያያዘ ስሜት ነበር የወጠረው ። እሷ ለአቤል ደብዳቤ ልትጽፍለት መሆኑን ለቅርቡ ሰው አጫውቶ ፣ ተንፍሶ እንዲወጣለት ይፈልጋል ። ግን ለማን ? ለአሥራት ? ለቢልልኝ ? ለዮናታን ? . . .

" ምነው ዝም አልክ ? " አለችው ቤተልሔም ፣ ዝምታው አስከፍቶአት ።

" አአይ ፤ እንዲሁ ነው " አለና ፣ " ግድ የለሽም ፣ ግንኙነታችን እንደ ጥንቱ ቢቀጥል ይሻላል " አላት እያመነታ ።

አኩርፋ ለመሔድ ተነሣች ።

' እፎይ ! ትሒድልኝ ' አለ እስክንድር በልቡ ።

# ምዕራፍ ሠላሳ

ማሰብና መጀመር የተለያዩ ሆነውበት ተቸግሯል — አቤል ። ሐሳቡ በጣም ይመጥቅበታል ። ሲጽፍ ያሰበው ነገር መጽሐፍ ይሆንበታል ። ለሐሳቡ መግቻ የሚያገኝ ለትም አይመስለው ። ወረቀቱን ይዞ ቁጭ ሲል ግን፣ ከብዕሩ ጠብ የሚል ነገር ይጠፋል ። ባዶ ወረቀት ላይ ፣ " ማን ፎር ሂምሰልፍ " ከሚል አርዕስት ጋር መፋጠጥ ብቻ !

'ችግሩ ከቋንቋው ይሆን ? ' ሲል አሰበ ። ' በሰው ቋንቋ ከምቸገር ሐሳቤን እንደ ልቤ ላንቀረቅርበት በምችለው በራሴ ቋንቋ ለምን አልጽፍም ? '

ባዶውን ወረቀት ከአጠገቡ አገለለና መጽሐፍ ገለጠ ። ለጽሑፉ የሚጠቅሙትን መጽሐፎች መርጦ አውጥቶ ጠረጴዛው ላይ ከምሯል ። መጻፍ ከመጀመሩ በፊት በዚህ አርዕስተ - ጉዳይ ላይ የተጻፉ ብዙ መጽሐፎች ማንበብ እንዳለበት ስለ ተረዳ፣ ሰሞኑን እያነበበ ነበር። ችግሩ ግን ከሚያነበው መጽሐፍ ላይ ብዙ ሰዓት መቆየት አለ መቻሉ ነው ። ከመጽሐፉ ውስጥ ጠቃሚ ሐሳብ ሲያገኝ የእሱ ሐሳብ ቀድሞ ይመጥቅና ጻፍ ጻፍ ይለዋል ።

አሁንም ከተቀመጠበት ተነሥቶ ትንሽ ተንጎራደደ ። ከመንጐራደዱ ጋርም የሚጽፈው ነገር ብልጭ አለለት ።

ሰው ከራሱ ጋር የሚጣላው ለምንድነው ? በግል ምኞትና ግብ አእምሮው ተወጥሮ ሲጨነቅ ነው ። ነገር ግን የሰው ልጅ የመጨረሻ ግቡ እኛ እንጂ፣ እኔ መሆን የለበትም ። ከራሱ ጋር ሊታረቅ የሚችለው በዚህ እምነት ተጠምቆ ከግሉ ይልቅ ለማኅበራዊ ችግር ክብደት ሲሰጥና ደስታውን ከኅብረተሰቡ ጣፋጭ ሕይወት ውስጥ ለማግኘት ሲሞክር ነው ። ሰው በመጀመሪያ ለሕያውነቱ ከፍተኛ ግምት

መስጠትና ማድነቅ አለበት ። ይህን ካመነ ደግሞ ማናቸውም
በውስጡ የሚከሠቱ ነገሮች የሕያውነቱ ነጸብራቆች ስለሆኑ
እንዳመጣጣቸው ተቀብሎ መፍታት እንጂ ለችግሮች መረ
ታት የለበትም ። ሰው በትግሉ በተፈጥሮ ላይ ፍጹም የበላ
ይነቱን መቀዳጀት አለበት ።

አቤል መጻፍ የፈለገውን መቋጠሪያ ሐሳብ ያገኘ መስ
ለው ። ደስ ደስ አለው ። በአንጻሩ ግን ከውስጡ አዘናጊ
ስሜት ይታገለው ነበር ። ‘ አይ አቤል ! አሁንስ ጅል ሆንክ ፤
አዲስ ሐሳብ ያፈለቅክ መስሎህ ነው ? ስንት ፈላስፋዎች
ብለውት ብለውት የበቃውን ነገር እንዴት እንደ አዲስ
ታነሣዋለህ ? እባክህ ይልቅ ያልተባለ አዲስ ነገር ፈልግ ።
ለዚያውስ በዚህ ዓለም ላይ ምን ያልተባለ ነገር አለ ? ’

አቤል የራሱ ስሜት አስጠላው ። ‘ ለምንድነው ስሜቱ
ገንቢውን ትቶ አፍራሹ ላይ የሚሮጠው ? አዲሱ ሰው ሁሉን
ነገር “ ተብሏል ” እያለ ራሱን የሚያዘናጋ ከሆነና እጁን
አጣምሮ ከተቀመጠ ነገር ተበላሸ ። ከአሁን በፊትም ማንም
ቢሆን ፍጹም አዲስ ነገር ይዞ አልተነሣም ። ሁሉም ዕውቀ
ቱን የቀመረው በተከሠተ ወይም በተባለ ነገር ላይ እየቆመ
ነው ። እና ፣ አቤል አቤልሻ ! ይልቅ ደፍረህ ጀምር ፣ የዐቅ
ምህን ሞክር ፤ ሜር ! ’ አለና ፣ እንደገና ቁጭ አለ ።

እንዴት እንደሚጀምረው ቁልጭ ብሎ ታየው ። ስፌ
አርዕስት ነው የያዘው ፤ ስለዚህ በንዑስ ርዕስ ከፋፍሎ ፣ እያን
ዳንዱን ንዑስ ክፍል በጽሑፍ ማስረጃና በሕይወት ገጠመኝ
አስደግፎ ማስኬድ ! ሰውነቱን አንዳች የደስታ ስሜት ወረ
ረው ። ሐሳቡ ካለበት መጥቆ ሲሮጥ ንዑስ ርዕሱ ልጓም ሆኖ
ያዘለት ። ሰው የራሱ ወዳጅ የሚሆንበትን ሐሳብ ከመደር
ደሩ በፊት ከራሱ ጋር የሚጣላባቸውን ሁኔታዎች ለመደር
ደር ተገደደ ። እዚህ ላይ ለመድረስ ደግሞ፣ ሰው በተፈጥሮ
ይዟቸው የሚወጣውንና ከአካባቢው የሚቀስማቸውን ዐበ
ይት ጸባያት ይዞ መነሣት ነበረበት ። የጅማሬ ሐሳቡን በዚህ
ንዑስ ርዕስ ሥር አጠቃልሎ ፣ “ በዚህ ዓለም ላይ ታላቅና
ክቡር ፍጡር ነው ” ሲል ጀመረ ።

በተመስጦ እየጻፈና ደጋፊ ሐሳቦች ፍለጋ መጽሐፎች
እያገላበጠ ትንሽ እንደ ቆየ ፣ ሞኒካ ሻይ ይዛለት መጣች።



የአምስት ሰዓት ሻይ ነበር ። ጊዜው ከምኔው እንደ ሮጠ
ገረመው ።

“ ጽሑፉን ጀመርኩት ‘ ኮ ” አላት ፣ ገና እየገባች
ሳለች ።

“ ዳስ ኢስት ሸን ” አለችው ሞኒካ ፣ ፈገግ ብላ ደስ
ታዋን በመግለጽ ።

አቤል ይህንኑ “ ጀመርኩት ” የሚለውን ቃል ለዮና
ታንም ለመንገር ተቻኮለ ። እንዲያመጡለት የጠየቃቸውን
የቀድሞ የተበላሹ የጥናት ጽሑፎቹን ባመጡለት ጊዜ ፣ የገባ
ላቸው ቃል ትዝ አለው ። ወረቀቶቹን ተቀብሎ ፊታቸው በከ
ብሪት ካቃጠለ በኋላ ፣ “ አሁን ከፊትዎ የቆመው አዲሱ
አቤል ነው ። አዲስ ጽሑፍ አዘጋጅቶ ያሳይዎታል ” ብሏ
ቸው ነበር ። አሁን ዮናታን የሚመጡበት የምሳ ሰዓት ራቀ
በት ።

ሞኒካ አሁን አቤል ያለበትን ጥሩ ስሜት ካረጋገጠች
በኋላ፣ ወደ መኝታ ክፍሏ ሔዳ አንድ ጉርድ ፎቶግራፍና የታ
ሸገ ኢንቬሎፕ ይዛ ተመለሰች ።

“ ይህችን ልጅ ታውቃታለህ ? ” አለችው ፣ ፎቶውን
ዐይኑ ሥር አቅርባ ።

ፋት ብሎ የነበረውን ሻይ ቶሎ መዋጥ አቃተው ።
የልብ ትርታ የሚቀሰቅስ ምስል ! አስደንግጦ የሚያስደስት
ምስል ! ‘ ማወቅ ብቻ ነው ! ? አምልኬባታለሁ እንጂ ! ’ ሊላት
ፈለገ። የሞኒካ ቶሎ መልስ መፈለግ ግን፣ አቤል ነገሩን አመ
ዛዝኖ እንዲናገር ጊዜ አልሰጠውም ።

“ አዎ ! ” አላት ፣ ሌላውን ስሜቱን ዋጥ አድርጎ ።

“ የት ? ”

“ ዩኒቨርስቲ ውስጥ አንድ ሴሚስተር ሙሉ በዐይን
ፍቅር የማቀቅኩላት ናት ” አላት ፣ ቃናው በተለወጠ ድምፅ ።

“ ከዚህ ፎቶዋ ጋር ደብዳቤ ልካልሃለች ” አለችና
የታሸገውን ፖስታ ሰጠችው። ፈጥኖ ተቀበላት ። ነገር ግን፣

ፈጥኖ መቅደድ አልቻለም ። አንዳች ነገር እጁን የያዘው ይመስል ተንቀጠቀጠ ።

በሚያነብበት ጊዜ ነጻ እንዲሆን በማሰብ ሞኒካ ክፍሉን ለቅቃለት ወጣች ። ደብዳቤዉንና ፎቶዉን ከእስክንድር ከተቀበለች ሁለት ቀን አልፎአል ። ለአቤል ወድያውኑ ያልሰጠችው እንዲህ ጥሩ ስሜት እስኪታይበት በመጠበቅ ነበር ።

አቤል ደብዳቤዉን ገልጾ ማንበብ ጀመረ ፡—

“ አቤል ፣ ስምህን ደብዳቤ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ስጽፈው የተሰማኝን ስሜት ልገልጽልህ አልችልም ። የምወደውንና የምፈልገውን ቃል መጥራት ለምን እንደሚያስፈራኝ ሊገባኝ አልቻለም ። የዚህን ደብዳቤ ረቂቅ ብታየው ትገረማለህ ። ስርዝ — ድልዝ ብቻ ነው ። ከስሜቴ ጋር ክፉኛ መታገሌን በዚህ መገመት ትችላለህ ።

“ ይህን ደብዳቤ እንድጽፍልህ ያደፋፈረኝ እስክንድር ነው ። ጥሩ ጓደኛ ነው ያለህ ። እሱ ባይገፋፋኝ ኖሮ እንዲሁ ስሜቴን አምቄ ውስጥ ውስጤን እሠቃያለሁ እንጂ ከቶም አልሞክረውም ነበር ። አንተ በእኔ የተነሣ የተቀበልከውን ሥቃይ ስሰማ ለብቻዬ ተደብቄ ስቅስቅ ብዬ ነው ያለቀሥኩት ፤ ግን ጥፋተኛው ማን ነው ? እየህ አቤል ! እኔ መቼም ሴት ነኝ ፤ ድፍሬ መጥቼ እንዳላነጋግርህ የአካባቢ ተጽዕኖ አለብኝ ። አንተ ግን በሩቅ ከምትሠቃይ ቀርበህ ብታነጋግረኝና እወድሻለሁ ብትለኝ ምን ነበረበት ።

“ሕመምህ ጠልቆ የተሰማኝ አሁን ነው ። ለካስ ፍቅር ተገጣጥሞ ካልሰመረ ሥቃይ ነው ። በካምፓስ ውስጥ አንተን በዐይኔ ካጣሁበት ጊዜ ጀምሮ ያለሁበትን ሁኔታ ልገልጽልህ አልችልም ። አንተን ለማየት እናፍቃለሁ ፤ ብቸኝነት ያሠቃየኛል ፣ አካባቢዬ ያስጠላኛል ፤ ጥናት ያንገሸግሸኛል ፤ ሁሉ ነገር ከብዶና መርሮ ይታየኛል ። እውነቴን ነው የምልህ ! የተፈጥሮ ክሥተት ባይሆን ኖሮ፣ አፍላ ፍቅር ፈጽሞ አያስመኝም ።

“ በመጀመሪያው ሴሚስተር ከትምህርቴ እንዳልሰናከል እፈራ ስለ ነበር፣ ፍቅርህን ክፉኛ ታቃውሜዋለሁ ።



አሁን የተረዳሁት ነገር ቢኖር ግን ፣ ፍቅር ታግለው የሚጥሉት ነገር አለመሆኑን ነው ። ገና መጀመሪያ የዩኒቨርስቲውን ግቢ ስረግጥ ካየኸኝ ጀምሮ በዐይን እንደምትከተለኝ ያልተረዳሁልህ እንዳይመስልህ ። እያንዳንዱ እይታህ ከንግግር የበለጠ ተሰምታኛለች ። እንዲያውም አንዳንዴ ቃላት መግለጽ የማይችሉትን ዐይን እንደሚናገር ተረድቻለሁ ። በተለይ ፣ ታስታውስ እንደሆነ ፣ አንድ ቀን እኔ ፣ ማርታና ቤተልሔም ከካምፓስ ወጥተን ስንሔድ ምን ያህል በቅናት ስሜት እንደ ተመለከትከኝ መቼም አልረሳውም ። አንተ ሌላ ቦታ የምንሔድ መስሎህ ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን የሔድነው ሰርግ ቤት ተጠርተን ነበር ። ታዲያ ያኔ የዋልኩት ውሎ ውሎ አይበለው ! በቅናት የተከተለኝ ዐይን ፣ ዐይኔ ውስጥ ቀርቶ ፣ ቀኑን ሙሉ ሲለበልበኝ ነው የዋለው . . .

“ ይህን ሁሉ የምጽፈው የቆየ ቁስልህን ለመቀስቀስ አይደለም ። በአንድ በኩል ደብዳቤው በእርግጥ ከእኔ ከትዕግሥት የተላከልህ መሆኑን እንድታምንበት ሲሆን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ስሜትህ ያልገባኝ ወይም ሥቃይህን ያልተረዳሁልህ እንዳይመስልህ ነው ።

“ከላይ እንደ ገለጽኩልህ ፣ ችግሩን በመፍራት ፍቅርህን ታግዬ የማሸንፈው አልሆንኩም ። ብሞክረውም አንተን መርሳት ፍጹም የማይቻል ሙከራ ሆነብኝ ። ምክንያቱም በአካባቢዬ ሴቶች ስለ አንተ ሲያወሩ በሰማሁ ቁጥር ስሜቴ ይቀሰቀሳል ። ስምህን የሚያውቁት ፣ ‘ ያ ጎበዙ ተማሪ’ በሚል ቅጽል ነው የሚጠሩህ ። ይህ ቃል በእኔ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ነው ያሳደረብኝ ። በጉብዝናው በሚደነቅ ተማሪ መፈቀር ደስ ያሰኘኛል ። ግን ደግሞ ግንኙነታችን ከዐይን አለ ማለፉን ሳመዛዝን ያበሽቀኛል ። ያ ሁሉ ዐልፎአል ። አሁን ስሜቴን አፍረጥርጬ ያወጣሁልህ ይመስለኛል ። አንተም ግልጽ ሁንልኝ ። ፍቅርን ሕመም ያደረግነው እኛው ነን ፤ እባክህ ጐን ለጐን ቁጭ ብለን አንተ በእኔ ፣ እኔ ባንተ እንደሰት ። ትምህርትህ በእኔ ምክንያት በመቋረጡ አዝናለሁ ። የምረዳህም ሆነ የምክስህ ነገር ቢኖር፣ ከወዲሁ ሙሉ ፈቃደኝነቴን እገል

ጽልሃለሁ ። በእኔ ግምት ካሳው ፍቅር ነው ። ፍቅሬን ሰጥቼህ ፍቅርህን ከመቀበል ሌላ ምን መፍትሔ ይኖራል ?

ያንተው ትዕግሥት አዳነ ”

አቤል ደብዳቤውን ሁለቴ አንብቦ በዝግታ አጠፈው ። እውስጡ ያነበበው የፍቅር ቃላትን ብቻ ሳይሆን እንባም ጭምር ነው ። ትዕግሥት ፊቷ በእንባ ሳይታጠብ ይህን ደብዳቤ ጻፈች ማለት ዘበት ነው ። ጽሑፉን ያነበበ ሳይሆን ድምጿን የሰማ መሰለው ። ግን በእርግጥ ትዕግሥት እንዲህ ግልጽ ሆና የውስጧን የምትናገር ሴት ትሆን ? ‘ ማነው ጥፋተኛው ? ’ የሚለው ቃል ታወሰውና ፣ ‘ እውነት ማነው ?’ ሲል አሰበ ። እሷንም ራሱንም ጥፋተኛ ማድረግ አልቻለም ። ‘ አንዲት የፍቅር ቃል — እወድሻለሁ ብትለኝ ’ ያለ ችው አንጀቱን በላው ። ነገር ግን ቃሏ አንድ መሆኗ ሳይሆን ክብደቷ ነው ለትዕግሥት ያልገባት ። ይህችን በፍቅረኛ ፊት መተንፈስ መቻል ምንኛ መታደል ነው !

ስለ እስክንድር አሰበ ። ለደብዳቤዉ መጻፍ ያደረገው ጥረት አስገረመው ። ከአሁን በፊትም እሱን ለመርዳት ያደ ረገው ሙከራ ሁሉ ታወሰው ። ከራሱ ጋር ተጣልቶ በስይጣ ናዊ ግፊት ፎቅ ላይ በቆመበት ጊዜ፣የደረሰለት ዕለት ትዝ አለው ። “ እባክህ ችግርህን ንገረኝና ልረዳልህ ፣ ብቻህን አትጨነቅ ” በማለት አቤልን የወተወተበትም ጊዜ ነበር ። እና አሁን ጥረቱ ፍሬ አስገኘ ።

“ አንብበህ ጨረስክ ? ” አለችው ሞኒካ ፣ ተመልሳ መጥታ ። ዐይኑ ዕንባ አቅርሮ ተመለከተች ። አቤል በትዕ ግሥት የፍቅር ቃላት ልቡ ተነክቶ የፍቅር ዕንባ ሲያነባ፣ከአ ሁን በፊት በእሷ ምክንያት የደረሰበት ቁስል እየሻረለት ነበር ።

“ አዎ ጨረስኩ ” አላት ዝግ ባለ ድምፅ ፣ ዐይን ዐይኗን እያየ ።

“ እንዴት ነው ? ”

“ ድንቅ ነው ፤ ሸጋ ነው ! ”

“ እኔም መልስ መጻፍ ይኖርብኛል ” አላት ጸጉሩን እያሻሸ ።



“ እዚሁ ድረስ ትመጣልሃለች ። ደብዳቤ መጻፍም አያስፈልግህ ” አለችው ሞኒካ ፣ ፈገግ እንዳለች ።

“ መቼ ? ”

“ እሑድ ጠዋት ። ”

የያዘውን ቀን አሰበ ። ሐሙስ ነው ። ለእሑድ ገና ሁለት ቀንና ሦስት ሌሊት ይቀረዋል ። እንዴት ይደርስ ይሆን ? የትዕግሥትን ፎቶግራፍ ከጠረጴዛው ላይ አንሥቶ እንደገና ተመለከተው ።

አቤል በዚህ ሐሳብ ውስጥ በመዋዠቅ ላይ እንዳለ የምሳ ሰዓት ደርሶ ዮናታን መጡ ። ከምሳቸው በፊት ወደ ጥናት ክፍሉ ወስዶ ያስተናገዳቸው አቤል ነበር ።

“ ጽሑፉን ’ ኮ ጀመርኩት ! ” አላቸው ፣ በደስታና በኩራት ድምፅ ።

“ ግሩም ! ” አሉት ዮናታን ፣ ጠረጴዛዉ ላይ ያሉትን ቁሳቁሶች እያዩ ። የትዕግሥት ፎቶግራፍ ከመጽሐፉና ከወ ረቀቶቹ ጐልቶ ታያቸው ። ሊጠይቁት አሰቡና ስሜታቸውን ቆንጠጥ አደረጉ ። አሁንም እንደ ድሮው ይደብቃቸው ይሆን ?

“ እሷም ልትመጣ ነው ፤ ደብዳቤዋ ደርሶኛል ” አላቸው ፣ ዐይናቸውን ተከትሎ ስሜታቸው ያረፈበትን በመገመት ።

“ ግሩም ! ሥራና ፍቅር ተገጣጠሙ በለኛ ! ” አሉት ፣ ደስታ ፈንቅሎአቸው ።

ዐይናቸው ከፎቶግራፉ ወደ ጥናት ጽሑፉ ሲሸጋገር ደግሞ ከወረቀቱ አናት ላይ ፣ “ በዚህ ዓለም ላይ ታላቅና ክቡር ፍጡር ሰው ነው ” የሚለው መንደርደሪያ ደምቆ ተመለከቱ ።

‘ ፍጹም ጤናማ አመለካከት ነው ፤ ጤናማ ኅብረተሰብ የጤናማ ግለሰቦች ውጤት ነው ’ ብለው አሰቡ ።

"በጅማሬህ በጣም ተደስቼአለሁ ። ቀጥልበት ። ታላቅ ሥራ ሠርተህ ታላቅ ሰው የምትሆንበትን ጊዜ በተስፋ እጠብቃለሁ" አሉት ።

ፈገግ እያለ ዐይን ዐይናቸውን ተመለከታቸው ። መነጽሩን ዐልፎ ዐይናቸው ውስጥ ፍቅር ይነበባል ።

የመጨረሻ ዐረፍተ ነገራቸው ጭንቅላቱ ውስጥ ደወለበት ።



# ምዕራፍ ሠላሳአንድ

የጠዋት ፀሐይ የማንንም ፈቃድ ሳትጠይቅ ፈገግ ብላ በዝግታ ወደ ጥናት ክፍሉ ገባች ። ፈገግታዋ ሙቀት እንጂ ድምፅ ስለ ሌለው ፥ አቤል ቶሎ አላያትም ። እያዘገመች የተቀመጠበት ወንበር ላይ ደርሳ ግራ ጐኑን ስትሞቀው ነቃ — ከእንቅልፉ ሳይሆን በተመስጦ ይሠራው ከነበረው ጽሑፍ ላይ ። እና ፥ ብዕሩን ወረቀቱ ላይ ወርውሮ በተቀመጠበት ተንጠራራ ። ሰውነቱን አፍታታ ።

እጁ ላይ ሰዓት የለም ። ነገር ግን፥ከንጋቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ መሆኑን ለመገመት አልተቸገረም ። ከተቀመጠበት ሳይንቃነቅ ሦስት ሰዓት ያህል መቆየቱ አላስገረመውም ። ከሌሊቱ ዐሥር ሰዓት ከእንቅልፉ እየነቃ እስከ ንጋት ድረስ መሥራት፥ሰሞኑን ልማድ እያደረገው መጥቷል ። በንጹሕ አእምሮ ስለሚሠራ ፥ ፍሬያማ ውጤትም አግኝቶበታል ። ዮናታን ይህንኑ በመመልከት ለማንቃት እንዲረዳው የሳሎኑን ባለደወል የጠረጴዛ ሰዓት መኝታ ክፍሉ ውስጥ አድርጎ ውለታል ። ቀን ቀን ለጥናት ጽሑፉ የሚረዱትን መጽሐፎች ሲያገላብጥ ውሎ፥ በዚች በሌሊቷ ሰዓት መጻፉ ጥሩ መንገድ ሆኖለታል ።

ተንጠራርቶ ሲያበቃ ከተቀመጠበት ተነሣ ። ወደ በረንዳው መናፈሻ ብቅ ብሎ፥ፀሐይዋን ሙሉ በሙሉ ሊሞቃት ፈለገ ። የሰንበት ፀሐይ ! ጭለማው ገልጦ የእሑድ ፀሐይ ብቅ ካለች ከውጭ የሚመጣ ሰው አለ ። ስለዚህ የእሑድ እንግዳውን ለመቀበል ጸጉሩን ማበጣጠር ፥ ልብሱን መቀያየር ነበረበት ።

ጸጉሩን ሲያበጥር ልቡ ድቤ መምታት ጀመረ ። ዕረፍ ብለው አያሳርፉት ነገር ! የልብን ከበሮ አይቆጣጠሩት ነገር ! የገዛ ልቡ አናደደው ። በድንገት የበሩን ደወል የሰማ መስ

ለው ። ተሳስቷል ። ናፍቆቷ የፈጠረው ደወል ካልሆነ በስተቀር ፥ በክፍሉ ውስጥ የተሰማ ድምፅ የለም ። የሹካ ፥ ማንኪያና የሰሐን ድምፅ ግን በርግጥ ከሌላኛዉ ክፍል ይሰማል ። ያቺ ሞኒካ ስትንደፋደፍ ነው ። መቼም እሷ ጠዋት መተኛት አትወድ !

ወደ በረንዳው መናፈሻ ወጥቶ ከፎቁ ቁልቁል ተመለከተ ። የዮናታን መኪና እቦታዋ የለችም ። ጠዋት ሲነሡ ስለ ሰማ፥የት እንደሔዱ አላጣውም።በአስፋልቱ ላይ ከሚሠሩ መኪናዎች መሐል ነጥሎ የሚለያትይ መስል ዐይኑን ወደ ሩቅ ወረወረ ። የቤት መኪናዎች እምብዛም የሉም ። ታክሲዎች ናቸው ሽቅብ ቁልቁል ውር ውር የሚሉት ።

ቆሞ መጠበቁ ሰለቸው ። የቆመበት ጊዜ ከዐሥራ አምስት ደቂቃ ባይበልጥም ለእሱ የዓመት ያህል ረዘመበት ። ‘ ምን ሆነው እንዲህ ቆዩ ? ’ አለ በሐሳቡ። ‘ አልሔድም ብላቸው ይሆን ? ወይስ የሙሽራ ልብስ አልብሰው ሊያመጧት ይሆን ? ’

ትዕግሥቱ አልቆ ወደ ውስጥ ተመለሰና ሞኒካ ጋ ሔዶ። ወጥ ቤት ውስጥ ምግብ እያበሰለች ነበር ። የቡታ ጋዙ ሦስቱም ምድጃ ድስት ተጥዶበታል ። ሰርግ ሰርግ ሸትተው ፤ የወጡ ሽታ ራብ ለቀቀበት ። ቁሌቱ ገና ይንተሸቱሻል ። የበሰለው ደግሞ ክዳኑን ሽቅብ እየገፈተረ ይንተከተካል ። ሞኒካ ፊት ላይ ከፉኛ መቻኮል አነበበ ።

“ ምን ልርዳሽ ? ” አላት ። እሷም ፈገግ ብላ ፥ ከምድጃው ላይ አንዱን ድስት አውርዳ ፥ ቡና በማንቀርቀሪያ እንዲጥድላት ነገረችው ።

ሁለቱም የሥራ ድርሻቸው ላይ አትኩረው እግረ መንገዳቸውን ስለ ጽሑፍ ሥራው ሁኔታ በመጨዋወት ላይ እንዳሉ ድንገት ደወሉ ተንቃጨለ ።

አቤል ሲሰማው በላብ ተጠመቀ ፤ጭንቅ አለው ፤የልቡ ትርታ ፍጥነቱን ጨመረ ። ‘ ምን ሰው ያስደነግጣሉ ! ቀስ ብለው አይደውሉም እንዴ ? ’ የቡና ማንቆርቆሪያ ክዳን እንደ ወደቀበት ያስተዋለው ቆየት ብሎ ፥ ትንሽ ከተረጋጋ በኋላ ነው ።



ሞኒካ ዋናውን በር ከፍታ እንግዶቿን ስትቀበል ፥ አቤል ወጥ ቤት ውስጥ እንደ ቆመ ጆሮውን ላከ ። የተነባበረ የጫማ ድምፅ ። የማን የማን ይሆን ? የዮናታን ፥ የእስክንድር ። የሚሰማው የወንዶች ድምፅ ብቻ ሆነበት ። የልቡ ምት ስላስፈራው ደረቱን በእጁ ደገፈ ። ወዲያው ግን ሞኒካ ራሷን በእንግሊዝኛ ስታስተዋውቅ ስለ ሰማ አዲስ ሰው መምጣቱን ገመተ ።

ያላበውን እጁን አጠገቡ ያገኘው ነገር ላይ ጠራረገ ። ግንባሩን ፥ ጉንጩን ዐይኑን በእጁ አሻሸ ። እንደ ቆመ ጸጉሩን አበጣጠረ ። የሸሚዝ ኮሌታውን እያስተካከለ በረዥሙ ተነፈሰ — ጭንቀት የሚያባርር ፥ ፍርሐት የሚያስወግድ አተነፋፈስ ! እና ርምጃውን በልቡ እየቆጠረ ወደ ሳሎን ገባ ።

ከአጭር ጠይም ሴት ልጅ ጋር ዐይን ለዐይን ተገጣጠሙ ። የሁሉም ፊት በፈገግታ ደምቆአል ። ከፈገግታው ሁሉ ለአቤል ጐልቶ የታየው የትዕግሥት ነው ። በጉንጯ መሰርጐድ የታጀበ ፈገግታ ! ይህን ፈገግታዋን ለመጀመሪያ ጊዜ ካየው አንሥቶ ከአምስት ወር ራብ በኋላ ማየቱ ነው ። የሚወደውን የጉንጯን ስርጉድ ቀርቦ ሲያይ የመጀመሪያው ጊዜው መሆኑ ነው ። ማንን ቀድሞ መጨበጥ እንዳለበት ግራ ገብቶት ሲርበተበት አብራው የቆየችውን ሞኒካንም እንደ አዲስ ጨበጣት ።

ለእስክንድር ያለውን ስሜት ቆንጥጦ መያዝ አልቻለም ። ስሜቱ ፈንቅሎት ጉንጩን ጥብቅ አድርጐ ሳመውና ፥ “ ይህ ሁሉ የአንተ ጥረት ያስገኘው ፍሬ ነው ” አለው ። ፊቱን በቅጽበት ወደ ዮናታን መልሶ ፥ “ እና ደግሞ የርስዎ ! ” አላቸው ። ፍቅሩን በዐይኑ ከመግለጽ በቀር ተንጠራርቶ ሊስማቸው አልደፈረም ። ሦስተኛ ባለውለታውን ሊያመሰግን ዘወር ሲል ከአጠገቡ አጣት ። ሞኒካ ድስት ሲገነፍል ሰምታ እየሮጠች ወደ ወጥ ቤቱ ተመልሳ ነበር ።

ትዕግሥት በነጭ የሀገር ልብስ ነው የመጣችው ። አቤል ይህንኑ ለብሳ የተመለከተበትን እሑድ ወዲያው አሷ ስታወስም ። ቆይቶ ቆይቶ ነው ከእነ ማርታ ጋር ሰርግ ሴት

ሔድ ለብሳው እንደ ነበር ያስታወሰው። ለላምታውንና ምስጋናውን ጨርሶ ሲቀመጥም ልቡ አልተረጋጋም ነበር ። ይበልጥ የትርታውን ፍጥነትና አስጭናቂነት ጨመረ ። ዘሎ ዘሎ አንዴ ቀጥ እንዳይል አቤል ፈራ ።

ትዕግሥት ማለት እሷ ነች ። ታዲያ የተመኙትን ሲያገኙ መንቀጥቀጥ ነው ? ደብዳቤዉ ያሳደረበት ስሜትና ሲገናኙ የደረሰው ሁኔታ ባለመገጣጠሙ በልቡ በሽቀ ። ያ ሁሉ የፍቅር ቃላት ጋጋታ ምን ዋጠው ? ይኖራል ! ጸጥታውን የሚሰብርለት ድምፅ እጥቶ ነው እንጂ በሁለቱም ውስጥ አለ ።

አቤል አንዳች ቃል መተንፈስ ፈልጎ ምላሱን ተጠራጠረው ። ምናልባት የተሳሰረበት እንደሆንስ ? ከፍቅር እመቤቱ ፊት የተቀመጠው ገላው የሚንቀጠቀጥ — ጀርከ የሚመታ መሰለው ።

በድንገት ዐይኑ የእጁ ጠባሳ ላይ ዐረፈ ። ምግብ አዳራሹ ውስጥ የወደቀ ጊዜ የወጡ ፍንጣቂ ያተረፈለት ጠባሳ ። መጥፎ ስሜት አልተናነቀውም ። መጥፎ የልብ ጠባሳ ነበር እንጂ የእጅ ጠባሳ ምንም አይደለም ። የልቡን ቁስል ደብዳቤዋ ባመነጨበት እንባ ካጠበው ሰንብቷል ።

“ ተጫወች እንጂ ” የሚል ቃል እንደ ምንም ከአፉ ገፍትሮ አወጣ ።

ትዕግሥት በእሺታ ፈገግ አለች ። ፈገግታዋ ጠዋት ከሥራው ላይ ካባነነችው ፀሐይ ይበልጥ ደምቆ ታየው ።

ሳያስቡት የዝምታው ባሕር ዮናታንና እስክንድርንም ውጦአቸው ነበር ። ከተቀመጡ ጀምሮ ቃል አልተነፈሱም ። ታዛቢ ባይሆኑም ታዛቢ መሰለዋል ። ወጥ ቤት ውስጥ የሚንተሸተሸው ምግብ ሽታ የእስክንድርን አንጀት እያላወሰው ነበር ። በአፉ ምራቅ ሲሞላ ተሰማው ።

“ በመጀመሪያ የመኝታና የጥናት ክፍሎችህን ለትዕግሥት አስጎብኛታ ! ” አለ ዮናታን ፣ በቤቱ ውስጥ እንቅስቃሴና ድምፅ ለመፍጠር በማሰብ ።



አቤል ከትዕግሥት ጋር ተነሣ ። ዮናታንና እስክንድርን በዝግታ ከኋላቸው ተከተሏቸው ።

“ ፍቅራቸው በጥሩ መልክ ይቀጥል ይሆን ? ” አለ እስክንድር በሹክሹክታ ድምፅ ፣ ወደ ዮናታን ጆሮ ጠጋ ብሎ ።

“ ቢቀጥል መልካም ነው ። ባይቀጥልም አቤልን እንዳለፈው አይጐዳውም ። ተቀራርበው ቃላት ከተለዋወጡ ዐይኑን መግለጥ ይችላል ” አሉ ዮናታንም በሹክሹክታ ።

በአቤልና ትዕግሥት መሐከል የጫማቸው ድምፅ ካልሆነ በስተቀር የቃላት ልውውጥ አልተሰማም ። የመኝታ ክፍሉን ጎብኝታ ወደ ጥናት ክፍሉ ስትገባ ግን ትዕግሥት ተነፈሰች ።

“ በጣም ትልቅ ይቅርታ ! ” አለችው ፣ ዐይኗ ዕንባ አቅርሮ ።

“ ምነው ለምን ? ” አላት ፣ ዕንባዋ የቀሰቀሰበትን ስሜት ከጉሮሮው ወደ ውስጥ ለመዋጥ እየታገለ ።

“ ትምህርትህ በእኔ ምክንያት በመቋረጡ ይቅርታ አድርግልኝ !! ”

“ ታዲያ አንቺ ምን አጠፋሽ ? ” አለና አቤል አሁንም ጉሮሮው ላይ የሚተናነቀውን ነገር በምራቁ አወራርዶ ፣ “ ይልቅ እዚሁ ቤት የጥናት ጽሑፍ ማዘጋጀት ጀምሬአለሁ ። ለሥራው የሚረዱኝ መጽሐፎችና ሐሳቦች በማፈላለግ ትረጂኛለሽ ? ” አላት ።

ፈቃደኝነቷን ለመግለጽ ራስን መነቅነቅ ወይም ቃላት መናገር አላስፈለገም ።

“ እና ትምህርቴንም በአዲስ ዓመት ፣ በአዲስ ልቦና ፣ በአዲስ ተስፋ እቀጥላለሁ ። ”

ቃላት አንሰዋቸው ዐይን ለዐይን ሲተያዩ አልተፋፈሩም ። ዐይኗ ብሌን ውስጥ ምስሉን ሲመለከት እሷም ዐይኑ ብሌን ውስጥ ምስሏን እየተመለከተች ነበር ።

ትዕግሥት ከአቤል ዐይን ዳርቻ ላይ ዐይን እር አየች ። ልትጠርግለት ብትሞክርም እጅዋ ይንቀጠቀጥ ይሆን ? እንደ ምንም ደፍራ እጅዋን ዘርግታ በጣቷ አነሣችለት ።

" ምንድን ነው ? " አላት ከንፈሩ እየተንቀጠቀጠ ።
" ጉድፍ " አለችው ፣ የእሷም ከንፈር እየተንቀጠቀጠ ።

ዐይኑን የነካው እጅዋን ጥብቅ አድርጎ ሳመው ።

ዮናታንና እስክንድር በደስታ ፈዘው ቀሩ ። እውን ሳይ ሆን የፊልም ትርኢት የሚያዩ ነበር የመሰላቸው ። በተለይ እስክንድር ራሱን መቆጣጠር አቅቶት፣ እንደ ሕፃን ፈንደቅ ፈንደቅ የሚል ስሜት ታገለው። ደስታ በሣቅ ፣ ሣቅም በጥርስ የሚገለጽ ነገር ባይሆን ኖሮ መላ ሰውነቱ እየሣቀ ነበር ።

ለአፍታ ያህል ጓደኞቻቸው ፊቱ ላይ ድቅን አሉበት ። ማርታ የነገር ቅንድቧን እያርገበገበች ፣ ድብርት በጋቢው ተጀቡኖ እየተልጐመጐመ ፣ ሚስተር ሆርስ ቼሱን ታቅፎ ቅልጥሙን እንደ ዘረጋ ፣ ቤተልሔም በሩጫና ሰዓት ወደ ሽንት ቤት እየሮጠች ፣ ሳምሶን ጉልቤው ጡንቻውን ወጣ ጥሮ ለአቤል ሲማታለት እየተጋበዘ — ሁሉም በእስክንድር ሐሳብ ውስጥ ተሰለፈ ። ' ምነው አንዳፍታ መጥተው ይህን ትርኢት ለማየት በታደሉ ! ' አለ በልቡ ።

አቤል የትዕግሥትን እጅ ስሞ አልለቀቀውም ። እን ደገና ወደ ደረቱ አስጠግቶ ጥብቅ አርጐ ያዘው ። እጅዋ እንደ ኤሌትሪክ ሽቦ የአቤልን ልብ ትርታ እየተቀበለ ወደ እሷ ያስተላልፍ ጀመር ። ትርታው ነዘሯት አላፈገፈገ ችም ። ይልቁንም መላ ሰውነቷን በዝግታ ወደ አቤል አካል አስጠጋችው ። ትንፋሻቸው ተገጣጠመ ። ሁለቱ እንደ አንድ ሰው !

" እ — እ — እወድሻለሁ ። "
አስቸግራው የኖረችውን አንዲት ቃል ተነፈሳት ።